# የምክር ቤት ዘርፍ
# የሙስና መከላከል እና ሥነ-ምግባር ግንባታ

## (የሥልጠና ሞጁል)

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

— ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ —

CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ህዳር 2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

# የምክር ቤት ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥነምግባር ግንባታ
# (የሥልጠና ሞጁል)

ህዳር 2017

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

# የምክር ቤት ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥነምግባር ግንባታ

## (የሥልጠና ሞጁል)


አዘጋጆች፡-

ያሲን ሁሴን (PhD) (አርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ)

ተስፋዬ ጆማ (PhD) (አዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ)

አርታኢ፡-

አቶ ሀረጎት አብርሃ

አቶ የኋላሸት ደሳለኝ

አቶ ቤዛ በኃይሉ

አቶ አንተነህ ሀይሌ

ግራፊክስ ዲዛይን፡-

አቶ በለጠ ብርሀኑ


© የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን

**ህዳር 2017 ዓ.ም**

## ማውጫ

**መሪ ምልክቶች**.....................................................................................iii

**መግቢያ**..........................................................................................................1

**ምዕራፍ አንድ - የሙስና እና ስነ መግባር አጠቃላይ ገጽታ** ........................................3

**1.1 ክፍል አንድ የሙስና ወንጀል ምንነት**.......................................................3

1.1.1 የሙስና ምንነት..........................................................................................3

1.1.2 የሙስና ዓይነቶች........................................................................................4

1.1.3 የሙስና ወንጀል ምንነት...............................................................................4

1.1.4 በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች.......................................5

**1.2 ክፍል ሁለት - የሥነምግባር አጠቃላይ ገጽታ**..............................................13

1.2.1 የሥነምግባር ትርጉም..................................................................................14

1.2.2 የሥነምግባር ደንብ ምንነት..........................................................................15

1.2.3 ሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ.........................................................................16

**ምዕራፍ ሁለት - የምክር ቤት ዘርፍ የሙስና ስጋት ተጋላጭነት እና የሙስና መከላከያ ስልቶች:**....................................................................................................20

**2.1 ክፍል አንድ የምክር ቤት ዘርፍ የሙስና ስጋት ተጋላጭነት እና የሙስና አይነቶች**

2.1.1 የፓርላማ ሥርዓት ምንነት...........................................................................20

2.1.2 የፓርላማ ስርአትና ሙስና መከላከል...............................................................23

2.1.3 የምክር ቤት ዘርፍ የሙስና ስጋት ተጋላጭነት....................................................25

2.1.4 በምክር ቤት ዘርፍ የሚፈጸሙ የሙስና አይነት....................................................32

**2.2 ክፍል ሁለት - የምክር ቤት ዘርፍ የሙስና መከላከያ ስልቶች:**............................37

2.2.1 የዘርፉን የሰው ሃይል ማጎልበት......................................................................38

2.2.2 ግልጽነትና ተጠያቂነት ማስፈን......................................................................38

2.2.3 የሥነ-ምግባር ደንብን ተግባራዊ ማድረግ ........................................................39

2.2.4 የሃብትና ጥቅም ማሳወቅና ማስመዝገብ.............................................................39

2.2.5 የጥቅም ግጭትን የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን መከላከል..............................................39

2.2.6 የዘርፉን የፀረ-ሙስና ሚና ሚንስትሪም/የስራ አካል ማድረግ...................................40

2.2.7 የመንግስት የስራ ሃላፊዎች ሚናን ማጠናከር......................................................40

2.2.8 ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራት……………………………41
2.2.9 ቴክኖሎጂን መጠቀም………..…………………………………………...41
**ምዕራፍ ሶስት- የምክርቤት ዘርፍ ሙስናና ብልሹ አሠራርን የመከላከል ሚና እና ማጎልበቻ መንገዶች**……………………………………………………………………43
**3.1 ክፍል አንድ- የምክርቤት ዘርፍ ሙስናና ብልሹ አሠራርን የመከላከል ሚና**
3.1.1 ወቅታዊ የሆኑ ሕጎች እንዲወጡ ማድረግ……………………………………44
3.1.2 በረቂቅ ህጎች ላይ የሙስና ስጋት ትንተና ማድረግ..………………………………46
3.1.3 በመንግሥት ተቋማት ላይ የሚደረግ ክትትልና ቁጥጥር..…………………………48
3.1.4 የበጀት አመዳደብ..……………………………………………………56
3.1.5 የሚሾሙ የሥራ አስፈፀሚ አባላት ማጽደቅ……………………………………59
**3.2 ክፍል ሁለት- የምክርቤት ዘርፍ ሙስናና ብልሹ አሠራርን የመከላከል ሚናቸውን ማጎልበቻ መንገዶች**……………..……………………………………………………63
3.2.1 ሙስናን በመከላከል ዙሪያ የሰራተኞች እና አባላትን ግንዛቤ ማሳደግ………………63
3.2.2 ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነፃ መሆን...………………………………………....64
3.2.3 የዴሞክራሲ ሥርዓት እና ባህል እንዲጎለብት የላቀ ሚና መወጣት.....................64
3.2.4 የጠባቂ (Watchdog) ተቋማትን ለየት ባለ መንገድ የመደገፍ አቅምን ማሳደግ......66
3.2.5 የሙስናና ብልሹ አሠራርን መረጃ ማግኛ ሥርዓት ማጠናከር..……………………67
3.2.6 የዜጎችን አመኔታ የሚገነቡ ተግባራትን ማጠናከር እና አርአያ መሆን……………...69

**መሪ ምልክቶች**




መግቢያ



ዓላማ



ማነቃቂያ ጥያቄ



ተግባር መወያያ ጥያቄዎች



አስረጅ ናሙና



የምዕራፉ ማጠቃለያ



የምዕራፍ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

# መግቢያ

ሙስና ያላደጉትንም ሆነ ያደጉትን ሃገራት እየፈተነ ያለ አለምአቀፍ ችግር ነው፡፡ በአፋጻጸሙም በብዙኃን እና የተለያዩ አካላት ተሳትፎ እና መስተጋብር የሚፈጸም የወንጀል ተግባር ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ቀዳሚ የወንጀሉ ተዋናይ ከሚሆኑት አካላት መካከል ባለሀብቶች፣ በየዘርፉ የላቀና ከፍተኛ ዕውቀትና ሙያ ያላቸው ሰዎችና የመንግሥት ባለሥልጣናት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ተግባሩ በመካከላቸው በሚመሠረት ጥቅም ላይ የተመሠረተው ስብስብ ግንኙነት እና ቁርኝት በመሆኑ ሙስናን የመዋጋትን ሥራ አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ሙስና በሀገር ጥቅምና እድገት ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ከፍተኛ መሆኑን በመገንዘብ የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴዎችን የመምራትና የማቀናጀት ተልዕኮን በመቀበል በዘርፉ ከተሰለፉ ባለድርሻ አካላት ጋር እየሰራ ይገኛል፡፡

እነዚሁ ባለድርሻ አካላት የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በብቃትና ዕውቀት ላይ በተመሠረተ ሁኔታ የፀረ-ሙስና ጥረቶችን እንዲያስተባብርና እንዲያቀናጅ ይፈልጋሉ፡፡ ፍላጎታቸው ከሚጠበቁት አገልግሎት አንጻር ሲጤን ትምህርትና ሥልጠና ማግኘት፤ የአሠራር ሥርዓት ጥናት እንዲጠናላቸው መፈለግ፣ የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ጽሑፎች ዝግጅት ላይ የምክር አገልግሎት ማግኘት፣ የህትመትና የኤክትሮኒክስ ውጤቶችን በበቂ፣ደረጃውን እና ጥራቱን በጠበቀ ሁኔታ ማግኘት ሆኖ ይታያል፡፡

ባለድርሻ አካላት በሙስና መከላከል ረገድ ከኮሚሽኑ ጎን ሊቆሙ የሚችሉት በዘርፉ የተሻለ ዕውቀትና ክሂሎት እንዲሁም ለእንቅስቃሴው ቁርጠኛ አቋም መያዝ ሲችሉ ብቻ ነው፡፡ የባለድርሻ አካላትን አቅም ከዚሁ አንጻር ለመገንባት የሚያስችሉ የሥልጠና ሞጁሎች ዝግጅት ውስጥ በምክር ቤት ዘርፍ ላሉ ተቋማት የሚዘጋጀው አንዱ ነው፡፡

## የስልጠና ሞጁሉ ዋና አላማ

የዚህ ሞጁል ዋና ዓላማ በምክርቤት ዘርፍ ባለ ተቋማት የሚስተዋሉ የሙስና ስጋቶችና መከላከያ ስልቶች እነዲሁም በዘርፈ ያሉ ተቋማት ሙስናን በመዋጋትና በመከላከል ረገድ ያላቸውን ሚና በተመለከተ ግንዛቤ፣ አቅም እና ሁለንተናዊ ተሳትፎን ለማጎልበት የሚያስችል ዕውቀት፤ ክሂሎትና አመለካከት አደራጅቶ ማቅረብ ነው፡፡ ይህንን መሠረታዊ ዓላማ ለማሳካትና ሥልጠናውን ወደ ተግባር ማውረድ እንዲያስችል አጠቃላይ እሳቤዎችን ከተጨባጭ ሀገራዊ ኩነቶችና ከሠልጣኞች ተሞክሮዎች ጋር በተዛመደ ሁኔታ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

## የሞጁል አወቃቀር

ይህ ሞጁል በክፍል በተደራጁ ሶስት ምዕራፎች የተዋቀረ ሲሆን የመጀመርያው ምእራፍ የሙስናና የሥነምግባር ገጽታዎችን በቅደም ተከተል የሚዳስስ ሲሆን ሁለተኛው ምእራፍ ላይ በምክር ቤት ዘርፍ ሊኖሩ የሚችሉ የሙስና ተጋላጭነት ስጋቶች እና የሙስና አይነቶች ተዳሰውበታል፡፡ በዚሁ ምእራፍ ላይ የሙስና መከላከያ ስልቶች ጠቅለል ባለ መልኩ ቀርበዋል፡፡ በምእራፍ ሶስት ደግሞ የምክር ቤት ዘርፍ ተቋማት ሙስናንና ብልሹ አሰራርን በመከላከል ረገድ ያላቸው ሚና እና ማጎልበቻ መንገዶች ሰፋ ብሎ ቀርቧል፡፡ እያንዳንዱ ምዕራፍ የየራሱ መግቢያ፣አላማ፣ ለስልጠናው የተሰጠ ጊዜ ይኖራዋል፡፡

## የስልጠናው ተተኳሪዎች

ይህ የስልጠና ሞጁል በዘርፉ ውስጥ ባሉ ተቋማት ለሚገኙ ሰራተኞች እና ለም/ቤት አባላት ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን እንደየተቋማቱ ነባራዊ ሁኔታ ራሱን ችሎ በሚዘጋጅ የሥልጠና መርሐ ግብር ያተገበራል፡፡

## የስልጠናው ስነ ዘዴ

ስልጠናው  የሠልጣኞች ንቁ ተሳትፎን፣ ውይይትንና ቀደምት እውቀትን የሚጋብዝ ሲሆን ሠልጣኞች ወደ አዲስ ርእስ ከመግባታቸው በፊት የቀደመ ተሞክሯቸውን በማንሳት ከርእሱ ጋር ለማገናኘት እንዲጥሩ በሚያስችል አቀራረብ ተዘጋጅቷል፡፡ ለዚህም እንዲረዳ የማነቃቂያ ጥያቄዎች፣ አስረጅ ናሙናዎች፣የውይይት ጥያቆዎች እንዲሁም መጨረሻ ላይ የማጠቃለያ ሀሳብና የምዕራፍ ማጠቃለያ ጥያቄዎችም ቀርበዋል፡፡

## የማሰልጠኛ ግብዓቶች

ሰልጠናውን ውጤታማ ለማድረግ ፓወር ፖይንት፤ማርከር፤ ፍሊፕ ቻርት፣ ፕሮጀክተር፣ ፖይንተር እና ላፕቶፕ ኮምፒውተር የመሳሰሉ ግብአቶችን ማሟላት ያስፈልጋል፡፡

## ስልጠናው የሚወስደው ጊዜ

እንደሁኔታው የሚጨምር ወይም የሚቀንስ ሆኖ አስራ ሁለት ሰዓት የሚሸፈን ሆኖ የተዘጋጀ ስልጠና ነው፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# የሙስና እና ስነ ምግባር አጠቃላይ ገጽታ

## መግቢያ

የሙስና መከላከል ስራን በተጨባጭ ለመስራት ስለሙስና ወንጀል ምንነት አስቀድሞ መረዳት ተገቢ ነው፣ ምክንያቱም ብዙ ሰዎች የሙስና ወንጀልን ከጉቦ መስጠትና መቀብል ጋር ብቻ አያይዘው ስለሚረዱት ነው፡፡ ይሁንና ለሙስና ምንነት አንድ አለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት ባይቻልም የሙስና ወንጀል መገለጫዎችን ግን ዘርዝሮ ማየት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ሰልጣኞች በሙስና መከላከል ዙሪያ ተገቢውን እውቀትና ክህሎት እንዲያገኙ ይህ ምእራፍ የሙስና ወንጀል ምንነትና መገለጫዎችን የሚቀርቡበት ምእራፍ ነው፡፡

ሌላው በዚህ ምእራፍ የተዳሰሰው ጉዳይ ስነ ምግባርን የተመለከተ ነው፡፡ ስነ ምግባር የተሟላ ስብዕና የሚገነባበት መሰረት ነው፡፡ በተለይ እንደ ፓርላማ ያሉ የመንግስት ቁልፍ ተቋማት ካላቸው ከፍተኛ ሀገራዊ ተልእኮ አንጻር ስነ ምግበር የተላበሰ አሰራር መተግበር እና ለህዝቡ አርዓያ ሆነው መገኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይሁን እንጅ በአለም ደረጃ የምክር ቤት አባላት ላይ የሚስተዋል የስነ ምግባር ጉድለት እና ሙስና እየተባበሰ ያለ አሳሳቢ ችግር ነው፡፡ ስለሆነም የሥነምግባር ግንባታ ላይ በፍጥነት እና ትኩረት መስራት እንደ ማህበረሰብም ሆነ እነደ ሃገር ለመቀጠል የግድ መከወን ያለበት ተግባር ነው፡፡

ስለሆነም የግልጽነትና የተጠያቂነት ሥርዐትን በመዘርጋት በዘርፉ ተቋማት ሰራተኞች እና ም/ቤት አባላት ላይ የሚስተዋሉ የስነ ምግባር ችግሮችን መቅረፍ ተገቢ ነው፡፡ ይህን ለማሳካት በሚደረገው ጥረት ውስጥ ደግም የዘርፉ ተቋማት ሰራተኞች እና የምክር ቤት አባላት የሥነምግባርን ምንነትና አጠቃላይ ገጽታ በቅጡ መረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ ምእራፍ በክፍል ሁለት ትኩረቱን እዚሁ ላይ በማድረግ የሥነምግባር ምንነት እና መሠረታዊ ባሕርያት፣ የሥነምግባር ደንብ እና የሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ የሚሉትን ጉዳዮች ይዳስሳል፡፡

## የምእራፉ ዓላማ

**ከዚህ ምእራፍ መጠናቀቅ በኋላ ሰልጣኞች፡-**

- የሙስና ወንጀል ምንነትን ይለያሉ፤
- በሀገራችን ያሉትን የሙስና ወንጀሎች መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፤
- የሥነምግባር ምንነት እና መሠረታዊ ባሕርያትና ገጽታዎች ያብራራሉ፤
- የሥነምግባር ደንብ ለተቋማቸው ሰራተኞች/አባላት ያለውን አስፈላጊነት ይገልፃሉ፤
- የሥነ ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ዓይነቶችን ያስረዳሉ፤

**የሚወስደው ጊዜ፡** 2፡00 ሰዓት

## 1.1 ክፍል አንድ የሙስና ወንጀል ምንነት

### 1.1.1 የሙስና ምንነት

 **የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

1. ከጉቦ ውጭ የምታውቁትን የሙስና ወንጀል ዓይነቶችን ዘርዝሩ
2. ሙስና ማለት ሌብነት ነው በሚለው ሃሳብ መስማማት አለመስማማታችሁን አስረዱ።

ሙስና የሚለዉ ቃል የሚያስተላልፈዉን ትርጉም በተገቢዉ ደረጃ ተገንዝቦ አንድ ሊያስማማ የሚችል ሁሉን አቀፍ የሕግ ትርጉም ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቷል። ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል (Transparency International) የተባለ ተቋም "ሙስና" የሚለዉን ቃል ሲፈታዉ እንዲህ ይላል። Corruption is defined as "Misuse of Entrusted Power for Private Gain." በዚህ ትርጉም መሰረት "ሙስና ማለት በአደራ የተሰጠን ሥልጣን አላግባብ ለግል ጥቅም ማዋል" ነዉ የሚል ሲሆን ከዚህ መረዳት የሚቻለዉ በአደራ የተሰጠን ሥልጣን አላግባብ በመገልገል ጉዳይን አላግባብ ማጓተት ወይም አላግባብ ፈቃድ በመስጠትና በማጽደቅ ጉቦ ወይም የማይገባ ጥቅም መቀበል በሙስና ወንጀል እንደሚያስጠይቅ ይገልጻል።

### 1.1.2 የሙስና ዓይነቶች

የሙስና ወንጀሎችን አይነት የበለጠ ለመረዳ በሁለት ተከፍለዉ ቀላል እና ከባድ ወይም (petty and grand) በሚል ለመረዳት መሞከር ይቻላል። በዚህም መሰረት ቀላል ሙስና በታችኛዉ ሀላፊነት እርከን ወይም በዝቅተኛ መጠን የሚፈፀሙትን በሚመለከት ሲሆን ከባድ ደግሞ በከፍተኛ ስልጣን እርከን ወይም በብዙ መጠን የሚፈፀም ወንጀልን የሚመለከት ነዉ። ከባድ ሙስና ስር ሲሰድ ስርአታዊ (systemic) በመሆን መንግስትን ሊቆጣጠር (state capture) የሚችል ነዉ።

### 1.1.3 የሙስና ወንጀል ምንነት

የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና ማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/1993 ለመጀመሪያ ጊዜ ለሙስና ወንጀል ትርጉም የሰጠና በወቅቱ በስራ ላይ በነበረዉ የ1949 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ዉስጥ ከሚገኙ የወንጀል ድንጋጌዎች መካከል የሙስና ወንጀል ሊባሉ የሚችሉትን ያስቀመጠ ህግ ነበር። በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2(1) ለሙስና ወንጀል የተሰጠዉ ትርጓሜ የሚከተለዉን ይመስላል፦

የሙስና ወንጀል ማለት ከመንግስት ወይም ከህዝብ አገልግሎት ወይም ከህዝብ ጥቅም ጋር በተያያዘ የሚፈጸም ማናቸዉም ወንጀል ሆኖ የተመደበበትን የመንግስት ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራ ያለአግባብ በመጠቀም ለራስ ወይም ለሌላ ሰዉ ወይም ቡድን ጥቅም መጠየቅ፣

የተስፋ ቃል መቀበል ወይም ማግኘት ወይም ሌላዉን ሰዉ መጉዳት ሲሆን መደለያ መቀበልን፣ጉቦን፣ የማይገባ ጥቅም መቀበልን፣በስልጣን መነገድን፣ በስልጣን ያለአግባብ መገልገልን፣ የመንግስት ስራ ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራን ለግል ጥቅም በሚያመች አኳኋን መምራትን፣በስራ ተግባር ላይ የሚፈጸም መዉሰድና መሰወርን፣በመንግስት ስራ ላይ ሆኖ በማስገደድ መጠቀምን፣ሚስጥር ማባከንን እና የመሳሳሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል" የሚል ትርጉም ተሰጥቶት ነበር፡፡

ሆኖም በዚህ አዋጅ ለሙስና ወንጀሎች የተሰጠዉ ትርጉም የተወሰኑ የሙስና ወንጀል የሚሆኑ የወንጀል አይነቶችን የዘረዘረ ቢሆንም ጉቦ መስጠትና ማቀባበል ፣ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ይዞ መገኘት፣ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና የመሳሰሉትን የሙስና ወንጀሎች የማያካትት ከመሆኑም በላይ *"... የመሳሰሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል..."* በሚል የተቀመጠዉ ሀረግ በክስ አቀራረብና ዉሳኔ አሰጣጥ ላይ መቋጫ የሌለዉ የትርጉም ልዩነት በዳኞች ፣በዓቃቤ ህጎች እና በጠበቆች መካከል እንዲፈጠር አድርጎ ነበር፡፡

ከ1996 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ ዉስጥ በተግባር የታዩ ችግሮችን በመፍታት የተሟላ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር በማድረግ የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማጠናከር እና ሀገራችን ያሰባትን አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ግዴታ በአግባቡ እንድትወጣ ለማድረግ እና በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝባዉ ድርጅት ሰራተኞች፣በመንግስት የልማት ድርጅት ሰራተኞች እና በመንግስት ሰራተኞች የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በማካተት ይዞ የወጣዉ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ነዉ፡፡

የሙስና ወንጀል ድንጋጌዎች በአዋጅ ቁጥር 881/2007 ላይ ከአንቀጽ 9 እስከ 33 ላይ ተመልክቷል፡፡ በህጉ አወቃቀር መሠረት የሙስና ወንጀል ተብለው የተለዩት በ25 አንቀፆች የተጠቃለሉ ጉዳዮች ብቻ ናቸው፡፡

### 1.1.4 በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች

#### 1.1.4.1 በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል (አንቀፅ 9)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ፤ የተሰጠውን ሹመት፣ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት በግልፅ ተግባር(በማድረግ) ወይም በግድፈት(ባለማድረግ) ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ፤ በግልፅ ከተሰጠው ሥልጣን ወይም ኃላፊነት አሳልፎ የሠራ እንደሆነ፤ ወይም ሥልጣን ወይም ኃላፊነት ሳይኖረው ወይም ከሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ ወይም ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ የሠራበት እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

### 1.1.4.2 ጉቦ መቀበል (አንቀፅ 10)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራ ግዴታዉ ማድረግ የማይገባዉን ለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ላለማድረግ በቀጥታም ወይም በተዘዋዋሪ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ጥቅም እንዲሰጥ ጠየቀ ፣የተቀበለ እንደሆነ  በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.1.4.3 የማይገባ ጥቅም መቀበል (አንቀፅ 11)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ማድረግ የሚገባውን ተግባር ለማከናወን ሲል ይህንኑ ተግባር ከመፈፀሙ በፊት ወይም ከፈፀመ በኋላ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ፣ ያገኘ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.1.4.4 አስታራቂ ሽማግሌዎችና ሌሎች ሰዎች የሚፈፅሙት ጉቦ የመቀበል ወንጀል (አንቀጽ 12)

ማንኛዉም አስታራቂ ሽማግሌ ፣የግልግል ዳኛ፣ የፍርድ ቤት ነባሪ ፣ ንብረት ጠባቂ ፣ወይም አጣሪ ፣ሥራዉን ለማካሄድ በባለስልጣን የተሾመ ተርጓሚ ወይም አስተርጓሚ ወይም በዳኝነት ወይም በዳኝነት ነክ በሚታይ ጉዳይ ላይ በሙያዉ ረገድ አስተያየቱን ወይም የምስክርነት ቃሉን

የሚሰጥ ማንኛዉም ልዩ አዋቂ (ኤክስፐርት) ፣ወይም ገቢና ወጪን ኦዲት የሚያደርግ ኦዲተር፣ ወይም ግንባታ በተገባዉ ዉል መሰረት መከናወኑን የሚረጋግጥ መሃንዲስ ማድረግ የሚገባዉን ላለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ለማድረግ ጉዳ ከሚመለከተዉ ሰዉ ላይ ጥቅም እንዲሰጠዉ የጠየቀ ወይም ተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.1.4.5 የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ስራን በማያመች አኳኋን መምራት (አንቀጽ 13)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት፣ ወይም ለማስገኘት በማሰብ ሥልጣኑን ወይም ሃላፊነቱን ተጠቅሞ፦

በንግድ ወይም በሌላ ሥራ፣ በግዢ ወይም በሽያጭ ወይም ከሚያከናውነው ሥራ ጋር በተያያዘ በማናቸውም የሥራ ግንኙነት ማናቸዉንም ዓይነት ጥቅም የወሰደ ወይም ይህን ጥቅም የሚያገኝበትን ውል የተዋዋለ፤ ወይም ሌላ ዘዴ የፈጠረ እንደሆነ፤

አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ከተወሰነው በላይ በሆነ ዋጋ የዕቃ ማቅረብ ውል፣የሥራ መቋረጥ ውል ወይም ማናቸውም የሥራ ውል የተዋዋለ ወይም በዉል ከተመለከተው ዕቃ ወይም አገልግሎት ውጭ የተቀበለ እንደሆነ፤

በጠቅላላዉ በሥራዉ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት መሠረት በአደራ የተሰጠዉን ወይም ሊጠብቀዉና ሊከላከለዉ የሚገባዉን የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ጥቅም የሚጎዳ ተግባር በማናቸዉም ዘዴ የፈፀመ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.1.4.6 አደራ በተሠጠው ዕቃ ያለአግባብ ማዘዝ (አንቀፅ 14)

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በሕግ አግባብ ሳይፈቀድለትና የግል ንብረት ለማድረግ በማሰብ ሳይሆን ታሽጎ የተረከበዉን ጥቅል፣ ኢንቨሎፕ፣ ሰነድ፣ ባለዋጋ ነገር፣ ወይም እንደታሸገ የተረከበውን ማናቸውንም ዕቃ፦

የከፈተ፣ ያስከፈተ፣ የወሰደ ወይም ያስወሰደ ወይም የእሽጉን ይዘት የገለጠ ወይም ዕቃውን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም የተገለገለበት ወይም ሌላ ሰው እንዲገለገልበት የፈቀደ እንደሆነ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### 1.1.4.7 በሥራ ተግባር የሚፈፀም የመውሰድና የመሰወር ወንጀል (አንቀፅ 15)

የማይገባ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ ማንኛዉም የመንግሥት ሠራተኛ በብርበራ፣ በመያዝ፣ በመውረስ ሥርዓት፣ በሐራጅ ሽያጭ፣ በህግ ውርስ ወይም ፍርዱ በንብረቱ ላይ እንዲፈፀም በመወሰኑ ወይም ይህን የመሰለ ማናቸውም ሥራ በሚያከናውንበት ወይም በሚያስፈፅምበት ጊዜ፤ ወይም

የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በማንኛውም የሥራ አጋጣሚ በእጁ ሊገቡ የቻሉትን ወይም በአደራ የተረከባቸውን ወይም የሚጠብቃቸውን፤ ዕቃዎችን፣ ሰነዶችን፣ ባለዋጋ ነገሮችን፣ጥሬ ገንዘቦችን፣ ተንሳቃሽ ወይም አላቂ ዕቃዎችን የወሰደ ወይም የሰወረ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.1.4.8 በሥልጣን ወይም በኃላፊነት መነገድ (አንቀፅ 16)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በሥራው ምክንያት ባለው ወይም አስመስሎ ባቀረበው ተሰሚነት፦

አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ተወስኖ የሚሰጥ የሥራ ደረጃ፣ ሹመት፣ ሥራ ፣ ሽልማት፣ የአገልግሎት ዋጋ፣ ልዩ ችሮታ፤

በቁጥጥሩ ወይም በአመራሩ ሥር በሚገኙ ባለስልጣኖች፣ኃላፊዎች ወይም የአስተዳደር ክፍሎች የሚደረግ ዉል፣የንግድ ስምምነት፣የስራ ጨረታ፣የዕቃ ማቅረብ ዉል ፣ወይም ሌላ ጥቅም ወይም

በአጠቃላይ ከአንድ ባለስልጣን ፣ኃላፊ ወይም የአስተዳደር ክፍል የሚሰጠዉን ጥቅም ወይም የሚረዳ ዉሳኔ፣ ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ስጦታ ወይም ሌላ ጥቅም የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.1.4.9 በህገወጥ መንገድ መሰብሳብ ወይም ማስረከብ (አንቀፅ 17)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት በማሰብ፦

ሊከፈል የማይገባ መሆኑን ወይም በህግ ከተወሰነው ታሪፍ በላይ መሆኑን እያወቀ ቀረጥ፣ ግብር፣ ልዩ ልዩ ገቢ ወይም ልዩ ልዩ የገቢ ጥቅም ፣ ምንዳ፣ ደመወዝ፣ ካሳ ወይም ሌላ ወጪ የሰበሰበ ወይም እንዲሰበሰብ ያዘዘ እንደሆነ፤

ማናቸውንም ዕቃ ወይም ክፍያ በሚያስረከብበት ወይም በሚሰጥበት ጊዜ ማስረከብ ወይም መክፈል ከሚገባው አሳንሶ ያስረከበ ወይም የከፈለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

### 1.1.4.10 ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት (አንቀፅ 18)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራዉ ምክንያት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ጥቅም ካለዉ ማንኛዉም ሰዉ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ጥቅም ለማግኘት ፣በጉዳዩ ላይ ጥቅም ያለዉን ማንኛዉንም ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ሲል ከህግ፣ ከሥራ ደንብ፣ ወይም ከመመሪያ ወይም ከተለመደዉ አሠራር ዉጭ ያለ በቂ ምክንያት ያልወሰነ ፣ያዘገየ ወይም ባለጉዳዩን ያጉላላ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.1.4.11 ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማግኘት (አንቀፅ 19)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረው ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸውንም ዋጋ ያለውን ነገር የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

ሁለተኛዉ በዚህ አንቀፅ የሚያስቀጣዉ ድርጊት ንብረትን፣ የፋይናንስ አቋምን፣ ስጦታ መቀበልን ማስመዝገብ ወይም ማሳወቅ እንደሚገባ በህግ ወይም በደንብ በተደነገገ ጊዜ አለማሳወቅ በተመሳሳይ ያስቀጣል፡፡

በአገሩ ወይም በአካባቢው ባህል ወይም ልማድ መሠረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለው ሥጦታ መቀበል ወይም ከስጋ ወይም ከጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም የቅርብ ወዳጅ ስጦታ ማግኘት አያስጠይቅም፡፡

### 1.1.4.12 ያለአግባብ ፍቃድ መስጠት ወይም ማፅደቅ (አንቀፅ 20)

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት፣ብቁ ላልሆነ ወይም በህግ ሊሰጠው ለማይገባ ሰው ማናቸውንም የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ የሰጠ ወይም ያፀደቀ ወይም እንደሆነ፣ ወይም አንድ ነገር የሚከናወንበትን ቦታ ያለአግባብ የፈቀደ ወይም የሰጠ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.1.4.13 ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ (አንቀፅ 21)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የሆነ ወይም የነበረ ሰዉ  የኑሮ ደረጃዉ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ የበለጠ እንደሆነ፤

ያለዉ ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚየገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ በሙስና መንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.1.4.14 የሥራ ሚስጥርን መግለፅ (አንቀፅ 22)

አግባብነት ባለዉ ህግ አያስጠይቅም ተብሎ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ፣ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰዉ ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ በሥራዉ ምክንያት ያወቀዉ ሆኖ በጠባዩ ሚስጥር የሆነዉን ወይም በሚስጥር እንዲጠበቅ የታዘዘዉን ወይም ለህዝብ እንዳይገለጽ የተከለከለዉን መረጃ ፣ሰነድ ወይም ፍሬ ነገር ሥራዉን ወይም ሹመቱን ከለቀቀ በኋላ ቢሆንም እንኳ የገለጸ ወይም የስተላለፈ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.1.4.15 መንግሥታዊ ወይም የህዝባዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት፣ ወደ ሐሰት መለወጥ ወይም በሐሰተኛ ሰነድ መገልገል (አንቀፅ 23)

ማንኛዉም ሰው  የሌላዉን ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ማናቸውንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ታስቦ የሚፈፀም ነዉ፤

አንድ ፅሁፍ፣ መዝገብ ወይም ማንኛውንም ሰነድ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት በማስመሰል ያዘጋጀ ወይም የፈጠረ እንደሆነ፤

በመንግሥት ወይም በህዝባዊ ድርጅት መዝገብ ፣ፅሁፍ ወይም ሰነድ የሰፈረን እውነተኛ ፅሁፍ በመለወጥ ወይም በመደለዝ፣ በሐሰተኛ ፊርማ፣ በእጅ በተደረገ ምልክት ወይም በጣት ፊርማ፣ በማህተም ወይም የሌለውን ሥልጣን ወይም ችሎታ እንዳለው አስመስሎ በመፈረም ሐሰተኛ ሰነድ የፈጠረ፤ ወደ ሐሰት በተለወጠ ወይም በሐሰት በተዘጋጀ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ፤ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.1.4.16 መንግስታዊ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን ማጥፋት ወይም ጉዳት ማድረስ (አንቀፅ 24)

ማንኛዉም ሰዉ የሌላዉን ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ተገቢ ያልሆነ ማናቸዉንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝብ ሰነድ ላይ ጉዳት እንዲደርስበት ያደረገ ፣የቀደደ፣ ያጠፋ ፣ጥቅም ላይ እንዳይዉል ያደረገ ወይም የወሰደ  እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

### 1.1.4.17 ዋጋ ያለዉን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ መስጠት (አንቀፅ 26)

ማንኛዉም ሰዉ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረዉ ለማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ወይም ከእርሱ ጋር ግንኙነት ላለዉ ማንኛዉም ሌላ ሰዉ ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸዉንም ዋጋ ያለዉ ነገር ያቀረበ ፣የሰጠ ወይም ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ያስጠይቃል፡፡

በአገሩ ወይም በአካባቢዉ ባህል ወይም ልማድ መሰረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለዉ ስጦታ መስጠት ወይም ለስጋ  ወይም ለጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም ለቅርብ ወዳጅ ስጦታ መስጠት አያስጠቅም፡፡

### 1.1.4.18 ጉቦ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መስጠት (አንቀፅ 25)

ማንኛዉም ሰዉ አንድ የመንግስት ሠራተኛ ወይም የህዝባዉ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በስራ ግዴታዉ ማድረግ የማይገባዉን እንዲያደርግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን እንዳያደርግ ጥቅም ወይም ስጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.1.4.19 ማቀባበል (አንቀፅ 27)

ማንኛዉም ሰዉ ለራሱ ማናቸዉንም ዓይነት ጥቅም ባያገኝም እንኳ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራን ለሚያከናዉን ሰዉ ጉቦ ለመስጠት ገንዘብ ፣ዋጋ ያለዉ ነገር

፣አገልግሎት ወይም ሌላ ዓይነት ጥቅም ከሌላ ሰዉ የተቀበለ እንደሆነ፤ ወይም የራሱን የባንክ ሂሳብ እንደዚህ ዓይነት ጉቦ ለማቀባበል ያዋለ እንደሆነ፤ ወይመ ጉቦ እንዲሰጣጡ ሁኔታዎችን ያመቻቸ ፣ያገናኘ ፣ ያስማማ ወይም የደለለ እንደደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል።

### 1.1.4.20 በሌለው ሥልጣን መጠቀም (አንቀፅ 28)

ማንኛውም ሰው ከመንግሥት ወይም ከህዝባዊ ድርጅት ሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ፣ ከተወገደ ወይም ሥልጣኑን፣ ኃላፊነቱን ከተወ በኂላ በሥራው ላይ ያለ በማስመሰል፤ለወደፊቱ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ እሆናለሁ ብሎ በማሳመን ወይም ሠራተኛ ሳይሆን መስሎ በመቅረብ፤
ይህንን አደርጋለሁ በማለት የተስፋ ቃል በመግባት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ወይም ሥጦታ ከሌላ ሰው የጠየቀ፣ የተቀበለ እንደሆነ ይጠየቃል፣

### 1.1.4.21 በግል ተሰሚነት መነገድ (አንቀፅ 29)

ማንኛውም ሰው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ባይሆንም በሰዎች ዘንድ ያለውን ወይም እንዳለው ያስመሰለውን ተሰሚነት በመጠቀም በአንድ የመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ብቻ ሊሰጥ የሚችለውን ልዩ መብት ወይም ጥቅም እኔ አደርግልሀለሁ በማለት ለሌላ ሰው ለማስገኘት ሲል ገንዘብ፣ ስጦታ፣ ሌላ ጥቅም የጠየቀ፣ የተቀበለ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ፤ በሙስና ይጠየቃል።
ሰጭዉም ቢሆን የህግ ተጠያቂነት አገልግሎቱ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ብቻ እንደሚሰጥ እያወቀ ልዩ መብት ወይም ጥቅም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ገንዘብ፣ ስጦታ፣ ሌላ ጥቅም የሰጠ፣ ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ይጠየቃል፣

### 1.1.4.22 በምርጫ ላይ የሚሰጥ መደለያ (አንቀጽ 30)

ማንኛውም ሰው የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለው ሌላ ሰው በመብቱ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀም ወይም መብቱን እነዲተው ለማድረግ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ገንዘብ ወይም በማናቸውም ሌላ አይነት ጥቅም የሰጠ፣ ወይም ለመስጠት ቃል የገባ እንደሆነ፣ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል።

### 1.1.4.23 ከባድ የእምነት ማጉደል (አንቀፅ 31)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር፣ ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ፣ የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ

ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ፤መዉሰዱ፣ ማስወሰዱ ወዘተ በህግ ግምት የሚጣል በመሆኑ ዐቃቤ ህግ ንብረቱ መጉደሉን እንጂ መዉሰድ ማስወሰዱን ማስረዳት አይጠበቅበትም፡፡

### 1.1.4.24 ከባድ አታላይነት (አንቀፅ 32)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣ የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለፅ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሌላውን ሰው ማታለል በህግ የሚያስቀጣ ነዉ፡፡

### 1.1.4.25 በሙስና ወንጀል የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና በወንጀሉ ስለመርዳት (አንቀጽ 33)

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል የተፈጸመው በሙስና ወንጀል አመንጪነት ከሆነ አግባብነት ያለው በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ህግ ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡

## 1.2 ክፍል ሁለት- የሥነምግባር አጠቃላይ ገጽታ



አስረጅ ናሙና

የአንድ ከተማ አስተዳደር በቅርቡ ያሰራው የመንገድ ዳር መብራት የጥራት ችግር ገጥሞታል፡፡ በዚህም ምክንያት በከተማው በምሽት የሚፈጸሙ ወንጀሎች እየተበራከቱ መጥተዋል፡፡ የከተማው ኗሪዎችም በተደጋጋሚ ችግሩን ለሚመለከታቸው የመንግስት አስፈጻሚ አካላት ቢያቀርቡም እኛ መፍትሔ እንፈልጋለን ከሚል ቃል ውጭ ተጨባጭ መፍትሄ ሳይበጅለት ስለቀረ ችግሩ ቅሬታውን በየደረጃው ላሉ ምክር ቤቶች ያቀርባሉ፡፡ አሁንም ግን ችግር ሳይፈታ እንደቀጠለ ነው፡፡

ከዚህ ሁኔታ በመነሳት

- በመንግስት አስፈጻሚ አካላት እና ምክር ቤት ወኪሎች የተጣሱ የሥነምግባር እሴቶች ምንድናቸው?
- የከተማው ኗሪዎች ምን ማድረግ አለባቸው?
- የዚህ አይነት የሥነምግባር ግድፈቶች እንዴት ሊቃለሉ ይችላሉ?

### 1. 2.1. የሥነምግባር ትርጉም

ሥነምግባር ብዙኃን ሁኔታዎችን የሚዳስስ ሰፊ ጽንሰ ሐሳብ ነው። ሥነምግባር በብዙ መንገድ ይገለጻል። ሥነምግባር የሰዎች ባሕሪ፣ አመለካከት፣ ተግባር፣ አሠራር፣ የኑሮና የሥራ ዘዬን ይገልፃል። ሥነምግባር ስሕተትንና መጥፎ የሆነውን ነገር በመተው ትክክለኛውን ወይም መልካሙን መርጠን እንድንከተል የሚያስተምረንና የሚመራን ፍልስፍናና አስተምህሮ ነው።

ሥነምግባር ማለት ጥሩ እና መጥፍ በጎ እና ክፉ ሃሳብ፣ ንግግርና ዴርጊትን የሚገሌጽ ሥርዓትን የያዘ ጽንሠ ሃሳብ ነው። የትክክለኛና ትክክለኛ ያሌሆነ ባሕርይ መለኪያ ነው። አንዴ ሃሳብ ወይም ድርጊት መልካም ወይም መጥፍ፣ ትክክል ወይም ስህተት፣ዋጋ ያለው ወይም ዋጋ የሌለው፣ ፍትሃዊ ወይም ኢ-ፍትሃዊ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚጠቅም መለኪያ ነው። ሥነ-ምግባር ትክለክኛ ሃሳብንና ድርጊትን ከስህተት ለይቶ ለማውጣት የሚረዳና የሰውን ባሕሪ የሚቀርጽ መመሪያ ሲሆን፣ የሰው ልጅ መጥፍ የሆኑ ምኞቶች እንዲያሸንፈትና ጠንቅረው እንዲይወጡ ለመቆጣጠር የሚረዳው የሥነልቦና ልጓም ነው። በአብዛኛው በተግባር የሚገለጽ እና የሰው ሌጅ እንደ እንስሳ ሣይሆን ሰብዓዊ ክብሩን ጠብቆ ውስጣዊ ፍላጎቱንም ተገቢ በሆነ ወቅትና ሥፍራ እንዲገልጽ ብልም እንዲያሚላ የሚያደርግ የሕይወት አቅጣጫን የሚያመለክት ነው።

ከስነ ምግባር ጋር በተዛምዶ የሚነሳው ጽንስ ሃሳብ ግብረ ገብ የሚለው ነው። ሁለቱ ሃሳቦች የሚቀራረቡ ቢመስሉም የሚያለያበት ነገርም አለ። ይኸውም ግብረገብ ወይም ሞራል በሥነምግባር የሚፈተሽ፣ የሚመረመር፣ የሚገመገም፣ የሚያጠና (Object of the Study) ሲሆን ሥነምግባር /Ethics/ ግን ግብረገባዊ እሴትን (moral value) የሚፈትሽ፣ የሚመረምር፣ የሚገመግም፣ የሚያጠና የጥናት ዘርፍ /Field of study/ ነዉ። በአጭሩ ሥነምግባር ግብረገብን የሚያጠና ሳይንስ ነው።

እንደ ጠና ደዎ (2009፡23) አገላለጽ ግብረገብ የሰው ድርጊት ወይም ጠባይ ሰናይ ወይም እኩይ፣ ትክክል ወይም ስህተት ከማለትም ባለፈ መደረግ ያለባቸውን እና የሌለባቸውን ድርጊቶች፤ ሰው ሊኖረው የሚገባ እና የማይገባ ጠባይን ለይቶ የሚደነግግ ማህበራዊ እሴት ነው።

ሥነምግባር በበኩሉ ትክክል እና ስህተት፣ ሰናይ እና እኩይ ስለሆኑት የሰው ልጅ ድርጊቶች እና ጠባዮች መልካምነት እና መጥፍነት የሚፈትሽ ብቻ ሳይሆን መሆን የሚገባቸውን እና የማይገባቸውን የሚያመለክት ነው። ማንኛውንም ግብረገባዊ ጽንሰ ሀሳብ ምክንያታዊ በሆነ መንገድ በመተንተንና በማደራጀት የሰዎች ግብረገባዊ ግንዛቤ እንዲዳብር ያደርጋል።

ሥነምግባር ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በአሁኑ ዘመን የላቀ ትኩረት ተሰጥቶት ይገኛል። ሥነምግባር ለሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል አስፈላጊ ቢሆንም፣ በተለይ በመንግሥት አሠራር

ወይም አስተዳደር ውስጥ ጉልሕ ስፍራ አለው:: ሥነምግባር ለኀበረተሰብ ቅን አገልግሎት በመስጠት ሂደት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው ነው::

### 1.2.2. የሥነምግባር ደንብ ምንነት

**ተግባር መወያያ ጥያቄዎች**

| |
|---|
| አንድ የፓርላማ አባል ከተመረጡበት ጊዜ ጀምሮ ያላቸው ባህሪ እና ስነ ምግባር እተቀየረ መጥቷል:: ከተመረጡበት አካባቢ የመንግስት ሃላፊዎች ጋርም "አልከሰስም" በሚል መንፈስ ገፍተው በያዙት መሬት የተነሳ እሰጥአገባ ውስጥ ገብተዋል:: |

ከዚህ በመነሳት

i. ባላችሁበት ሥራና ኃላፊነት ደረጃ ሊከበሩ የሚገቡ የሥነምግባር እሴቶችን ዘርዝሩ::
ii. ከሥራና ከኃላፊነታችሁ አኳያ በተቋማችሁ በነዚህ የሥነምግባር እሴቶች ዙሪያ የሚስተዋሉ መልካም ተመክሮዎችንና ክፍተቶችን አብራሩ::
iii. ከተቋማችሁ አኳያ የሥነምግባር ደንብ ያለውን ጥቅሞችና ፋይዳ አስረዱ::

የሥነምግባር ደንብ ሙስናና ብልሹ አሠራርን በመከላከል ረገድ የላቀ ፋይዳ አለው:: በይበልጥ በመንግሥት ተቋማት የሥነምግባር መርሆዎች መኖር ተቋማት የሚሰጧቸውን አገልግሎት ደረጃ ለመጠበቅ ያለው አስተዋፅኦ የላቀ ነው:: በተለይ እንደ ፓርላማ ባሉ ተቋማት እጅግ አስፈላጊ በመሆናቸው አባላት ሊያከብሯቸው የሚገቡ የሥነምግባር እሴቶችን ያካተተ የሥነምግባር ደንብ መቅርፅና ተግባራዊ ማድረግ የተለመደ ተግባር ነው:: የሥነምግባር እሴቶቹ ቁጥር ወይም ይዘት እንደ የሀገራት ነባራዊ ሁኔታና ፍላጎት የሚለያይና የሚወሰን ነው::

የሥነምግባር ደንብ መዘጋጀቱ ብቻውን በቂ አይደለም:: የፓርላማ አባላት ስለ ሥነምግባር ደንቦቹ በጥልቀት እንዲያውቁና የቀን ተቀን የሥራ መመሪያቸው እንዲያደርጉት መደረግ አለበት:: የሥነምግባር ደንቦቹ ሲጣሱ ደግሞ ሕጋዊ ብሎም አስተማሪ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል::

በዚህ ረገድ በሀገራችን ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ የሠራተኞች የሥነምግባር መርሆዎች እንደ አጠቃላይ በተለይ ደግሞ የምክር ቤት አባላት የስነ ምግበር እና ስነ ስርዓት ደንብ በሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ጸድቆ ተግባራዊ በመሆን ላይ ነው:: የሰራተኞች የሥነምግባር ደንብ አስራ ሁለት እሴቶችን ያካተተ ነው:: ከነዚህ መካከል ቅንነት/የተሟላ ስብዕና፣ ታማኝነት፣ ግልጽነት፣ ምሥጢር መጠበቅ፣ ሐቀኝነት፣ ተጠያቂነት ይጠቀሳሉ::

ምንም እንኳ ይህ የሰራተኞች ስነ ምግባር ደንብ ምን ያክል ለውጥ አምጥቷል የሚለው ጥናት የሚፈልግ ጉዳይ ቢሆንም ከእለት ተዕለት ተሞክሮ በመነሳት እንደ ሃገር የሰራተኞች ስነምግባር እየተሻሻለ ነው ብሎ መናገር አይቻልም፡፡

በተመሳሳይ የምክር ቤት አባላት የስነ ምግበር እና ስነ ስርዓት ደንብ በስራ ላይ መዋል ከጀመረ የሰነበተ ቢሆንም አንዳንድ የስነ ምግበር ጥሰቶች መስተዋላቸው እነደቀጠለ ነው፡፡

### 1.2.3. ሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ

**አስረጅ ናሙና**

| |
|---|
| በአንድ ወቅት የአንድ ሀገር መሪ ያቀረቡትን ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ግዢ የብድር ጥያቄ ፓርላማው አጸደቀ፡፡ ለጥያቄው በወቅቱ የቀረበው ምክንያት የሀገር ደህንነት አደጋ ላይ ነው የሚል መረጃ ነበር፡፡ ከጊዜ በኂላ ከተፎካከሪ ፓርቲ የገቡት ጦር መሳሪዎች ጊዜ ያለፈባቸውን እና በቁጥርም አነስተኛ ናቸው የሚል ቅሬታ መሰንዘር ተጀመረ፡፡ ለቅሬታው የሀገሪቱ መሪ ጽ/ቤት ውሳኔውን ያስተላለፈው ፓርላማው ነው የሚል መልስ ሰጠ፡፡ |

በዚህ ሁኔታ ፡-

i. ሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ምን መልክ ነበረው? ምንስ የጎደለው ነገር ነበር?
ii. ሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ሲባል ምን ትረዳላችሁ?

አወዛጋቢ እና አከራካሪ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ውሳኔዎች በምን ላይ መመሠረት አለባቸው? ለሚሰጡ ውሳኔዎች መመዘኛቸው ምን መሆን አለበት? በውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ ሥነምግባር ያለው ፋይዳ ምንድንነው?

ሰዎች ዕለት በዕለት የሕይወት ኑሯቸው ውስጥ በተለያዩ ጉዳዩች ላይ ውሳኔ ይሰጣሉ፡፡ ሕይወት በድርጊትና በውሳኔ የተሞላ ነው፡፡ አንዳንድ ውሳኔዎች በጣም ቀላልና ጊዜ የማይፈልጉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አንዳንድ ጉዳዮች ውስብስብ፣ ጥንቃቄ፣ መመካከር እና ጊዜ የሚጠይቁናቸው፡፡

በይበልጥ በከፍተኛ ኃላፊነት፣ የመንግሥትና የተቋማት ደረጃ የሚወሰኑ አንዳንድ ውሳኔዎች ልዩ ጥንቃቄ ይፈልጋሉ፡፡ በአብዛኛው በፓርላማ፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች እና በሲቪክ ማኅበረሰብ መሪዎችም የሚወሰኑ ውሳኔዎች ያላቸው አንደምታ ከፍተኛ ነው፡፡ የሚወሰኑ ውሳኔዎች ለሶስት ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጡ መሆን አለባቸው፡፡ እነዚህም ውሳኔው ሕጋዊ ነው ወይ? ወይም የሕግ መሠረት አለው ወይ? ሥነምግባራዊ ነው ወይ? በመጨረሻም ሙያዊ ነው ወይ? የሚሉት ናቸው፡፡ ከነዚህ የውሳኔ አሰጣጥ መስፈርቶች በተጨማሪ የሚከተሉትን የግብረገባዊ ውሳኔ አሰጣጥ መርሖዎችን ማገናዘብ ጠቃሚ ነው፡፡

☞ **የጠቀሜታዊነት ውሳኔ አሰጣጥ** (Utilitarian decision making approach):-በዚህ አቀራረብ መሠረት ውሳኔ የሚሰጠው ከፍተኛ ጥቅም የሚያስገኘውን ወይም ዝቅተኛ ጉዳት የሚያስከትለውን መሠረት በማድረግ ነው፡፡

☞ **በትክክለኛነት ላይ ያተኮረ የውሳኔ አሰጣጥ** (The Right decision making Approach):- የሰው ልጆች የማንም ተጽእኖ ሳይኖርባቸው "በነፃነት የመምረጥ መብት አላቸው" የሚለውን መርሕ መሠረት ያደረገ ነው፡፡

☞ **ሚዛናዊ ወይም ፍትሐዊ ውሳኔ አሰጣጥ** (The Fairness or Justice decision making Approach):- ክብርን፣ግብረገባዊ መብት እና እኩልነትን በሚያንጸባርቁ ድርጊቶች፤ ሂደቶችና ውጤቶች ላይ ያተኩራል፡፡ በይዘቱ የፍትሐዊነት እሴት በሌሎች ላይ ለውጥ የሚያመጣ ውሳኔን ለመስጠት የሚያስችል ግብረገባዊ መለኪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡

☞ **የጋራ መልካምነት ላይ ትኩረት ያደረገ የውሳኔ አሰጣጥ** (The Common - Good decision making Approach):- የትኛው አካሄድ ነው የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያራምደው የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ይረዳል፡፡ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ቡድኖች ምን ግብረገባዊ መብት አላቸው፤ እና የትኞቹ አካሄዶች እነዚህን መብቶች በትክክል ይወክላሉ በሚሉት ላይ ያነጣጥራል፡፡

☞ **ሰናይ ምግባር ላይ ያተኮረ የውሳኔ አሰጣጥ** (Virtues decision making Approach):- እያንዳንዳችን የምንፈልጋቸው ውስጣዊ እሴቶችና ግብረገባዊ ማንነቶች አለን፡፡ እያንዳንዳችን የተሻለ ግብረገባዊ ማንነቶችና እሴቶችን ለማግኘት ጥረት ማድረግን ያመለክታል፡፡

## የምእራፍ ማጠቃለያ

በዚህ ምእራፍ ውስጥ ሙስና ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ አንድ ወጥ የሆነ ዓለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት እንደማይቻል ተመልክተናል፡፡ በተጨማሪም የሙስና ወንጀል መገለጫ ጉቦ ብቻ እንዳልሆም መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚህ አኳያ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉትን 25 የሙስና ወንጀሎችን ለማየት ተችሏል፡፡ በዚህ ምእራፍ ውስጥ የቀረቡት የሙስና ወንጀሎች ትርጓሜ ናቸው፡፡ የወንጀሎቹን ዝርዝር ጉዳይና የሚጣለውን መቀጮ በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 881/2007ን ተጨማሪ ንባብ እንዲያደርጉ ይጠበቃል፡፡

በምዕራፉ ክፍል ሁለት ደግሞ ሥነምግባር ሙስናና ብልሹ አሠራርን በመከላከል ረገድ ያለውን የላቀ ሚና ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ በዚህም የሥነምግባር ጽንሰሐሳብ፣ የሥነምግባር አስፈላጊነት፣ የሙያ ሥነምግባር ምንነትና አስፈላጊነት የሚሉ ፍሬ ነጥቦች ተዳሰዋል፡፡

ሥነምግባር ግንባታን ለማረጋገጥ የሥነምግባር ደንብ መቅረጽና ግንዛቤውን በሰራተኞች ዘንድ ማስረጽ የጎላ ፋይዳ አለው፡፡ በዚሁ ረገድ ማንኛውም ተቋም ደንቡን ማዘጋጀት እንደሚገባው ተገልጿል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ውሳኔ ሲሰጥ የተለያዩ የሥነምግባር መርሖዎችን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡ የውሳኔ አሰጣጥ መርሖዎቹም ሕጋዊ፣ ሥነምገባራዊ እና ሙያዊ የሚሉት ናቸው፡፡ በቡድን ውይይት እና በተመክሮ ጽብረቃ ደረጃ የተዘጋጀው ዝግጅት የሠልጣኞችን ዕውቀትና ተመክሮ የሚያዳብር መሆኑ ይታመናል፡፡

## የምእራፍ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**ከዚህ በታች የቀረቡት ጥያቄዎች አሠልጣኞችሁ በሚሰጧችሁ ማብራሪያ መሠረት ምላሽ ስጡባቸው፡፡**

i. “ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት” በዘርፋችሁ እንዴት እንደሚስተዋሉ፤ የሚያስከትሉትን ጉዳት ተወያይታችሁ ለተሳታፊዎች አቅርቡ፤

ii. በዘርፉ ተዘወትረው የሚታዩት የሙስና ወንጀል ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው? ምክንያታችሁን አስረዱ፡፡

iii. “ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ወንጀል” ን ለመከላከል የሃብት ምዝገባ እንዴት ሊከላከል እንደሚችል አስረዱ፡፡

iv. ስለሃገር በሚል የአንድ ቴለቪዥን ፕሮግራም ላይ በተዘጋጀ የሚዲያ ውይይት መድረክ በታወቁ ጋዜጠኞች መካከል የጋለ ክርክር ይደረግ ነበር፡፡ የክርክሩ ዋና ሐሳብ የመንግሥታት ትኩረት ምን መሆን አለበት የሚል ነበር፡፡ በዚህ ክርክርና ውይይት የአንዱ ጋዜጠኛ ሐሳብ የብዙዎቹን ተሳታፊዎችን አሳመነ፡፡ የዚህ ጋዜጠኛዋና ሐሳብ እና ትንታኔ የሀገራት መሪዎች ቀዳሚ ትኩረት ስነምግባር መገንጋት መሆን አለበት የሚል ነበር፡፡ ካላችሁ ግንዛቤ በመነሳት በዘመናችን የሥነምግባር መጓደል እያስከተል ባለው ዋና ዋና ጉዳቶች ዙርያ ተወያዩ?

v. በአብዛኛው የአፍሪካ ሀገራት ስጦታና ጉርሻ መስጠት ባህል ነው፡፡ ለንግድና ኢንቨስትመንትን ለማሳለጥ ብሎም ሀገራትን በኢኮኖሚ ለማሳደግ ጠቃሚ መሣሪያ እንጅ የስነ ምግባር መጓደል ማሳያ አይደለም የሚሉ አሉ፡፡ ሌሎች ይህን ሐሳብ አጥብቀው ይቃወማሉ፡፡ በየትኛው ሐሳብ ትስማማላችሁ? ለምን? ምክንያታችሁን ዘርዝሩ፡፡

vi. አንዳንድ አካላት የስነ መግባር መጓደል መንስኤ የውጭ ባህል በሃገራችን በመስፋፋቱ ነው ብለው ይከራከራሉ፡፡ ስለዚህ የሃገራችንን ባህል መጠበቅ የባህል ወራራን ለመከላከል ዓይነተኛ ቅድመ ሁኔታ እንደሆነ ይመክራሉ፤ ሌሎች ደግሞ የእምነት

ተቋማት መዳከም ነው ይላሉ፤ የሕግ ቅጣት መላላትና የተጠያቂነት ሥርዓት መድከም ነው የሚሉም አሉ፡፡ ከዚህ ሐሳብ በመነሳት፡- ከላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች

- ✓ በየትኛው ሐሳብ ትስማማላችሁ? ለምን? በምሳሌ አብራሩ፡፡
- ✓ ሌሎች ምክንያቶች ካሉ በምሳሌ በማስደገፍ አብራሩ፡፡
- ✓ ከሀገራችንና ከተቋማችሁ አኳያ፣ ለስነ ምግባር መጓደል መሠረታዊ መንስዔ ናቸው የምትሏቸውን ጉዳዮች በምሳሌ በማስደገፍ አብራሩ፡፡

vii. "የሥነምግባር አውታር" (Ethics infrastructure) በሚል ከታች በሳጥን ውስጥ የተዘረዘሩት ሐሳቦች ሀገራት ሙስናን በመከላከል ተግባራዊ እንዲደርጉ (OECD) ምክርና ድጋፍ ይለግሳል፡፡ በሀገራችንና በተቋማት ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ሙስናን ለመከላከል ቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቷቸው ተግባራዊ ቢደረጉ የምትሏቸውን ጉዳዮች በደረጃ አስቀምጡ

| ዋና ዋና ጉዳዮች | ደረጃ |
|---|---|
| ጠንካራ ሕግ (Effective legal frame work) | |
| ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ ሥርኣት መዘርጋት (Effective acountability mechanism) | |
| ተግባራዊ የሥነምግባር ደንብ (Workable code of conduct) | |
| ሙያዊነትን ማኅበራዊ ማድረግ (Professional socialization) | |
| ምቹ የሥራ ሁኔታ መፍጠር (Supportive public service condition) | |
| የሥነምግባር መከታተያ ክፍል (Ethics Coordination body) | |
| ጠንካራ ሲቪል ማኅበረሰብ (Active civic society) | |

viii. **አንዳንድ ሰዎች የዓለምና የሀገራችንም** የሥነምግባር ደረጃ በከፍተኛ ችግር ላይ ወድቋል ብለው ያምናሉ፡፡ የሥነምግባር ደረጃውን ከፍ ለማድረግ ተሰሚነት ያላቸው ሰዎች ያላቸውን ሚና ‹‹Great people have great values and great ethics››የሚለውን የ"Jeffrey Gitomer" አባባል በማብራራት አመልክቱ፡፡

## ምእራፍ ሁለት

## የምክር ቤት ዘርፍ የሙስና ስጋት ተጋላጭነት እና የመከላከያ ስልቶች

### መግቢያ

የፓርላማ ስርዓት በብዙ የአለማችን ሃገራት ውስጥ የሚተገበርና ዜጎችን በሚወክሉ ተወካዮች በተደራጁ ምክር ቤቶች አማካኝነት ቀጥተኛ ባለሆነ መንገድ ዲሞክራሲን የሚተገበሩበት የፓለቲካ ስርዓት አይነት ነው፡፡ ሙስናን በመከላከል ረገድ ፓርላማዎች የሚጫወቱት ሚና ከፍ ያለ እንደሆኑ ሁሉ በእነሱ የአሰራር ሂደት ማለትም ህግ በማውጣት፣ በክትትልና ቁጥጥር፣ በውክልና ስራቸው ውስጥ ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ ስጋቶች እና በተግበር የሚፈጸሙ የሙስና አይነቶችም አሉ፡፡

በዚህ ምዕራፍ በምክርቤት ዘርፍ የሙስና ተጋላጭነት ስጋቶች እና ሊፈጸሙ የሚችሉ የሙስና አይነቶች ይቀርባሉ፡፡ የሚሸፈኑ ዝርዝር ሐሳቦችም፣ የፓርላማ ስርዓት ምንነት፣ የፓርላማ ስርዓት ሙስና ለመከላከል ያለው አቅም ፣ የፓርላማ ዋና ዋና የሙስና ተጋላጭነት ስጋቶች እና በዘርፉ ሊፈጸሙ የሚችሉ የሙስና አይነቶች የሚሉት ናቸው፡፡

ሙስና ብዙ ዘርፎችን የሚዳስስ፣ መፈጸሚያ መንገዱም በየጊዜው እየተለዋወጠና እየረቀቀ የሚሄድ ወንጀል ነው፡፡ ለመከሰቱ ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮችም እንዲሁ በርካታ ናቸው፡፡ ታዲያ ይህን ተለዋጭ ባህሪ ያለውን ሙስና ለመዋጋት ዘርፎች እንደየተቋማቸው ባህርይ

በየጊዜው የሚሻሻል፣ መጠነ ሰፊ ጉዳዮችን የሚዳስስ የሙስና መከላከልያ ስትራቴጂዎችን መንደፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሙስናን የመከላከል ተግባር ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የችግሩን ምንጭ የማድረቅ ተግባር ነው፡፡ ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመከላከል በሙስናና ብልሹ አሰራር ምክንያት ይባክን የነበረውን ሃብት በመታደግ ያለውን  ሃገራዊ ሃብት ለታለመለት ሥራ ለማዋል ያስችላል፡፡

ችግሩ ከተከሰተ በኋላ የችግሩን ፈጣሪ እና የባከነውን ሃብት ለማፈላለግና ለማግኘት የሚባክነውን ተጨማሪ ወጪ ያስቀራል፤ በመንግስት ተቋማት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ክፍተት የማይፈጥር ጠንካራ የአሰራር ሥርዓት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ በዚህ ምእራፍ ክፍል ሁለት ውስጥ በዘርፉ ውስጥ ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችሉ ስልቶች ይዳሰሳሉ፡፡

**ዓላማ**

- የፓርላም ስርዓት ምንነትን ይገልጻሉ
- የፓርላማ ስርአት ሙስና ለመከላከል ያለውን አቅም ይተነትናሉ
- በተቋማቸው ጎላ ብለው የሚታዩ ዋና ዋና የሙስና ስጋት ዓይነቶችን ይለያሉ
- በተቋማቸው ሊፈጸሙ የሚችሉ የሙስና ዓይነቶችን ይዘረዝራሉ
- የሙስና መከላከያ ስልቶችን ይተነትናሉ፣
- የሙስና መከላከያ ስልቶችን ያወዳድራሉ፣

**የሚወስደው ጊዜ- 6፡00 ሰዓት**

## 2.1 ክፍል አንድ- የምክር ቤት ዘርፍ የሙስና ስጋት ተጋላጭነት እና የሙስና አይነቶች

### 2.1.1 የፓርላማ ሥርዓት ምንነት

**ማነቃቂያ ጥያቄዎች**

| |
|---|
| የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ሥርዓት ባይኖር ኖሮ መንግሥታት እንደ መንግሥት መቆም አይችሉም ነበር፡፡ ዘመናዊ ሥልጣኔና ዴሞክራሲ ሥርዓት እያደገ የመጣው የተወካዮች ምክርቤት አደረጃጀት እየተስፋፋ በመሄዱ ነው የሚሉ አካላት አሉ፡፡ |

የዘመናዊ መንግሥት አስተዳደር ከመመስረቱ በፊት የቀድሞ ነገሥታትና የሀገር መሪዎች የተለያዩ ዓዋጆችን ሲያውጁ ኖረዋል፡፡ እነዚህኑ አዋጆችም ይፈፅሙና ያስፈፅማሉ፡፡ የዳኝነት ሥራን ያከናውኑ ነበር፡፡ ይህ ማለት ነገሥታቱ ሁሉም ሥልጣን፤ ሕግ የማውጣቱን፣ የወጡትንም ሕግ የማስፈጸሙ እና ዳኝነትን ወይም ፍርድ የመስጠት ተግባራትን ጠቅልለው በእጃቸው ውስጥ ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ የሀገር ሀብትና ነገሥታት ሀብት ተለያይቶ ካለመቀመጡም በላይ በነገሥታት፣ በቤተሰቦቻቸውና ለመሳፍንቶች መጠቀሚያ ብቻ የሚውል ነበር፡፡ ይህ ዓይነት አስተዳደር በሰው ልጅ ታሪክ ረጅም ዘመን የቆየና በበርካታ ሀገራት የነበረ ሥርዓት ነው፡፡

ዘመናዊ የመንግሥት አስተዳደር ቀስ በቀስ ከተስፋፋበት ጊዜ ጀምሮ በተለይ ከ200 ዓመት ወዲህ መንግሥት ሦስት ዋና ዋና አካላትን የያዘ አወቃቀር መሠረት በማድረግ መደራጀት ጀመረ፡፡ እነዚህም የሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈጻሚ እና ሕግ ተርጓሚ የሚባሉት ናቸው፡፡ የሀገርን ሕግ የሚያወጣው ሕግ አውጪ አካሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ወይም ፓርላማ ተብሎ ይጠራል፡፡

ዘመናዊ የፓርላማ አሠራር በእንግሊዝ ሀገር በ13ኛው ክፍለ ዘመን በንጉሥ ቀዳማዊ ኤድዋርድ ዘመን እንደ ተጀመረ ይታወቃል፡፡ በወቅቱ ፓርላማው በንጉሣዊ አገዛዝ ቁጥጥር ስር በመሆኑ ምክንያት የሀገርን ሀብት ከብክነት የመታደግ ሚናው ዝቅተኛ ነበር፡፡

በአሁኑ ወቅት በአብዛኛው የዓለም ሀገራት የፖለቲካ፣ የአስተዳደር፣ የመንግሥት መዋቅር ማዕከል ሆኖ ይወሰዳል፡፡ በእንግሊዝ የተጀመረው ፓርላማ፣ ዛሬ ከ190 በላይ በሆኑ ሀገራት ዐብይ የፓለቲካ አስተዳደር አደረጃጀት ሥርዓት ሆኖ ይስተዋላል፡፡ የፓርላማ አወቃቀር እና ስያሜው እንደየሃገሩ ሁኔታ የተለያየ ነው፡፡ በእንግሊዝ ፓርሊያሜንት፣ በአሜሪካ ኮንግረስ፣ በጃፓን ዳይት፣ በቻይና የሕዝብ ብሔር ኮንግረስ፣ በራሽያ ዱማ፣ በጀርመን ቡንድስታግ፤ በእስራኤል ክኔትስ እና በሀገራችን ምክርቤት በሚል ይጠራል፡፡

ለፓርላማ መመሥረት መነሻ ሰነድ ሕገመንግሥት ሲሆን፣ እንደየሀገሩ ሁኔታ ባለአንድ ቤት ወይም ባለሁለት ቤት ፓርላማ በማቋቋም በስራ ላይ ይውላል፡፡ በአብዛኛው በሕዝብ ቁጥራቸው አነስተኛ በሆኑ ሀገራት ባለአንድ ቤት ፓርላማዎች ይደራጃል፡፡

ወደ ሃገራችን ስንመጣ የፓርላማ አወቃቀር የተጀመረው በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ነው፡፡ በ1923 ዓ.ም የወጣውን የጽሑፍ ሕገመንግሥት አንዱ ውጤት ፓርላማ ማቋቋሙና ስራ ላይ ማዋሉ ነው፡፡ ይህ ፓርላማ ባለሁለት ቤት ነበር፡፡ የፓርላማዎቹ ስያሜ የሕግ መወሰኛ ምክርቤት (የላይኛው ምክርቤት) እና የሕግ መምሪያ (የታችኛው ምክርቤት) የሚል ነበር፡፡ የመጀመሪያው የፓርላማ ስብሰባ በ1924 ዓ.ም የተካሄደ ነበር፡፡ በሀገራችንም

የመጀመሪያው የዘመናዊ ፓርላማ አወቃቀር መሠረት የጣለው ፓርላማ ንጉሰነገስቱን ከማማከር ውጪ ሚና አልነበረውም፡፡ የሚወሰኑ ውሳኔዎች ወይም ሕጎች በንጉሱ እውቅና፣ ተቀባይነት እና መጨረሻም መጽደቅ አለባቸው፡፡ ከዚህ የተነሳ ፓርላማው እንደ ምክርቤት የሚጠበቅበትን ኃላፊነት እየተወጣ አልነበረም፡፡

በደርግ አገዛዝ ዘመን ሸንጎ የሚል ሁለተኛው የፓርላማ መሰል ተቋም በ1979 ዓ.ም ተደራጀ፡፡ የሚፈለገውን ያህል እንቅስቃሴ ሳያደርግ ሸንጎው በ1983 ዓ.ም ተበተነ፡፡ በ1983 ዓ.ም የሽግግር መንግሥት ምክር-ቤት ለአራት ዓመታት በሥልጣን ላይ ቆየ፡፡ 1987 ዓ.ም በፀደቀው ሕገመንግሥት መሠረት በፌደራል እና በክልሎች አሁን በስራ ላይ ያሉት ምክርቤቶች ወይም ፓርላማዎች ተቋቋሙ፡፡ በዚህ ደረጃ ከቋቋሙት ምክርቤቶች በተጨማሪ እስከታችኛው የመንግሥት አስተዳደር እርከን ደረጃ ተደራጅተው ይገኛሉ፡፡

በማንኛውም ሀገር የሚዋቀር የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ወይም ፓርላማ ሥልጣንና ተግባር እንደዚሁም የምክርቤት አባላት ቁጥር በሕገመንግሥት ውስጥ ተዘርዝሮ ይቀመጣል፡፡

በሀገራችን በፌደራል ደረጃ የተዋቀረው የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ሥልጣንና ተግባር በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት (1987 ዓ.ም) አንቀጽ 55 የተደነገገ ሲሆን ከነሱ መካከል የሚከተሉት በምሳሌነት ተጠቅሰዋል፡-

- ህጎችን ያወጣል
- የፌደራል መንግስት በጀት ያጸድቃል፡፡
- የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋምን ያቋቋማል፣ተቋሙን የሚመሩ አባላትን ይሰይማል፣ ስልጣንና ተግባሩን በህግ ይወስናል፡፡
- ምክር ቤቱ ጠቅላይ ሚኒስቴሩን እና ሌሎች የፌደራል መንግስት ባለስልጣናትን ለጥያቄ የመጥራትና የህግ አስፈጻሚው አካል አሰራር የመመርመር ስልጣን አለው፡፡
- ለህግ አስፈጻሚው አካል በተሰጠ ማንኛውም ስልጣን ላይ የምክር ቤቱ አባላት በአንድ ሶስተኛ ድምጽ ሲጠየቅ ምክር ቤቱ ይወያያል፡፡ ምክር ቤቱ በጉዳዩ ላይ የመመካከርና አስፈላጊ መስሎ የታየውን እርምጃ የመውሰድ ስልጣን አለው፡፡
- ምክር ቤቱን የሚመሩ አፈ ጉባኤና ምክትል አፈ ጉባኤ ይመርጣል፣ለምክር ቤቱ ስራ የሚያስፈልጉትን ቋሚና ጊዚያዊ ኮሚቴዎች ያዋቅራል፡፡

በተጨማሪ ለምክርቤቱ እና ምክርቤት አባላት ሙያዊ ድጋፍና አገልግሎት የሚሰጥ እና የእለት ከዕለት ስራዎችና ተግባራት የሚያከናውን ፅ/ቤት አለ፡፡

## 2.1. 2 የፓርላማ ስርአትና ሙስና መከላከል

### ማነቃቂያ ጥያቄ

| |
|---|
| የፓርላማ ስርዓት ከሌሎች የፓለቲካ ስርዓቶች በተለየ ሙስናን ለመከላከል ምን የተሻለ አቅም አለው ብላችሁ ታስባላችሁ? |

ሙስናን ከመከላከል ረገድ ም/ቤቶች ከሚሰሩበት የፖለቲካ ስርዓት አንጻር የተለያየ ሚና፣ መሳርያ እና አጠቃቀም መንገድ ሊኖራቸው እንደሚችል መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በዚህ ረገድ ሶስት የተለያዩ አማራጮን መመልከት እንችላለን እነርሱም የዌስት ሚኒስቴር፣ ኮነግሬሽናል እና የቅይጥ ስርዓት ናቸው፡፡

የዌስት ሚኒስቴር ስርዓት መለያ ባህሪ የስራ አስፈጻሚው ከም/ቤቱ በም/ቤቱ የሚመረጥና ለመቆየትም የምክርቤቱን መተማመኛ የግድ የሚፈልግ መሆኑ ነው፡፡ ይህም ሚኒስቴሮች የምክር ቤቱ አባል እንዲሆኑ ስለሚያስችል ተጠያቂነትን ከማረጋገጥ አንጻር የተሻለ እድል የሚፈጥር ያድረገዋል፡፡ ይህንን ለመተግበርም የመጠየቅ፣ በየጊዜው የመተማመኛ ድምጽ ሃሳብ ላይ ምርጫ የማድረግ እንዲሁም የኮሚቴ ግምገማን እንደ መሳርያ ይጠቀማል፡፡

የመጠየቅ መሳርያ እጅግ አዋጭ የሚሆነው በግል ለተወከሉ የመንግስትን የፋይናንስ አስተዳደር፣ አሰባሰብ እና ለአባላት የሚቀርቡ ቅሬታዎች ዙርያ ጥያቄ ለሚያነሱ  አባላት ነው፡፡ ይህ በተለይ ውጤታማ የሚሆነው ጉልበት ያለው እና ነጻ ሚድያ ካለ በአስፈጻሚው ላይ ተጨማሪ ግፊት በማድረግ ውጤታማ የታማኝነት ሰርዓት እንዲዘረጋና በባልስጣናት የተፈጸሙ ስህተቶችን እንዲታረሙ ያስችላል፡፡

የመተማመኛ ድምጽ መንሳትን ስንመለከት ደግሞ በዌስት ሚኒስቴር ስርዓት ውስጥ ፓርላማው ስራ አስፈጻሚውን የሚቆጣጠርበት የመጨረሻ መሳርያ ሲሆን በአብላጫ ድምጽ ሲጸድቅ  ም/ቤቱ ስራ አስፈጻሚውን በየትኛውም ጊዜ ለማሸነፍ ያስችለዋል፡፡

ወደ ኮሚቴ ግምገማን ስንመጣ በተሰጣቸው ከፍትኛ የመመርመር ስልጣን ማለትም ምስክር እንዲቀርብ የማድረግ እንዲሁም መረጃ እንዲቀርብ በመጠየቅ ስራ አስፈጻሚውን መቆጣጥር ይችላሉ፡፡በተለይ ደግሞ በጠንካራ የውስጥ ባለሙያና ኦዲተር መስያ ቤቶች ከተደገፉ የስራ አስፈጻሚውን ያልተገባ ባሕሪ እና አሰራር የሚያሰውግድ እና እርምት እርምጃ እንዲወስድ የሚያደርግ መሳርያ ነው፡፡

የኮንግሬሽናል ስርዓትን ስንመለከት ከዌስትሚኒስቴር የሚለየው ዋናው ባህሪ የህግ አውጭው እና አስፈጻሚው በቀጥታ በህዝብ ምርጫ የሚመረጡ መሆናቸው ነው፡፡ በዚህ የመንግስት ስርዓት የህግ አውጭው እና አስፈጻሚው መካከል የስልጣን ክፍፍል እና ምጥጥን ይኖራል፡፡

ስለሆነም ስልጣን በአንድ የመንግስት ቅርንጫፍ የመጠቅለል እድሉ አነስተኛ ነው፡፡ ይህም በስልጣን መከማቸት የተነሳ ሊፈጠር የሚችለውን የሙስና ስጋት ይቀንሳል፡፡ በተለይም በተለያየ የውክልና ህግ የተመረጡ ሁለት ም/ቤቶች በሚኖሩበት ጊዜ የስልጣን ክምችትን ይበልጥ የመቀነስ እድሉ ይሰፋል፡፡ በተመሳሳይ ህግ አውጭው ስራ አስፈጻሚውን የመለወጥ እድሉ አነስተኛ ነው፡፡

በኮንግሬሽናል ስርዓት የም/ቤት የመጠየቅ ሚናን ስናይ እንደ ዌስትሚኒስቴር ስርአት አስፈጻሚውን ቶሎ ቶሎ የመጥራትና የመጠየቅ እድሉ አነስተኛ ነው፡፡ይህም ስህተቶችን ለማጋለጥ እና ተጠያቂነትን የማስፈን አቅሙን ይቀንሰዋል፡፡

ሶስተኛው አይነት የፓለቲካ አወቃቀር ቅይጥ የምንለው ሲሆን ከላይ የተዘረዘሩትን የሁለቱን በተለያየ መንገድ የሚያነጸባርቁ ስርዓቶችን የሚያጠቃልል ነው፡፡ ምንም እንኳ ካለው ባህሪ አንጻር ከዲሞክራሲያዊ ተጠያቂነትና እና ሙስና ተጋላጭነት በተያያዘ ያለውን አዝማሚያ ማስቀመጥ አዳጋች ቢሆንም እንደ አንድ የፓለቲካ እና ተቋማዊ አማራጭ መቅረቡ ም/ቤቶች ያላቸውን የተለያየ አማራጭ ለማሳየት ይረዳል፡፡

በማንኛውም ሀገር የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ወይም ፓርላማ የሚዋቀረው ሕዝብ በቀጥታ በመረጣቸው ወኪሎች አማካኝነት ነው፡፡ ፓርላማ የመንግሥታት አንዱ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ነው፡፡ ሕጎችን ያውጣል፣ ያሻሽላል፣ ያጸድቃል፡፡ የመንግሥት በጀት የማጽደቅና የመደልደል ሚና ይጫወታል፡፡ የአስፈጻሚው አካልን ተግባርና አፈጻጸም የመመልከት፣ የመከታተል፣ የመቆጣጠር፣ የመመርመር እና የመደገፍ ኃላፊነትም አለበት፡፡ የዜጎችን መብት እና ጥቅም የማስጠበቅ ሚናም ሌላው ተግባሩ ነው፡፡

ይሁን እንጅ ፓርላማዎች በህዝብ ዘንድ ያላቸው መታመን የዳበረ ዲሞክረሲ አላቸው በሚባሉ ሀገራት ሳይቀር እያሽቆለቆለ እንደመጣ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ተደጋጋሚ የሙስና ቅሌቶች በዴሞክራሲያዊ ተቋማት ላይ ያለው እምነት ዝቅተኛ እንዲሆን አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ እ.ኤ.አ. በ 2017 ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል ግሎባል ሙስና ባሮሜትር መሠረት የፓርላማ አባላት በአውሮፓ እና በመካከለኛው እስያ ውስጥ በጣም ሙሰኛ ባለሙያዎች ተደርገው ይታያሉ፡፡ 31 በመቶው ምላሽ ሰጪዎች አብዛኛዎቹ ወይም ሁሉም የፓርላማ አባላት ሙስና ይሰራሉ ብለው እንደሚያምኑ ተናግረዋል ፡፡ በተመሳሳይ 30 በመቶው ምላሽ ሰጪዎች የመንግስት ባለስልጣናትንም ሙሰኛ እንደሆኑ አድርገው እንደሚገነዘቡ ተናግረዋል፡፡ በአውሮፓ ህብረት የተደረጉ ጥናቶች በብሔራዊ ፓርላማዎች ላይ ዝቅተኛ እምነት እንዳላቸው ሪፖርት አውጥተዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ በ38 አገሮች በተካሄደው የፔው የምርምር ማዕከል የግሎባል አመለካከት እና አዝማሚያዎች ዳሰሳ ጥናት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በአጠቃላይ የውክልና ዴሞክራሲን ሀሳብ በተመለከተ ህዝባዊ ቁርጠኝነት በብዙ አገሮች በሚያስደንቅ ሁኔታ ደካማ ነው፡፡

በዜጎች የተመረጡ ተወካዮች ህግን የሚወስኑበት ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ሀገራቸውን ለማስተዳደር ጥሩ መንገድ እንደሆነ ሲጠየቁ 26 በመቶው የሃንጋሪ ምላሽ ሰጪዎች እና በፖላንድ ካሉት 20 በመቶው ብቻ "በጣም ጥሩ" ሲመልሱ በስዊድን እና በጀርመን 54 እና 46 በመቶው በቅደም ተከተል "በጣም ጥሩ" ነው በማለት መልሰዋል፡፡

በዚሁ የፔው ዳሰሳ፣ 42 በመቶ የሚሆኑ ምላሽ ሰጪዎች እንዲህ ዓይነቱ ሥርዓት ጥሩ ሐሳብ ነው ብለው ያስባሉ፡፡ "ጠንካራ መሪ" ያለ ፓርላማ ወይም ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብነት ውሳኔ ሊሰጥ የሚችልበትን ስርዓት በጥናቱ በተደረጉ ሀገራት 14 በመቶ ድጋፍ ብቻ የነበረ ቢሆንም፣ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ያለው አስተያየት በአገሮች መካከል በእጅጉ ይለያያል፡፡ ለምሳሌ በጣሊያን ውስጥ 29 በመቶ የሚሆኑት ምላሽ ሰጪዎች እንዲህ ዓይነቱ ቁጥጥር ያልተደረገበት ሥራ አስፈፃሚ ያለው ሥርዓት በተወሰነ ደረጃ ወይም በጣም ጥሩ ነው ብለው ያስባሉ፡፡

እነዚህ አኃዞች እንደሚጠቁሙት ፓርላማዎች ጠንካራ ህዝባዊ አመኔታን መገንባት ባለመቻላቸው በተወካይ ዴሞክራሲ እንደ ሥርዓት እርካታ እየታጣበት መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከዚህ በመነሳትም አሁን ያለውን የፓርላማ አሠራር በመሠረታዊነት ማሻሻል እንደሚያስፈልግ ይጠቁማል፡፡

### 2.1. 3 የምክር ቤት የሙስና ስጋት ተጋላጭነት

**ማነቃቂያ ጥያቄ**

| |
|---|
| ፓርላማው ከተሰጠው ሃላፊነትና ተግባር እንዲሁም ይህንን ከሚፈጽምበት የአሰራር ሂደቶች ውስጥ የትኞቹ ይበልጥ ለሙስና የተጋለጡ ናቸው? |

የሙስና ስጋት ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ፍትሃዊ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ወይም ሁኔታን ለመቆጣጠር እንደ ጉቦ መስጠት ወይም መቀበልን የመሳሰሉ ስነምግባር የጎደላቸው ወይም ህገወጥ ተግባራት ላይ ሊሳተፉ እንደሚችሉ ያመለክታል፡፡ ከዚህ ባስ ሲልም እስከ መንግስትን መቆጣጠር (State Capture) ሊደርስ የሚችል ስጋትን ሊደቅን ይችላል፡፡ ይህ ስጋት እምነትን ሊያዳክም፣ ፍትሃዊ ውድድርን ሊያዛባ እና የሃገራት ኢኮኖሚዎችን እና ማህበረሰቦችን ሊጎዳ ይችላል፡፡

ፖለቲከኞችና የህዝብ ተወካዮች ለሙስና የመጋለጥ እድላቸው በተለይ በአላደጉ አገሮች የሰፋ ነው። በብዙ የአፍሪካ ሀገራት የፓርላማ አባላት የሚከፈላቸው ዝቅተኛ ክፍያ ከሁሉም በላይ የሙስና ምንጭ እንደሆነ ተለይቷል። ምርጫዎች ውስጥ መሳተፍ ውድ በመሆኑም ተመረጮች ለምርጫ ዘመቻዎች ግብዓቶችን በማሰባሰብ ሂደት አላስፈላጊ አንዳንዴም ከህግ በተፃረረ መልኩ እንቅስቃሴ ሊደርጉ እንደሚችሉ ይታመናል። በተጨማሪም መራጮች ተወካዮቻቸው ላይ ተፅኖ በማሳደር ለሙስና ተጋላጭ ሊያደርጋቸው መቻሉ ታሳቢ ማድረግ ይጠበቃል (Davies, 2009)።

### 2.1.3.1 የጥቅም ግጭት

የጥቅም ግጭት (Conflict of interest) ማለት አንድ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣን ወይም ኃላፊ በስራ ተግባር እና ኃላፊነቱ ዉስጥ ከህዝብ ወይም ከመንግስት፤ከሃገር ጥቅም ይልቅ የግለን፤የቤተሰቡን ወይም የራሱን የቅርብ ዘመደ የገንዘብ ወይም ማንኛውም ሌላ ጥቅም ለማስቀደም ወይም ለማስጠት የሚያስችሉ ሁኔታዎች መኖር እንዲሁም ከመንግስታዊ ስራ ወይም ኃላፊነት ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚጋጭ ወይም ግጭት ሊፈጥር የሚችል ሁኔታ የሚያጋጥምበት ሁኔታ ነዉ።

የጥቅም ግጭት የሚኖረው የምክር ቤት አባላት የግል ፍላጎቶች ይፋዊ ተግባራቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ ወይም ተገቢ ባልሆነ መንገድ ላይ ተጽእኖ ሲያደርጉ ነው። የፍላጎት ግጭትም ሊኖር የሚችለው የምክር ቤት አባላት የግል ጥቅማቸው በህግ ከተሰጣቸው ተግባራቸው የበለጠ ሊጠቅም እንደሚችል በምክንያታዊነት ሲያስቡ ነው። ምንም እንኳ ተጨባጭ፣ እምቅ ወይም የታሰበ የጥቅም ግጭት መኖሩ ወዲያውኑ ብልሹ አሰራርን ባያመጣም የጥቅም ግጭቶች ሳይገለጡ፣ ሲቃለሉ፣ መጠቀምያ ሲሆኑ ወይም ሲደበቁ የሙስና እድሉ ይጨምራል።

የፓርላማ አባላት በማህበረሰብ አባላት እና በንግድ ስራ ላይ የሚያሳድሩት ተገቢ ያልሆነ ተጽእኖ ለፓርላማው ዘርፍ ዘላቂ አደጋ ነው። ይህ በተለይ አደጋ የሚሆነው የፓርላማ አባላት- እንደ ግለሰብ ሚኒስትሮች ወይም በፓርላማ ውስጥ- የህዝብ ገንዘብ አጠቃቀምን በተመለከተ ውሳኔ ሲያደርጉ ነው።

የጥቅም ግጭቶችን በአግባቡ አለመቆጣጠር ለፓርላማው ዘርፍ ቁልፍ አደጋ ነው። ተገቢነት ከሌለው ተጽእኖ ጋር በሚመሳሰል መልኩ፣ ይህ በተለይ — ውሳኔዎችን ሲያደርጉ ወይም ሲነኩ እና ለራሳቸው፣ ለፓርቲያቸው ወይም ለጓደኞቻቸው የገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅም ሊኖር የሚችልበት አደጋ ነው።

### 2.1.3.2 ከህግ ማውጣት ሂደት የሚያያዙ ስጋቶች

እንደ ህግ አወጪ አካል ፓርላማ ህጎችን የሚያወጣበት ሂደት ማለትም ረቂቅን ከማዘጋጀት ጀምሮ እስከ ድህረ ህግ ምርመራ ድረስ ሙስና ሊፈጸምበት የሚችልበት እድል እንዳለ በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶችና የሃገራት ተሞክሮዎች በግልጽ ያሳያሉ፡፡

የህዝብ ተወካዮች እንዲሰሩት የሚጠበቀው አንዱና ዋነኛው ተግባር የህዝብ ፖሊሲዎች በማውጣት ዜጎች ከመንግስት ተግቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ ማገዝ ነው፡፡ በዚህም በአብዛኛውም የዜጎችን የዕለት ተዕለት ህይወታቸው ጥራት ይወስናሉ፡፡ ይሁን እንጅ ከዚህ በተፀራሪ ተወካዮች የተሰጣቸውን ሃላፊነት ባለመወጣት ለግልና ቡዱናዊ ጥቅማቸውን ለማረጋገጥ የህግ አወጣጥ ስርኣቱን ሊያውሉት ይችላሉ፡፡ የሚወጡ ህጉች የህዝቡን ጥቅም ወደ ጎን በመተው በመንግስትና ዜጎች ያለውን ትምምን ይቀንሰዋል፡፡ ይህም የህግ አወጣጡ ስርኣት ለፖሊሲ ካፕችር (Policy Capture) ተጋላጭ ያደርገዋል (OECD, 2017) ፡፡

የሚወጡ ህጎችን በተመለከተ ዋና የሙስና አደጋ ስጋት ምክንያቶች የሚከተሉትን ይይዛል፡፡

- ***ከመጠን በላይ የሆነ የውሳኔ ሰጭነት-*** አብዛኛዎቹ የሙስና አደጋ መንስኤዎች በህጎች ውስጥ ለባለሥልጣናት ወይም ለተቋማት ከልክ ያለፈ ውሳኝነት የሚሰጡ ማለትም እንደ ከመጠን ያለፈ ሥልጣን፣ ፍትሃዊ ባልሆነ መልኩ ሰፊ የሥልጣን አጠቃቀም መመዘኛዎች፣ ወይም የሌሉ(ግልጽ ያልሆኑ) ከቁጥጥር ውጪ የሆነ ወሳኝነትን የሚሰጡና የሚጋጩ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡
- ***ደካማ ተጠያቂነት-*** የባለሥልጣናት እና ተቋማት ለውሳኔያቸው እና ለድርጊታቸው ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ በቂ ዘዴዎችን ማዘጋጀት ያልቻሉ ድንጋጌዎች ሙስናን ጨምሮ ለደካማ ምግባር መኖር እድልን ያሰፋሉ፡፡
- ***በቂ ያልሆነ ግልጽነት-*** ህጉ በሚመለከታቸው ባለስልጣናት እና ሂደቶች አሠራር ውስጥ በቂ ግልጽነት አለመኖር
- ***የሆነ አካልን ለመጠቀም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም-*** ከሕዝብ ጥቅም ወጪ የተወሰኑ ፍላጎቶችን ለመጥቀም ስልታዊ በሆነ መንገድ የተነደፉ ህጎች
- ***የሥርዓት ጥሰቶች-*** በሕግ ማውጣት ሂደት የሥርዓት መስፈርቶችን በመጣስ የሚከሰቱ የአደጋ ስጋቶች

### 2.1.3.3. የፖለቲካ ፓርቲ ፋይናንስ

በዘመናዊ ዴሞክራሲ የሕግ አውጭ አካላት አባላት የሚሾሙት በሕዝባዊ ምርጫ ነው። ምንም እንኳን በመርህ ደረጃ ህግ አውጭው የመራጮችን ፍላጎት ብቻ ማገልገል ያለበት ቢሆንም የተደራጁ የፍላጎት ቡድኖች ብዙውን ጊዜ ለፖሊሲ ጥቅማጥቅሞች ሲሉ ገንዘብ ወይም መረጃ በሚሰጡ ህግ አውጪዎች ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ይሞክራሉ።

የፖለቲካ ፓርቲዎች የግለሰቦች የመደራጀት እና ሃሳብን የመግለጽ መሰረታዊ መብቶች የሚገልጹበት የጋራ መድረኮች ናቸው። በዚህም የሀገርንና የሕዝብን ጥቅምና ፍላጎት መሠረት ያደረጉና ያስቀደሙ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች እንዲወጡ ወይም የወጡትም ቢሆን በአግባቡ እንዲፈጸሙ ለመከታተል ያስችላሉ። በተለይ ደግሞ ሥልጣን ላይ ያለው አካል ሥልጣኑን ያለአግባብ እንዳይገለገል በመቆጣጠርና የተፈጸሙ ወንጀሎችን ለሕግ እንዲቀርቡ እና ሕዝብ እንዲያውቃቸው በማድረግ የላቀ ሚና ይቻወታሉ።
እነዚህን ተግባራት በበቂ ሁኔታ ለመጠቀም ፓርቲዎች የገንዘብ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። ለዚህም የገንዘብ ልገሳዎችን ከተለያዩ አካላት ሊቀበሉ ይችላሉ። በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ እና ፖሊሲ ሂደት ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ ከግምት ውስጥ በማስገባት የፖለቲካ ፓርቲዎች ፋይናንስ ፍትሃዊነትንና ግልጽነትን በሚያረጋግጥ መልኩ መደራጀቱን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። (Kergueno and Vrushi, 2020)
ነገር ግን በግለሰቦች እና በድርጅቶች ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚደረጉ ልገሳዎች ከሙስና አደጋ ጋር ሊመጡ ይችላሉ። ምክንያቱም ለጋሾች ለስጦታቸው ምላሽ ምቹ ህጎችና ደንቦችን፣ የህዝብ ንብረት ሽያጭን፣ ወይም የመንግስት ኮንትራቶችን በልዩነት እንዲሰጣቸው ሊጠብቁ ይችላሉ።

አሳሳቢው ጉዳይ በፖለቲካ ፓርቲዎች የገንዘብ ድጋፍ ላይ የጥቂት የግል ዘርፍ ተዋናዮች ፍላጎት የበላይነት ነው። ይህ ወደ ህጋዊ የፖሊሲ ቁጥጥር (Policy capture) ሁኔታ ሊያመራ ይችላል። በግሉ ዘርፍ ያሉ ግለሰቦች ወይም ኩባንያዎች ገንዘብ የመለገስ መብታቸውን ተጠቅመው በምላሹ በመንግስት ጨረታዎች ላይ ተስማሚ ህግ ወይም ልዩ ተመራጭነትን እንዲያገኙ ያስችላቸዋል።

#### 2.1.3.4 ከምርጫ ሂደት ጋር የተያያዙ ስጋቶች

በምርጫ ቅስቀሳዎች ውስጥ ያለው ሙስና በሰፊው የሚያተኩረው በምርጫ ስልቶች ማለትም እያንዳንዱን የምርጫ ክፍል ያካተቱ መዋቅራዊ ሂደቶች እና በትክክል እንዲሰራ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን አላግባብ መጠቀምን እና የመንግስት ሀብቶችን አላግባብ መጠቀም ላይ ነው። ይህም የህዝብ አገልግሎቶችን አላግባብ መጠቀም እና የሲቪል ሰርቪሱን እና ሌሎች ሀብቶችን አላግባብ መጠቀምን ሊያካትት ይችላል።

### 2.1.3.4.1 የምርጫ አሰራርን አላግባብ መጠቀም

የምርጫ ዘዴዎች ምርጫን ለማካሄድ የተቀመጡ መዋቅሮች እና ሂደቶች ናቸው፡፡ እነዚህም የምርጫ ህጎች፣ የድምጽ መስጫ መዝገቦች፣ የድምጽ ቆጠራ እና የውጤት ማስታወቂያ ይገኙበታል፡፡ በምርጫ ወቅት የተወሰኑ ተዋናዮችን በዘመቻው ወቅት ጥቅም ለመስጠት ከእነዚህ ዘዴዎች ውስጥ የተወሰኑትን መጠቀም ይቻላል፡፡

*የምርጫ ህግን መጠምዘዝ*

የምርጫ ህግ ምርጫ እና የእጩዎች እና የፓርቲዎች ዘመቻዎች እንዴት መወዳደር እንዳለባቸው በትክክል ያስቀምጣል፡፡ የምርጫ ህጎችን በተደጋጋሚ ወይም ከምርጫ በፊት መቀየር መራጮችን ግራ ለማጋባት ሊያገለግል ይችላል፡፡

የምርጫ ቅስቀሳ ጊዜን ማሳጠር ወይም ማራዘም ለአንድ ፓርቲ ወይም እጩ ከሌላው የበለጠ ጥቅም ለመስጠት ወይም የፓርቲ ፋይናንስ ደንቦችን ለመጣስ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል (የቬኒስ ኮሚሽን 2003) ፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ ታዛቢዎች በካናዳ የ2015 የምርጫ ቅስቀሳ ጊዜ መራዘሙ ወግ አጥባቂ ፓርቲን እንደሚደግፍ እና የፓርቲ ፋይናንስ ደንቦችን እንዲያልፍ እና ትልቅ የፋይናንስ አቅሙን እንዲጠቀም አስችሎታል (ክላርክ 2015) ይጠቁማሉ፡፡

*የተቀነባበሩ የመራጮች መዝገቦች*

የመራጮች የምርጫ መዝገቡ የሚሰራበት ዘዴም ለማጭበርበር እና አድልዎ ለመፈጸም ከፍተኛ እድሎችን ይፈጥራል፡፡ ይህ በተለይ ዜጎች እራሳቸው መመዝገብ ካለባቸው ነገር ግን በሂደቱ ላይ በቂ ቁጥጥር ከሌለ ብዙ የተጭበረበሩ መራጮች ምዝገባን ሊያስከትል ይችላል፡፡

በሌላ በኩል የመመዝገቢያ መስፈርቶች በጣም ከባድ ወይም ገዳቢ ከሆኑ የተወሰኑ መራጮችን ድምጽ ለመስጠት እንዳይመዘገቡ ሊከለክሉ ይችላሉ፡፡ ከዚህም በላይ ሰዎችን ከመራጮች መዝገብ ውስጥ ለማስወገድ የሚያስችል ጠንካራ እና ፍትሃዊ ዘዴ ከሌለ ሙሰኛ የፓርቲ ኃላፊዎች እጩአቸውን የማይደግፉ መራጮችን ከዝርዝሩ ውስጥ በማስወገድ ሊጠቀሙበት ይችላሉ (Gomes et al, 2012)

በደንብ ያልተገነባ የመራጮች መዝገብ የሙት ድምጽ (Ghost Voting) የመስጠት እድል ሊፈጥር ይችላል። ይህም ስሙ በመራጭነት የተመዘገበ ነገር ግን በህይወት የሌለ ሰው እንዳለ ተገርጎ ድምጽ ሲሰጥ የሚከሰት ነው።

*የድምጽ ቆጠራን ማጭበርበር*

የድምጽ ቆጠራ አጠቃላይ የምርጫውን ሂደት ጥያቄ ውስጥ ሊጥሉ ለሚችሉ በርካታ የሙስና አደጋዎች ክፍት ነው። ለምሳሌ የምርጫ ካርዶችን ከምርጫ ጣቢያው ውጭ ባሉ ቦታዎች ማከማቸት ትልቅ የሙስና እድል ይፈጥራል። ምክንያቱም የምርጫ ካርዶች በሙስና የተዘፈቁ ባለስልጣናት በቀላሉ ሊቀየሩ ስለሚችሉ ነው።

**2.1.3.4.2 የመንግስት ሀብቶችን አላግባብ መጠቀም**

በስልጣን ላይ ያሉ ፓርቲዎች እና እጩዎች በምርጫ ቅስቀሳ ከሌሎቹ እጩዎች የበለጠ ጥቅም ለማግኘት የመንግስትን ሃብት በተለያዩ መንገዶች አላግባብ ለመጠቀም ሊሞክሩ ይችላሉ። ከነዚህ ዘዴዎች መካከል ድምጽ ለመግዛት የመንግስት አገልግሎቶችን መጠቀም (ድጎማ የሚደረግላቸው ምርቶችን)፣ ሲቪል ሰርቪሱን አላግባብ መጠቀም (አስገዳጅ ለሆነ የገንዘብ ድጋፍ ከሰራተኛው ደመወዝ መቁረጥ፣ ሰራተኞችን ከፍሎ የምርጫ ስራ ማሰራት)፣የግሉ ዘርፍ መመዝበር (ገንዘብ ካላዋጠችሁ ውል አቋርጣለሁ ብሎ ማስፈራራት)፣ የመንግስት ሚዲያዎችን በአድሎ መጠቀም የሚሉት ይገኙበታል።

**2.1.3.5 ሀብትና ጥቅምን ማሳወቅና ማስመዝገብ**

በአንድ ተቋም ውስጥ ግልፅነትና ተጠያቂነት ማረጋገጫ መርሆዎች አንዱ የተቋማት አመራርና ሰራተኞች ሀብት ምዝገባ ማድረግ ነው። በዚህ ረገድ የፓርላማ አባላት ካለባቸው ከፍተኛ ሃላፊነት እና ሊደርስባቸው ከሚችለው ከባድ ተጽእኖ አንጻር ሃብታቸውን ማስመዝገብ ይጠበቅባቸዋል። እንደ ህግ አውጪ አካል ደግሞ የምዝገባ ሰነዶች አጣርቶ ለሌሎች አብነት የሚሆኑ እርምጃወች ቢወሰድ ኖሮ አፈፃፀሙ አስተማሪነቱ የጎላ ይሆን ነበር። መመዝገቡ ተጠያቂነት ማስፈን ካልቻለ ግቡን መቷል ብሎ መውሰድ አዳጋች ያደርገዋል።

**2.1.3.6 ክትትል እና ቁጥጥር ተግባር**

ክትትል እና ቁጥጥር እንደ ህግ ማውጣት እና ውክልና ሁሉ አንዱ የፓርላማ ዋና ተግባር ነው። ፓርላማዎች ህዝቡን ወክለው የመንግስት አስፈፃሚ አካልን እንዴት ይይዛሉ የሚለውን ጉዳይ ያመለከታል። ጠንካራ የፓርላማ ክትትልና ቁጥጥር ለዲሞክራሲ አስፈላጊ እና በፀረ-ሙስና ትግል ውስጥ ትልቅ ሚና ይጫወታል።

ፓርላማዎች መንግስታትን በብቃት እንዲይዙ ከሚያስችሉ ቁልፍ መስፈርቶች መካካል በግልፅ የተቀመጡ የቁጥጥር ስልጣን ያሉት ጠንካራ የህግ ማዕቀፍ እና እነዚያን ስልጣኖች በተግባር በጥሩ ሁኔታ የሚጠቀሙ የበቁና የነቁ የፓርላማ አባላት መኖር የሚሉት ዋናዎቹ ናቸው። ነገር ግን ይህ ካለኖረ ደካማ ቁጥጥር ሲለሚኖር ሙስና መፈጸም እድሉን ያሰፋዋል።

ፓርላማዎች የፓርላማ አባላትን የቁጥጥር ተግባራቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ ያለመከሰስ መብት የሚያረጋግጡ እና ከፖለቲካ ፓርቲ ዲሲፕሊን ተጽዕኖ የሚጠብቃቸው ህጋዊ እርምጃዎች ከሌሉና በቅጡ ስራ ላይ ካለዋሉ ዳካማ የቁጥጥር ስራ መኖርን ያመላክታል።

ሌላው ከቁጥጥር በተያያዘ ሊኖር የሚችል የሙስና ስጋት ማሳያ ፓርላማዎች ለተቃዋሚዎች እና ለገለልተኛ የፓርላማ አባላት በክትትል ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር እድሎችን የማይሰጡነት ሁኔታ ሲኖር ነው። ይህም የገዢ ፓርቲ አባለት ብቻ የሞሉበት ቁጥጥር እዲደረግና በውጤቱም የፓርቲን ስም ላለማጥፋት ሲባል የይስሙላ ቁጥጥር እንዲያደርጉና ሃላፊነታቸውን እንዳይወጡ ሊያደርጋቸው ይችላል።

ፓርላማዎች የቁጥጥር ሂደቶችን እና መረጃዎችን ለህዝብ ተደራሽነት የማያረጋግጡ እና የሲቪል ማህበረሰብ ባለድርሻ አካላትን እና የተጎዱ ባለድርሻ አካላትን ማስረጃ እንዲያቀርቡ ወይም ከፓርላማ ጋር በክትትል ተግባራት ላይ እንዲሳተፉ የማይጋብዙ ከሆነ የሙስና ስጋት መኖርን ያመለክታል። የሚመለከታቸው የፓርላማ ኮሚቴዎች የቁጥጥር ባለድርሻ አካላት ሪፖርቶች በጊዜው መመርመር እና ፓርላማዎች ውጤቶቻቸውን እና ምክሮቻቸውን ከአስፈጻሚው አካል ጋር ተግባራዊ ማድረግ አለመቻል የሙስና ስጋትን ይፈጥራል።

በተመሳሳይ የፓርላማ አባላት የክትትል ተግባራቸውን ግልጽ በሆነ መንገድ የማያካሂዱ ከሆነ፣ የቁጥጥር ተግባራትን በሚያከናውኑበት ጊዜ የጥቅም ግጭቶችን ማስወገድ ካለቻሉ እና ለጋራ የህዝብ ጥቅም በሚጠቅም መልኩ ካልሰሩ የሙስና ተጋላጭነትን ይጨምራል።

### 2.1.4. በምክር ቤት አካላት የሚፈጸሙ የሙስና አይነቶች

#### 2.1.4.1 በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል

ይህ የሙስና አይነት ጠቅለል ይዘት ያለውና ከሌሎች የሙስና አይነቶች ጋር ተዘማጅነት ያለው ሲሆን በአፈጻጸሙም አንድ አባል የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ፤ የተሰጠውን ኃላፊነት በግልፅ ተግባር(በማድረግ) ወይም በግድፈት(ባለማድረግ) ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ ነው። ለምሳሌ የመንግስት ሰራተኞች ለገዥ ፓርቲ እንዲመርጡ ማስገደድ በተወሰነ

መልኩ የመከሰት እድል አለው። በተጨማሪም ገዢው ፓርቲ የመንግስትን ግንዘብና ሃብት ለምርጫ ቅስቀሳና ማስፈፀሚያ የመጠቀም ዝንባሌም አንዱ ስልጣን አላግባብ መጠቀም ማሳያ ሊሆን ይችላል። (Harutyunyan, 2021)። ስለሆነም የግል፣ የፓርቲን እና የመንግስትን ስራ ለይቶ ማየት ተገቢ ነው።

#### 2.1.4.2 ጉቦ

**አስረጅ ናሙና**

| |
|---|
| የአሜሪካ ኮንግረስ እ.ኤ.አ. በ 2002 ጂም ትራፊካንት የተባለ በኮንግሬስ ከምስራቃዊ ኦሃዮ የተወከሉ ዲሞክራትን ያሰናበት ሲሆን ግለሰቡ በዚያው አመት መጀመሪያ ላይ በፌደራል ፍርድ ቤት አንዳንድ የኮንግረሱ ሰራተኞቻቸውን በኦሃዮ እርሻው ዙሪያ የቤት ውስጥ ስራዎችን እንዲሰሩ እና ከፌዴራል ደመወዛቸው ወርሃዊ ክፍያ እንዲከፍሉ መጠየቁን ጨምሮ በ10 የጉቦ፣ የታክስ ስወራ እና የማጭበርበር ክሶች ተከሶ ነበር። |

ጉቦ አንድን  ኃላፊ  ወይም የመወሰን ሥልጣን ያለው ሠራተኛ ተግባሩን ወይም በሕግ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ በማከናወን ተገቢውን አገልግሎት መስጠት ሲገባው የተሰጠውን ኃላፊነት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ወይም አንድን ኃላፊ ወይም የመወሰን ሥልጣን ያለው ሠራተኛ ተግባሩን ወይም በሕግ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዳያከናውን ሀሳቡን ወይም ድርጊቱን ለማስለወጥ ወይም በኃላፊነቱ ማድረግ የሚገባውን ትክክለኛ ተግባር እንዳይፈጽም ወይም ማድረግ የማይገባውን እንዲፈጽም ለማድረግ የሚሰጥ ወይም የሚጠየቅ ተግባር ነው።

ጉቦ ከሥነ ምግባር ውጭ የሆነ ወይም ሕገወጥ እርምጃ በመውሰድ የግል ጥቅምን ማለትም እንደ ስጦታ፣ ብድር፣ ሽልማት፣ ጥቅማጥቅም ወዘተ ቃል መግባት፣ ማቅረብ፣ መቀበል ወይም መጠየቅ ነው። ጉቦ ከሕዝብ ጥቅም ጋር የሚጻረሩ ውሳኔዎችን ያስከትላል። ይህም በተቋማት ላይ ህዝባዊ አመኔታን በመቀንስ እና ደካማ የህዝብ አገልግሎት አሰጣጥን ይወልዳል።

በተወካዮች እና በሴናተሮች የተወከሉ የህግ አውጭ አካላት አንዳንድ የህግ ማሻሻያዎችን በማስደረግ ገቢያቸውን ለመጨመር ለሚፈልጉ ነጋዴዎች መግቢያ መንገድ ሆነው ይታያሉ። ስለሆነም ለፓርላማ አባላት ቀጥተኛ ጉቦ መስጠት፣ የውክልና ዘመን ሲያጠናቅቁ ለተወሰኑ የሥራ መደቦች መሾም፣ የንግድ አካላት ተወካዮችን ወደ በመንግሰት መዋቀር ውስጥ በመትከል የውስጥ መረጃን መስጠት እንዲችሉ ማደረግ የመሳሰሉት ሙስና አይነቶች

ይፈጸማሉ፡፡ በተጨማሪም የንግድ ድርጅቶች በሕግ ማውጣት ሂደት ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ሎቢዝም እንደ ዘዴ የሚጠቀሙ ሲሆን በሂደቱም ጉቦ እንደ መሳርያ ይውላል፡፡

ከነዚህ የጉቦ ዘዴዎች መካከል አንደኛው የተወካዮች ቀጥተኛ ጉቦ ሲሆን በቁሳዊ ጥቅማጥቅሞች ምትክ አንድ ባለስልጣን በተነገረው መንገድ ድምጽ የመስጠት ግዴታ ውስጥ በመግባት የሚፈጸም ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የውስጥ ሎቢዝም የሚባለው ሲሆን የንግድ ኮርፖሬሽኖች፣ ጥምረቶች እና ማህበራት እንደ ምርጫ አካል በቀጥታ የፓርላማ ምርጫ ሂደትን ላይ ጫና የሚያሳርፉበት ነው፡፡ በዚህም የምርጫ ቅስቀሳን በሙሉ ወይም በትልቁ ፋይናንስ በማድረግ የሚያስመርጧቸውን አባለት በተገቢው መንገድ ድምጽ እን ዲሰጡ የሚያደርጉበት ነው፡፡ ሌላው ዓይነት የውስጥ ሎቢዝም በተወካይ አካላት ውስጥ አንድ ነጋዴ በቀጥተኛ እንዲመረጥ የሚደረግበት ነው፡፡ «የዘገየ ሙስና» (Parachuting) በሚባል የጉቦ ሙስና ደግሞ አንድ ተወካይ አንዳንድ የንግድ ቡድኖችን የሚጠቅሙ ረቂቅ ሕጎችን የመደገፍ ግዴታ ውስጥ በመግባት በምትኩ የተወካይነት ጊዜው ማብቂያ ላይ ጥሩ ክፍያ ላለው የተከበረ ሥራ የማግኘት ፍላጎት የተነሳ የሚፈጸም የጉቦ አይነት ነው፡፡(Boshno,2016)

በአጠቃላይ ማንኛዉም የምክር ቤት አባል በኃላፊነቱ ወይም በሥራ ግዴታዉ ማድረግ የማይገባዉን ለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ላለማድረግ በቀጥታም ወይም በተዘዋዋሪ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ጥቅም እንዲሰጥ የጠየቀ ፣የተቀበለ ወይም በተቃራኒው የሰጠ እንደሆነ የጉቦን ሙስና ወንጀል ላይ ይወድቃል፡፡

### 2.1.4.3 የማይገባ ጥቅም መቀበል

ይህ ከጉቦ ጋር የሚመሳሰል ነገር ግን የተለየ የሙስና ወንጀል ሲሆን አንድ የፓርላማ አባል በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ማድረግ የሚገባውን ተግባር ለማከናወን ሲል ይህንኑ ተግባር ከመፈፀሙ በፊት ወይም ከፈፀመ በኂላ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ፣ ያገኘ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ የሚፈጽመው ወንጀል ነው፡፡ ይህ በተለይም ፓርላመው ካለው የክትትል እና የቁጥጥር ስራ ጋር በተያያዘ ሊፈጸም የሚችል ሲሆን የይስሙላ ቁጥጥር እንዲደረግ፣ጉድለቶች እንዲሸፋፈኑና የተዛባ ሪፖርት እንዲቀርብ ሰበብ ይሆናል፡፡

### 2.1.4.4 በህገወጥ መንገድ መሰብሳብ ወይም ማስረከብ

**አስረጅ ናሙና**

የአንድ የገዥ ፓርቲ አባላት ፓርቲያቸው በቀጣይ ለሚካሄደው አጠቃላይ ምርጫ ቅስቀሳ ለማድረግ ይረዳው ዘንድ ሃብት ለመሰብሰብ እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ ለዚህም በምክር ቤት ውስጥ

በተለያዩ ቋሚ ኮሚቴ ውስጥ አመራር በሆኑ ተወካዮቻቸው በኩል ማህተም ጭምር በመጠቀም የፓርቲ ምርጫ ዘመቻ የሚሆን ገንዘብ ማሰባሰብያ ኩፖን ተጠቅመዋል፡፡

ይህ የሙስና አይነት ከፖለቲካ ፋይናንስ ጋር የሚገናኝ ሲሆን በተለይ ደግሞ ከምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ መዋጮ በተያያዘ በብዛት የሚፈጸም ነው፡፡የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም የግል ተወዳዳሪዎች ቅስቀሳ ለማድረግ ይረዳቸው ዘንድ ገንዘብ በህጋዊ መንገድ ማሰባሰብ የሚችሉ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ህገወጥ በሆነ መንገድ ሲሰበስቡ ብቻ ሳይሆን የሰበሰቡትንም ገንዘብ ለግል ጥቅማቸው ሲያውሉት ይሰተዋላል፡፡

### 2.1.4.5 ንብረትን አለማስመዝገብ

የምክርቤት አባላት ልክ እንደሌላው የመንግስት ሰራተኛ ንብረታቸውን፣የፋይናንስ አቋምን፣ ስጦታ መቀበልን እንዲያስመዘግቡ ወይም እንዲያሳውቁ ይጠበቃል፡፡ ይህም የሚደረገውም በተለይ የህዝብ ተወካይ እንደ መሆናቸው ለሌሎች ዜጎች በስነ ምግባር መልካም አርአያ ሆኖ መገኘት ስለሚጠበቅባቸው ጭምር ነው፡፡ በተጨማሪም ይህን ማድረግ ምክርቤቱ በህዝብ ዘንድ ያለውን ተቀባይነት የሚያሳድግና በአስፈጻሚው ላይ ለሚያደርገው የክትትልና የቁጥጥር ስራ የሞራል ልእልና የሚያጎናጽፍ ነው፡፡

### 2.1.4.6 ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ

አንድ የፓርላማ አባል የሆነ ወይም የነበረ ሰዉ የኑሮ ደረጃዉ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የግል ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ የበለጠ እንደሆነ እንዲሁም ያለዉ ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የግል ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚየገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

### 2.1.4.7 በሌለው ሥልጣን መጠቀም

ይህ የሙስና አይነት የምክር ቤት አባላት ኃላፊነታቸውን ከተዉ በኂላ ማለትም የተወካይነት ጊዜያቸው ካበቃ፣ከታገዱ፣ በሥራው ላይ ያሉ በማስመሰል ለወደፊቱ የመንግሥት ሰው እሆናለሁ ብሎ በማሳመን ወይም ሳይሆኑ መስሎ በመቅረብ፤ ይህንን አደርጋለሁ በማለት የተስፋ ቃል በመግባት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ወይም ሥጦታ ከሌላ ሰው ሲጠይቁ፣ ሲቀበሉ የሚፈጽሙት ወንጀል ነው፡፡

### 2.1.4.8 በምርጫ ላይ የሚሰጥ መደለያ

**አስረጅ ናሙና**

> እ.ኤ.አ. በ 2005 በብራዚል በኮንግሬስ ውስጥ በተከሰት የድምፅ ግዢ ቅሌት አናሳ ገዥው ሌበር ፓርቲ ለድምፃቸው ምላሽ ከሁለት አጋር ፓርቲዎች ለመጡ ኮንግረስ አባላት BRL 30,000 (US$ 12,500) ወርሃዊ አበል ከፍሏል በሚል ተከሷል።

ይህ የሙስና አይነት የሚፈጸመው ከምርጫ ጋር በተያያዘ ሲሆን አንድ ሰው የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለውን ሌላ ዜጋ በመብቱ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀም ወይም መብቱን እነዲተው ለማድረግ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ገንዘብ ወይም በማናቸውም ሌላ አይነት ጥቅም የሰጠ፣ ወይም ለመስጠት ቃል የገባ እንደሆነ የሚከሰት ነው። ይህ አይነቱ ሙስና “ድምጽን መግዛት” (Vote Buying) በመባል የሚታወቅ ሲሆን መራጮችን በመደለል ድምጽን እንዲሰጡ የሚደረግበት ነው። ይህ በተለይ የዳበረ የዲሞክራሲ ስርዓት ባላቸውና ከፍተኛ የምርጫ ፉክክር በሚደረግባቸው ሃገራት በብዛት የሚታይ ቢሆንም በአንዳንድ ታዳጊ ሃገራትም መስተዋሉ አልቀረም። ለምሳሌ የሚከተለውን አስረጅ ተመልከቱ

**አስረጅ ናሙና**

> የ[illegible] መንግስት በተቀናቃኙ ፓርቲ UNITA ውስጥ መለያየትን ለመፍጠር እና ሰዎችን ወደ አዲሱ የአገዛዙ ታማኝ “UNITA-Renovada” ለማስከዳት ከተጠቀመባቸው ስልቶች አንዱ ታዛዥ ያልሆኑትን የፓርላማ አባላት እንደ ቤት፣መኪናዎች እና ሞባይል ስልኮች ያሉ የፓርላማ መብቶቻቸውን መንጠቅ ነው። በተጨማሪም፣ ‘የሚገባቸው’ የፖለቲካ ውቅር አባላት የፓርላማ አባላትን እና የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን ጨምሮ ከፕሬዚዳንቱ ዓመታዊ የ‘የገና ቦነስ’ ይቀበላሉ። ይህ ጉርሻ በአንዳንድ ዓመታት ውስጥ እስከ $30,000 ከፍ ያለ ሲሆን ይህም አመታዊ ደመወዛቸውን ያስናቀ ነበር።

ይህ አይነቱ ሙስና በብዙ መልኩ ዲሞክራሲን የሚጎዳ ብቻ ሳይሆን ከተንሰራፋና በአጭሩ ማቆም ካልተቻለ ወደ ስርዓታዊ ሙስና ሊያድግ የሚችል አደገኛ የሙስና ወንጀል ነው።

ሌሎች ከምርጫ ጋር በተገኛኘ የሚፈጸሙ የሙስና አይነቶች እጩ ተወዳዳሪ ምልመላ፣ ድምፅ ማጭበርበርን እና የተሸናፊነት የምርጫ ውጤትን ላለመቀበል ሲባል ጸብ ለሚጭሩ ሰዎች ገንዘብ በመክፈልና በጥቅም በመደለል ሕዝብን ለግጭት እንዲያነሳሱ ማድረግን ያካትታል። በዚህ ሂደት የሚመረጡ አባላትም ወደፊት በሚኖራቸው የተወካይነት ሚና ሙስናን በመከላከል ረገድ ጠንክረው ይሰራሉ ብሎ ለመገመት ያዳግታል።

## 2.2 ክፍል ሁለት- የሙስና መከላከያ ስልቶች፡ አጠቃላይ ዳሰሳ

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች፤**

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብቡና ከጎናችሁ ተሳታፊ ጋር በመሆን ተወያዩና የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

1. የምታውቋቸውን የሙስና እና የብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶችና ጥቅማቸውን ዘርዝሩ፡፡
2. በዘርፋችሁ ተግባራዊ የሚደረጉ ጠንካራ የሙስና መከላከያ ስልቶች ዘርዝሩ፡፡
3. ሙስናና ብልሹ አሰራርን አስቀድሞ መከላከል የሚያስገኘውን ፋይዳ አብራሩ፡፡

### 2.2.1. የዘርፉን የሰው ሃይል ማጎልበት

ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል የዘርፉን የሰው ሃይል በእውቀት፣ በክህሎት እና በአመለካከት መገንባት ዋነኛው የመከላከያ ስልት ነው፡፡ ሰራተኞች የተቋማቸውን ራእይና ተልእኮ እንዲሁም እሴት ጠንቀቀው ሊያውቁ ይገባል፡፡ ተቋማቸው የሚሰራባቸውን የህግ ማእቀፎች የስራ መመሪያዎችና ደንቦችን ማወቅ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በእጅጉ ይረዳል፡፡ በተለይ ሰራተኞች ስራቸውን ስነ-ምግባርን የተላበሰ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ በሥነ-ምግባራር ጉዳይ ላይ አመለካከትን የሚቀርጹ የስነ-ምግባር ስልጠናዎችን በየጊዜው መስጠት ተገቢ ነው፡፡ ሙያዊ ብቃታቸውንም እንዲያጎለብቱ ሙያዊ ስነ-ምግባርን የሚያሻሽሉ ስልጠናዎች ሊዘጋጁ ይገባል፡፡

### 2.2.2 ግልጽነትና ተጠያቂነት ማስፈን

#### 2.2.2.1 ግልጽነት

የግልጽነት ጉዳይ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃን ለዜጎች የማድረስ ጉዳይ ነው፡፡ ዜጎች ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ከቻሉ አሰራሮች ሁሉ ግልጽ ስለሚሆኑ ለአስተዳደር በደል፣ ለብልሹ አሰራር ወይም ለሙስና ሰለባ አይሆኑም፡፡

ዘርፎች በሴክተሩ የሚሰጠውን መንግስታዊ አገልግሎት በተመለከተ ምን ዓይነት አገልግሎት፣ በምን መስፈርት፣ ለማን እንደሚሰጥ በዝርዝር የሚያብራራ መመሪያ ማውጣትና ተጠቃሚው ህብረተሰብ ይህንኑ በሚገባ እንዲያውቅ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

በመንግስት አሰራር ውስጥ የግልጽነት አሰራር ከሌለ ዜጎች የሚፈልገውን መረጃ በሚፈልገው ወቅትና መጠን ሊያገኝ አይችልም፡፡ ይህ ደግሞ መብቱን ለመጠየቅና ለማስከበር እንቅፋት ከመፍጠሩም ባሻገር ፈጻሚውን አካል ተጠያቂ ማድረግ አይችልም፡፡

#### 2.2.2.2 ተጠያቂነት

የተጠያቂነት አሰራር ማለት ስራውን የሚሰራው አካል ስራውን በአግባቡ መስራት እንዳለበት እና እንዲሰራ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ካልተወጣ፣ ለፈፀመው ጥፋት የሚጠየቅበት /በቅጣት ወይም ካሳ በመክፈል/ ስርአት ማለት ነው፡፡ ይህ እውን እንዲሆን ግን የሚጠይቅ ማለትም ስራህን በአግባቡ ሰርተሀል ወይም አልሰራህም በማለት ለመከታተል፣ ለመቆጣጠርና እንደሚፈለገው ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር ኃላፊነትን መወጣት በውስጥ ያሉ አሰራሮች፣ ደንቦችና አሴቶችን ባግባቡ ተግባራዊ ማድረግ ሲሆን፣ ተጠያቂነት ደግሞ ለውጭ ጠያቂ አካል ምላሽ መስጠት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ተጠያቂነት ተግባራዊ ከሚሆኑበት መንገዶች መካከል የተሰሩ ስራዎችን በተመለከተ፣ ለህግ አውጪው አካል፣ በየደረጃው ላሉ ሃላፊዎች ሪፖርት ማቅረብ፣ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት፤ ተጠያቂነት መንግስት የሚሰጠውን ስራ ባግባቡ በመስራት፣ ህብረተሰብን ለማገልገል ፈቃደኛ በመሆንም ይገለጻል፡፡

### 2.2.3. የሥነ-ምግባር ደንብን ተግባራዊ ማድረግ

በሙስና መከላከል ስትራቴጂ ውስጥ ሙስናን ለመከላከል ከሚጠቀሱ ዘዴዎች መካከል አንዱ የሥነ-ምግባር ደንብ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ በአንድ ተቋም ውስጥ የሥነ-ምግባር ደንብ መኖሩ በተቋሙ ውሰጥ ተቀባይነት ያለው የሥነ-ምግባር ደረጃ እንዲሰፍን ይረዳል፡፡ የተቋሙ ሪሶርስ(ሃብት) ባግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል፣ አድሎዊነት እንዲወገድ፣ ቅንነትና ታማኝነት እንዲሰፍን ይረዳል፡፡ በተጨማሪም ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር፣ የተሰጠን ሃላፊነትም ባግባቡ ለመወጣት የሥነ-ምግባር ደንብ አስፈላጊ መሳሪያ ነው፡፡ የሥነ-ምግባር ደንብ ማንኛውም ስራ ሲሰራ ሥነ-ምግባርን በተላበሰ መልኩ መሆን እንዳለበት ስለሚደነግግ ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር የሚያጋልጡ የሥነ-ምግባር ባህርያትን ለመግታት ትልቅ አስተዋጽ አለው፡፡

የሥነ-ምግባር ደንቡን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ሁሉም ሰራተኛ ተሳታፊ የሚሆንበትን መንገድ መቀየስም ተገቢ ነው፡፡ በመጨረሻም ለሚከሰቱ የሥነ-ምግባር መተላለፎችን አግባብ ላለው አካል እንዲጠቁሙ ማድረግ፣ በመጠቆማቸውም ምክንያት መገለል እና ሌሎች ጥቃቶች እንዳይደርስባቸው መከላከል ይገባል፡፡

### 2.2.4. የሃብትና ጥቅም ማሳወቅና ማስመዝገብ

በየዘርፉ ሊከሰት የሚችለውን ሙስናና ብልሹ አሰራር ለመከላከልና ተጠያቂነትን ለማስፈን ከሚጠቅሙ የመከላከያ ስትራቴጂዎች መካከል በዘርፉ ውስጥ ያሉ ሰራተኞችና የስራ ሃላፊዎች ሃብታቸውን እንዲያሳውቁና እንዲያስመዘግቡ ማድረግ አንዱ ነው፡፡ የሃብት ማሳወቅና ምዝገባ ሕጋዊና ትክክለኛ የሥራ ፍሬ የሆነን ሃብት ምንጩ ካልታወቀ ሀብት

ለመለየት ያስችላል፡፡ ከዚህ ባሻገር ውሳኔ ሰጪዎች ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ በጥቅም ግጭት ሙስና ውስጥ እንዳይገቡ ያግዛል፡፡

### 2.2.5. የጥቅም ግጭትን የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን መከላከል

የጥቅም ግጭት (Conflict of interest) ከመንግስት ወይም ከህዝብ ተሰጠውን ሃላፊነት ባግባቡ እንዲወጣ አደራ የተሰጠው የስራ ሃላፊ ወይም ባለስልጣን በስራ ተግባር እና ሃላፊነቱ ዉስጥ ከህዝብ፣ ከመንግስትና ከሃገር ጥቅም ይልቅ የግሉን፤ የቤተሰቡን ወይም የራሱን የቅርብ ዘመዱን የገንዘብ ወይም ማንኛውም ሌላ ጥቅም የማስቀደም ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም ከመንግስታዊ ስራ ወይም ኃላፊነት ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ግጭት ሊፈጥር የሚችል ሁኔታ ነው፡፡

የጥቅም ግጭት ማንኛውም ዓይነት ኃላፊነትና ስልጣን ባለበት ሁኔታዎች እና አካባቢ ውስጥ እንደሚኖር ይታመናል፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ውስጥ ያሉ የስራ ሃላፊዎችና ሰራተኞች ለዜጎች አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት ከሃላፊነታቸው ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የጥቅም ግጭት ውስጥ ሊከታቸው የሚችሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥማቸው ግጭቱን በመከላከል ወይም ባግባቡ ማስተዳደር የሚችሉበትን ስልት ሊቀይሱ ይገባል፡፡

ለምሳሌ በተቋማት ለጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በጥናት መለየትና የጥቅም ግጭት እንዳይከሰት ለመከላከል የሚያስችል አሰራርን መዘርጋት፣ ሲፈጠርም አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ይገባል፡፡

### 2.2.6. የዘርፉን የፀረ-ሙስና ሚና ሚንስትሪም/የስራ አካል ማድረግ

የጸረ-ሙስና ትግል የአንድ ሰሞን ወይም የዘመቻ ስራ አይደለም፡፡ ዘርፎች ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ቁርጠኛ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ቁርጠኝነታቸው ከሚገለጽባቸው መንገዶች መካከል የጸረ-ሙስና ሚናን የስራቸው አካል ወይም ሜይንስትሪም ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ይህም ሲባል ዘርፎች የጸረ-ሙስና ትግልን የእቅዳቸውና፣ የየእለት የስራ እንቅስቃሴያቸው፣ የሪፖርትና የውጤት ግምገማ አካላቸው ሊያደርጉት ይገባል ማለት ነው፡፡ የተቋሙ ማህበረሰብም በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ የሚያደርጉትን የጸረ-ሙስና እንቅስቃሴ በባለቤትነት ስሜት ላይ በመመስረት ተሳትፏቸውን ከፍ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር እያንዳንዱ ተቋም ሙስናን ለመከላከልና ለመዋጋት የሚረዳው አደረጃጀት ፈጥሮ ወደ ትግሉ በቁርጠኝነት እንዲገባ ያግዘው ዘንድ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችን ማጠናከር ይጠበቅበታል፡፡

### 2.2.7. የመንግስት የስራ ሃላፊዎች ሚናን ማጠናከር

የተቋማት የስራ መሪዎች በተቋማቻ ሙሽናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ግንባር ቀደም መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ከዚህ አኳያ በየተቋሙ ያሉ የስራ ሃላፊዎች ራሳቸውን የመልካም ስነ-ምግባር አርዓያ ከማድረግ ጀምሮ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በርካታ ተግባራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከነዚህም መካከል፡-

- ☞ በተቋም ውስጥ ሥነ-ምግባራዊ አመራርን ተግባራዊ ማድረግ፣
- ☞ ሙስናን የመከላከል ስራን በተቋም ውስጥ ሜይንስትሪም ማድረግ፣
- ☞ ሥነ-ምግባራዊ ባህል በተቋም ውስጥ እንዲሰፍን ማድረግ፣
- ☞ የጥቅም ግጭትን የመከላከከያ ስትራቴጂዎችን ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ፣
- ☞ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንደርድን እንዲወጣ እና ተግባራዊ እንዲደረግ ማድረግ፣
- ☞ በተቋሙ የአሰራር ስርዓት እንዲተገበር ለሙስና በር የሚከፍቱ አሰራሮችን ማሻሻል፣
- ☞ በስነ-ምግባራቸው የላቁና በአገልግሎታቸው የተመሰገኑ ሰራተኞችን እውቅና መስጠት፣

### 2.2.8. ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራት

በአንድ ዘርፍ ውስጥ ሥነ-ምግባርን ማስፈንና ሙስናን መከላከል ለዘርፉ ብቻ የሚተው እንቅስቀሴ ሳይሆን የባለድሻ አካላትንም ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው፡፡ ምክንያቱም ባለድርሻን ያላሳተፈ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ ረጅም ርቀት መጓዝ አይችልምና ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ህብረተሰቡ በዘርፉ የሚከሰቱ ሙስናና ኢ-ስነምግባራዊ ድርጊቶችን በማጋለጥ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማድረግ የሚችሉበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት ይገባል፡፡ እንዲሁም ዘርፎች ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን በዚህ ዙሪያ ከሚሰሩ የሲቪል ማህበራትና የሙያ ማህበራት ጋር በቅንጅትና በትብብር ሊሰሩ ይገባል፡፡

### 2.2.9. ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ማዋል

በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ተገልጋዮችን ለሙስና የሚያጋልጥ እንግልትን ለማስቀረት ቴክኖሎጂን ተግባራዊ ማድረግ ጠቃሚ ነው፡፡ ቴክኖሎጂ ለሙስና የሚያጋልጥ የተንዛዛ ቢሮክራሲን በማሳጠርና ቀልጣፋ አገልግሎት እውን እንዲሆን በማድረግና ተግባራት ከሰዎች ንክኪ ነጻ እንዲሆኑ በማድረግ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ወቅቱ የሚጠይቀው የመከላከያ ስልት ነው፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ያሉ ሰራተኞች ሙስናን መከላከል የሚያስችል የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን በመስራት፣ ራሳቸውን ለአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ዝግጁ በማድረግ በቴክኖሎጂ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ሃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

## ማጠቃለያ

ፓርላማዎች የሚመረጡት ህዝብን እንዲወክሉ እንዲሁም ህግ የማውጣት እና መንግስትን የመቆጣጠር ህገ መንግስታዊ ሃላፊነት እንዲወጡ ነው። ስለዚህም ሙስናን ለመግታት በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ ትልቅ ሚና አላቸው። ይሁን እንጅ የሙስና ተጋላጭ የሆኑ የአሰራር ሂደቶች እና የሚፈጸሙ ሙስናዎች በዘርፉ የሉም ማለት አይደለም። ስለሆነም የሙስና ስጋቶችን የሚቀርፍና ቀድሞ የሚከላከል ስራ ለመስራት ብሎም በመንግስት ውስጥ ሙሉ ተጠያቂነት እና ግልፅነትን ለማረጋገጥ ያሉትን ህገ-መንግስታዊ፣ ፓርላማ እና ሌሎች የህግ ዘዴዎችን በከፍተኛ ሁኔታ መጠቀም አለባቸው።

መከላከል ማለት አንድ ሁኔታ ወይም ችግር ከመፈጠሩ በፊት ወይም ተፈጥሮም ከሆነ ሰፋ ያለ ጉዳት ከማድረሱ በፊት አስፈላጊ እርምጃዎችን በመውሰድ ችግሩ በመፈጠሩ ይደርስ የነበረውን ጉዳት ሙሉ በሙሉ እንዳይፈጠር ማድረግ ወይም የጉዳቱን መጠን ዝቅተኛ እንዲሆን ማድረግ ነው። ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባርም በአንድ ዘርፍ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የችግሩን ምንጭ የማድረቅ ተግባር ነው። በአንድ ዘርፍ ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስናና የብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችል ብቸኛና ወጥ የሆነ የመከላከያ ሥልት የለም። ይሁንና እንደተቋሙ ባህሪና ተልዕኮ እንዲሁም በየጊዜው የሚለዋወጠውን የሙስና ስትራቴጂ ግምት ውስጥ ያስገባ የሙስና መከላከያ ስትራቴጂ ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሙስና እና ብልሹ አሰራርን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ዘጠኝ ስትራቴጂዎች ተመላክተዋል። ይሁንና የመከላከያ ስልቶቹ ስምንት ብቻ ናቸው ማለት እንዳልሆነ ሰልጣኞች ልብ ሊሉ ይገባል። ልምዳቸውንና እውቀታቸውን በመጠቀም ልዩ ልዩ የሙስና መከላከያ ስትራቴጂዎችን በማምጣት የበኩላቸውን ሃላፊነት ሊወጡ ይገባል።

### የምእራፍ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ።

1. ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ አኳያ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ባይኖር ምን ዓይነት ችግሮች ሊከሰቱ ይችላሉ? ምሳሌዎችን በማቅረብ ምክንያታችሁን ዘርዝሩ።
2. በተለያዩ የፓለቲካ ስርዓት ውስጥ የሚገኙ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤቶች ሙስናን ከመከላከል አንጻር ያላቸውን እመቅ አቅም ከነምክነያቱ ግለጹ።

3. የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤቶች ከሕግ አስፈጻሚና ዳኝነት አከላት በአወቃቀር ደረጃ የሚለዩባቸውን ባሕርያት አስረዱ፡፡
4. በአሁኑ ወቅት አንዳንድ ምሁራን የምክርቤቶች መኖር ለሀገራትና ህዝቦች የሚፈለገውን ያክል ጥቅም እምብዛም አላስገኙም በሚል ይከራከራሉ፡፡ በዚህ ሐሳብ ትስማማላችሁ? ምክንያታችሁን ዘርዝሩ፡፡
5. በዚህ ስልጠና ከተመለከታችኋቸው የመከላከያ ስልቶች መካከል በዘርፋችሁ ተግባራዊ የተደረጉት የትኖቹ ናቸው? የተገኘውስ ለውጥ ምንድን ነው?
6. በዚህ ስልጠና ውስጥ ከተመለከታችሁት የመከላከያ ስትራቴጂ መካከል በዘርፋችሁ ተግባራዊ ያልተደረጉት የትኖቹ ናቸው? ምክንያታችሁን አስረዱ፡፡
7. ከምትሰሩበት የስራ አካባቢ አንጻር ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሙስናና ብልሹ አሰራርን እንዴት መቀነስ እንደሚቻል በዝርዝር ለተሳታፊዎች አስረዱ፡፡
8. በዚህ ስልጠና ካያችኋቸው በተጨማሪ ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን ዘርዝሩና ለተሳታፊዎች አስረዱ፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የምክርቤት ዘርፍ ሙስናና ብልሹ አሠራርን የመከላከል ሚና እና ማጎልበቻ ዘዴዎች

## መግቢያ

ቀደም ብሎ እነደተገለጸው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ከሦስቱ የመንግስት አካላት አንዱ እና ዋነኛው ነው፡፡ ህግ ያወጣል፣ የአስፈፀሚውን በጀት ያጸድቃል፣ ክትትል ያደርጋል፣ የአስፈፀሚው አካል የሚያቀርባቸውን ባለሥልጣናት ሹመት ያፀድቃል፡፡ እነዚህ ሁሉ ኃላፊነቶች በአግባቡ መወጣት ማለት ሀገሪቱ በልማት እድገት፣ በዲሞክራሲና በመልካም አስተዳደር ሥርዐት ግንባታ ለምታደርገው እንቅስቃሴ አስፈፀሚውን አካል ሚና ማጎልበት ነው፡፡ ይህንን ኃላፊነት አለመወጣት ማለት ደግሞ ለሙስናና ለብልሹ አሰራር በር መክፈት ማለት ነው፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ሕገ መንግሥቱ ያስቀመጠውን የግልጽነትና ተጠያቂነት መርሕ ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ከማንኛውም የመንግሥትና የግል ተቋማት በእጅጉ የላቀ ኃላፊነት አለበት፡፡ የግልጽነትና ተጠያቂነት መርሖዎች መጓደል ለሙስናና ብልሹ አሠራር መስፋፋትና መንሰራፋት መንገድ ከፋች ሆኖ ይታያል፡፡ በዚህ ረገድ በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ ምክርቤቶች ይህን ዕኩይ ተግባርና ድርጊት በመከላከል ረገድ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ፡፡ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት አባላት የሙስና ወንጀል በመከላከል የመንግሥት ተቋማት፣ አሠራሮችና አገልግሎት አሰጣጦች ፍትሐዊ፣ ከመድሎና ከብልሹ አሠራር የጸዱ እንዲሆኑ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ የመንግሥት ተቋማትን በመከታተልና በመደገፍ፣የግልጽነትና የተጠያቂነት አሠራር እንዲጠናከር ዓይነተኛ ሚና አላቸው፡፡

እንዲሁም የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት አባላት ራሳቸው እና ተቋማቸው ከሙስናና ብልሹ ዕኩይ ተግባራት የጸዱ በመሆን ሙስናን የመከላከል ምሳሌነታቸውን ማሳየት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሙስና የፈጸሙ ማንኛውም ዜጎች ያለ ምንም ዓይነት ልዩነት በፍርድ እንዲጠየቁ የማድረግ የክትትል ስራ ይሰራሉ፡፡ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ሙስናና ብልሹ አሠራርን የሚከላከሉ ጠንካራ የፀረ-ሙስና ተቋማት እንዲቋቋሙ እና የሕግ ማዕቀፎች እንዲዘረጉ አስፈጻሚውን አካል መከታተልና መደገፍ ይጠበቅበታል፡፡ ስለሆነም የተወካዮች ም/ቤት እነዚህ ሁሉ ኃላፊነቶች በአግባቡ በመወጣት የሙስና መከላከል ሚናውን መጫወት አለበት፡

በዚህ ምዕራፍም ከላይ የተጠቀሱት አበይት ኃላፊነቶችን በመወጣት ሂደት ውስጥ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ያለውን ሚና ማቅረብ ተሞክሯል፡፡

በዚህ ምዕራፍ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ሙስናና ብልሹ አሠራርን የመከላከል ሚና ማጎልበቻ መንገዶች ይቀርባል፡፡ የሚሸፈኑ ዝርዝር ሐሳቦችም፣ የምክርቤት አባላትን ግንዛቤ ማሳደግ፣ ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነጻ ማድርግ፣ የዴሞክራሲ ሥርዓት እና ባህል ማጎልበት የሚሉት ናቸው፡፡ ከነዚህ በተጨማሪ ምክርቤቱ ተቋማትን ለየት ባለ መንገድ የመደገፍና አቅምን የማሳደግ፣ የሙስናና ብልሹ አሠራርን መረጃ ማግኛ ሥርዓት የማጠናከር እና የዜጎችን አመኔታን የሚገነቡ ተግባራትን ማጠናከር እና ለሌሎች አርአያነት ያላቸውን ተግባራት መፈጸም የሚሉትም ከሚብራሩ ፍሬሐሳቦች መካከል ናቸው፡፡ ርእሶቹን ሠልጣኞች እንዲረዷቸው ለማድረግ የሚያስችሉ የውይይት ጥያቄዎችም በዝግጅቱ ተካተዋል፡፡

### ዓላማ

**ሠልጣኞች ይህን ምዕራፍ ሲያጠናቅቁ፤**

- የምክርቤት ዘርፍ ተቋሙስናና ብልሹ አሠራርን በመከላከል ያለውን ሚና ያብራራሉ፣
- የተወካዮች ምክርቤት በሚያደርገው የህግ ማውጣት ሂደት ለሙስናና ብልሹ አሠራር ክፍተት የሚፈጥሩ ጉዳዮችን ይለያሉ
- የተወካዮች ምክርቤት በሚያደርገው የበጀት ማጽደቅ ሂደት ለሙስናና ብልሹ አሠራር ክፍተት የሚፈጥሩ አካባቢዎችን ይለያሉ፣
- የተወካዮች ምክርቤት የመንግስት ተቋማት ለሙስናና ብልሹ አሠራር የተጋለጡ እንዳይሆኑ በሚያደርገው የክትትል ሂደት ላይ ይሳተፋሉ ፣
- የእጩ የመንግስት ተሿሚዎች ብቃትን ማረጋገጫ ዘዴዎች ያዘረዝራሉ፤
- የምክርቤት አባላት ሙስናን የመከላከል ሚና የሚያጎለብቱ ዘዴዎችን ይዘረዝራሉ፤
- ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነፃ በሆነ መንገድ የተሰጣቸውን ተግባራት ያከናውናሉ፤
- የዘርፉ ተቋማት ዴሞክራሲ ሥርዓት እና ባህል እንዲጎለብት ያላቸውን ሚና ይለያሉ፤

**የሚወስደው ጊዜ:** 4:00 ሰዓት

## 3.1 ክፍል አንድ- የምክርቤት ዘርፍ ሙስናና ብልሹ አሠራርን የመከላከል ሚና

### ተግባራዊ መወያያ ጥያቄዎች

| |
|---|
| በመንግስት አስፈጻሚ አካላት ውስጥ ሊፈጸሙ የሚችሉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ሳይከሰቱ ለመከላከል እና ሲከሰቱም ተገቢውን ተጠያቂነት ለማረጋገጥ የምክርቤት ተቋማት ያላቸው ሚና ምንድነው? የተቋማችሁ ሚናው በምን በምን ዋና ዋና ተግባራት ይገላጻል? |

### 3.1.1 ወቅታዊ የሆኑ ሕጎች እንዲወጡ ማድረግ

**ማነቃቂያ ጥያቄ**

**ሶቅራጥስ** ፡- ሂፒያስ፣ ግን ህግ በሀገር ላይ የሚደርስ ጉዳት ወይስ ጥቅም ነው ትላለህ?
**ሂፒያስ** ፡- እኔ እንደማስበው ህግ የሚወጣው ይጠቅማል ከሚል እይታ አንፃር ነው፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ህጉ በመጥፎ ከተሰራ ጎጂ ነው፡፡ (Plato, Hippas Major, 284D)

ከላይ ከቀረበው ምልልስ በመነሳት

i. የህግ መኖር በራሱ ጠቃሚ ነው?

ii. "ህግ በመጥፎ ከተሰራ" የሚለውን ሀረግ እንዴት ተረዳችሁት?

ህግ ማውጣት የአንድ ምክር ቤት ሉዓላዊነት አስፈላጊ ባህሪ ሲሆን የፓርላማ ሉዓላዊነት 'Legislative Supremacy' በመባልም ይታወቃል፡፡ የህገ መንግስታዊ ዴሞክራሲ ስርዓት ባላቸው ሃገራትም የምክር ቤቱ መብት ነው፡፡ በዚህ ረገድ አለምአቀፍ የፓርላማዎች ህብረት እ.ኤ.አ በ 2001 ባቀረበው ሰነድ መሰረት ፓርላማዎች ተገቢውን ህግ ማውጣት፣ ተዛማጅ አለም አቀፍ የህግ መሳሪያዎችን በማፅደቅ ብሎም በብሔራዊ ሕግ ውስጥ ድንጋጌዎቻቸውን በማካተት ረገድ ንቁ ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተጨማሪም አንድ ምክር ቤት ህግ ከማውጣት ባሻገር ህጉን የሚያወጣበትንም መንገድ ማየት ዋሳኝ ነው፡፡ምክንያቱም ይህ ሂደት የህጉን ተቀባይነት ስለሚወስን ነው፡፡

በፓርላሜንታዊ ዲሞክራሲ ውስጥ አብዛኛዎቹ ህጎች ከአስፈጻሚው የሚመነጩ ቢሆንም ከሁሉም በላይ እዚህ ላይ አስፈላጊው ነጥብ ምክር ቤቱ ህጎችን በጥልቀት መመርመሩ እና ያሉትን እንደ የህዝብ ደምጽ መስማት ያሉ መሳሪያዎችን መጠቀሙ ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ ሪክ ስታፔንኸርስት እንዲህ ብለዋል፡- 'የህግ አውጭ ረቂቆች እና የኮሚቴዎች ውይይት በተለይም ኮሚቴዎች በህዝብ ምክክር ላይ በሚሳተፉበት ጊዜ ለአስፈፃሚ የበላይነት ተቃራኒ ሚዛን ይሰጣል፡፡

ይህ የበለጠ ተጠያቂነትን እና ግልጽነትን ከማጠናከር በተጨማሪ የሚወጣው ህግ የጋራ ጥቅሞችን የበለጠ እንዲያንፀባርቅ ያስችላል፡፡ ፖሊሲ ማውጣት በአጠቃላይ ለአስፈጻሚው አካል የተተወ ቢሆንም፣ ፓርላማ፣ እንደ የህዝብ ተወካይ ተቋም፣ የመንግስት ፖሊሲዎች እና ማሻሻያዎች ከፓርቲያዊ ፍላጎቶች እና ቅድሚያ ከሚሰጧቸው ጉዳዮች በተቃራኒ ሀገራዊ ፍላጎቶችን ከግምት ውስጥ እንዲገቡ ይረዳል፡፡

ይህ ግን የሚወሰነው ምክር ቤቶች በስራ አስፈጻሚው ላይ በሚያሳርፉት ተጽዕኖ መጠን ሲሆን በዚህ ረገድ ሲታይ አራት አይነት ፓላማዎችን እናገኛለን፡፡ እነሱም Rubber Stamp- በቀላሉ የአስፈፃሚ እርምጃን የሚደግፉ ፓርላማዎች፣ Emerging- በተጽዕኖ ረገድ በማደግ

ደረጃ ላይ ያሉ ፓርላማዎች ፣ Informed- በአስፈጻሚው አካል ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ፓርላማዎች እና Transformative- አስፈፃሚ አካላት በፖሊሲ እርምጃዎች ላይ የሚያሳትፋቸው እና የሚደራደራቸው ፓርላማዎች ናቸው።

ሌላው ተያይዞ መነሳት ያለበት ጥያቄ ሙስናን በመከላከል ረገድ ምን ምን አይነት ህጎች በፓርላማው መውጣት አለባቸው? የሚለው ነው። ምንም እንኳ ይህ የሚወሰነው ሃገራት ካሉበት የየራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ ቢሆንም እንደ አጠቃላይ ግን በአብዛኛው ሃገራት በተመሳሳይ የሚወጡ የህግ አይነቶች አሉ። ከነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል የመረጃ ተደራሽነት እና የመረጃ ነፃነት ህግ፣ የጠቋሚዎች ጥበቃ ህግ፣ የፓርቲ ፋይናንስ እና የምርጫ ዘመቻዎች ህግ፣ የፓርላማ አባላት እና ሌሎች የመንግስት ባለስልጣናት ታማኝነት ህግ፣ በመንግስት እና ህዝብ ጉዳዮች ውስጥ ግልፅነትን እና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚወጣ የቁጥጥር ህግ እና የመንግስት ግዥ ሕግ የሚሉት ናቸው። በሀገር ደረጃ አያሌ በሕግ መመራት የሚገባቸው ወቅታዊና አንገብጋቢ ጉዳዮች አሉ። እነዚህን ወቅታዊ ጉዳዮች ለሀገር ካላቸው ጠቀሜታና ፋይዳ አንፃር በቅደም ተከተል በማስቀመጥ በሕግ አግባብ እንዲመሩ ማድረግ አማራጭ የሌለው መንገድ ነው። ስለሆነም ከጉዳዮቹ መካከል አንገብጋቢውና ጊዜ የማይሰጠውን በመምረጥ በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ሕግ እንዲወጣላቸው ማድረግ ያስፈልጋል። ከዚህም በተጨማሪ በሕግ አወጣጥ ሂደቱ ላይ ባለድርሻ አካላትን ማወያየትና ሲቪል ማኅበራትን በነቃ ሁኔታ ማሳተፍ ወሳኝ ነው።

ጥቅሞቻቸውንና ፍላጎታቸውን ማስቀደም የሚፈልጉ ወይም የሌሎችን ጥቅም ለመጉዳት የሚያስችሉ ሕጎች እንዲወጡ የሚፈልጉ ቡድኖች አሉ። እነዚህ ቡድኖች የሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች አንገብጋቢና ቅድሚያ ሊያገኙ ከሚገባቸው ጉዳዮች ይልቅ የራሳቸውን ጥቅምና ፍላጎት ማስቀደም ነው። በተጨማሪም በባለድርሻ አካላትና ሲቪል ማኅበራት ዳብሮ ከሚወጣ ሕግ ይልቅ በሚቀርቧቸውና በጥቅም በሚደልሏቸው የም/ቤት አባላት በኩል በአቋራጭ እንዲጸድቅ የሚንቀሳቀሱ አካላትም አሉ። የምክርቤት አባላትም የራሳቸውን ጥቅም የሚያስቀድሙ ሕጎች እንዲወጡ በሚፈልጉ ቡድኖች ተጽእኖ ስር ሊወድቁ የሚችሉባቸው አጋጣሚዎች አሉ ማለት ነው። በኅብረተሰብ የተለያዩ አካላት ተሳትፎ ባልዳበረበት ሁኔታ የሚወጡ ሕጎች ወቅታዊና አንገብጋቢውን ከመምረጥ ይልቅ ለቡድኖች ጥቅምና ፍላጎት ያጋደሉ ሕጎች እንዲወጡ የተመቻቸ ሁኔታን ይፈጥራሉ ። ስለሆነም በተወካዮች ም/ቤት የሕግ አወጣጥ ሂደት ላይ የባለድርሻ አካላትና የሲቪል ማኅበራት ተሳትፎ ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል ወሳኝ ጉዳይ ሆኖ ይታያል።

### 3.1.2 በረቂቅ ህጎች ላይ የሙስና ስጋት ትንተና ማድረግ

**አስረጅ ናሙና**

ከግንቦት 2019 ጀምሮ በሥራ ላይ የዋለው የቱርክ ማህበራዊ እና አጠቃላይ የጤና መድን ህግ ቁጥር 5510 የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የተለያዩ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች ዓይነቶች እንዲመድብ እና "የላቀ ደረጃ ሆስፒታሎች" ተብለው የሚለዩ አዲስ የሆስፒታሎች ምደባ እንዲፈጥር ይፈቅዳል፡፡ እንደ የላቀ ደረጃ ሆስፒታል ለመቆጠር የሚያስፈልጉት መስፈርቶች ባለ 600 አልጋ፣ 60,000 ካሬ ሜትር የውስጥ መገልገያ ስፍራ፣ 240 ዶክተሮች እና 480 ነርሶች እንዲኖሩት ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ሆስፒታልም ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የተሻለ ጥቅም እንዲያገኝ ይጠበቃል፡፡ ነገር ግን መስፈርቶቹን የሚያሟላ አንድ ሆስፒታል ብቻ ሲሆን እሱም ቀደም ሲል የጤና ጥበቃ ሚኒስትር በነበሩት ፋህረቲን ኮቻ ባለቤትነት የተያዘ ነው፡፡

ከላይ በቀረበው አስረጅ በመነሳት

i. *ሙስናን ከመዋጋት አንጻር ህግች ከመውጣታቸው በፊት ምን ዐይነት ጥንቃቄ መወሰድ አለበት ትላላችሁ?*

ii. *በምክር ቤታችሁ የህግ ማወጣት ሂደት ውስጥ ህጎች የሙስና ስጋት የሌለባቸው ስለመሆኑ የሚጣራበት አሰራር አለ?*

iii. *የሚውጡ ህግች ምን ምን አይነት የሙስና ስጋቶች ሊታይባቸው ይችላል?*

አንድ ፓርላማ ሙስናን ከመከላከል አንጻር ሊሰራ የሚገባው ዋና ተግባር ረቂቅ ህጎች ከመጽደቃቸው በፊት ተገቢ የሆነ የሙስና ስጋት ትንተና ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም አጠቃላይ የሙስና ስጋት ትንተና ረቂቅ ህግ ሊፈጥር የሚችለውን ሁለት አይነት የሙስና አደጋዎችን ማለትም የማስፈጸም ስጋቶች (Enforcement risks) እና የመሰረተዊ ይዘት (Substantive risks) ስጋቶችን ይመረምራል፡፡

**የማስፈጸም ስጋቶች-** ሕጉ በተግባር እንዴት ይሰራል ከሚለው በመነሳት ሕጉን እንዲከተሉ፣ እንዲተገበሩት ወይም እንዲያስፈጽሙት በሚጠበቁ ሰዎች ባህሪ ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ልዩ ትኩረት በመስጠት ይተነትናል፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ህግ በአፈፃፀሙ ለፈጻሚዎች የማስፈጸሚያ ስልጣናቸውን ለግል ጥቅማቸው አላግባብ እንዲጠቀሙ ማበረታቻ እና እድል ሊሰጥ ይችላል፡፡

ስለዚህ የዚህ አይነት ስጋቶችን ለማወቅ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ማንሳት ተገቢ ይሆናል፡፡

☞ የመወሰን ነጻነት (Discretion) ፡ አስጻሚያ አካላት ከልክ ያለፈ ወይም ተገቢ ያልሆነ የመወሰን ነጻነት አላቸው?

- ጽሑፋዊ ትንተና (Textual Analysis) ረቂቁ አሻሚ ቋንቋ ይዟል? ሁሉም ቃላት በትክክል ተገልጸዋል?
- ማስፈጸሚያ (Enforcement)፡ ህጉን የማስከበር ሃላፊነት ለትኛው የመንግስት አካል ወይም አካላት ነው የተሰጠው? ይህን ለማድረግ በቂ ስልጣን አላቸው? የኃላፊነት መደራረብስ አለ?
- ቁጥጥር (Oversight) - አስፈጻሚ አካላት ውሳኔያቸውን እንዴት እንደሚጠቀሙ የመቆጣጠር ኃላፊነት ያለበት የትኛው የመንግስት አካል ወይም አካሎች ናቸው?

**መሰረታዊ የይዘት ስጋቶች-** የሚነሱት ደግሞ በተወሰኑ ሰዎች ወይም አካላት ላይ ሕጉ ከሚሰጣቸው ጥቅሞች እና ጉዳቶች በተያያዘ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ህግ ለተወሰኑ ግለሰቦች ወይም አካላት አጠራጣሪ ወይም አጠያያቂ የታለሙ ጥቅሞችን ሊሰጥ ይችላል፡፡ በተቃራውም የተወሰኑ ግለሰቦችን ወይም አካላትን ሊጎዳ ይችላል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ በቂ ማሳመኛ (Justfication) መኖር አለመኖር ነው፡፡ ይህን ለመለካት ረቂቁን የሚያብራራ ሪፓርት አለ? በተለያዩ ቡድኖች ላይ የሚደርሰው ጥቅም እና ጫና አሳማኝና ትክክል ነው? ከአጠቃላይ ህጉ የተለዩ ሁኔታዎች ተለይተዋል/ተብራርተዋል? የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሳት ያስፈልጋል፡፡

ሁለቱም የስጋት አይነቶች የሚከሰቱት ህግ ሲረቀቅ ወይም ከውጭ ምንጮች ምንም አይነት ግብአት ሳይኖረው ለምሳሌ በህጉ ጉዳይ ላይ ልዩ ፍላጎት ወይም እውቀት ያላቸው ወይም የአጠቃላይ ህዝቡ አካል የሆኑ ዜጎች ሳይሳተፉበት ሲቀር ነው፡፡

በዚህ ምክንያት፣ የሙስና ስጋት ትንትና ረቂቅ ህጉ ግልጽ በሆነ እና አሳታፊ ሂደት መዘጋጀቱን መገምገም አለበት፡፡ ይህም ረቂቅ ጽሑፉን በወቅቱ ይፋ ማድረግ እና በአንቀጾቹ ላይ በቂ ህዝባዊ ምክክር ማድረግን ያካትታል፡፡ ስለዚህ ከሁለቱ የስጋት አይነቶች በተጨማሪ **ከሂደት ጋር የተያያዙ ስጋቶችም** በስጋት ትንተናው መታየት እንዳለባቸው ያመለክታል፡፡ ስለሆነም የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማነሳት ከሂደት አንጻር ያሉ ስጋቶችን መተንተን ይቻላል፡፡

- ግልጽነት (Transparency) ረቂቁ ለግምገማ በቂ ጊዜ አግኝቶ በይፋ ለህዝብ ቀርቧል?
- ምክክር (Consultation) ረቂቅ ህጉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከሚነካቸው ግለሰቦች/ቡድኖች ጋር ምክክር ተደርጎ ነበር?

### 3.1.3 በመንግሥት ተቋማት ላይ የሚደረግ ክትትልና የመስክ ምልከታና (Over sight)

**አስረጅ ናሙና**

በዋናው የኦዲት መ/ቤት ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የሚቀርቡ የኦዲት ግኝቶች ችግሮችን ያመላክታሉ፡፡ የሚቀርቡ ሪፖርቶችም ከዓመት ዓመት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ ይሁን እንጅ የተወካዮች ምክርቤት ቋሚ ኮሚቴ ምልከታና ክትትል (oversight) ሪፖርቶች በዋናው ኦዲት መ/ቤት ከሚያመላክተው ውጤት ጋር ልዩነት አላቸው፡፡ በሁለቱም አካላት ሪፖርቶች የተመላከቱ ችግሮች በቅጡ ባለመፈታታቸው በዜጎች ዘንድ ቅሬታን ፈጥሯል፡፡

በዚህ ረገድ

1. የምክርቤት አባላት ቁጥጥር እና ክትትል ሙስናና ብልሹ አሠራርን ከመከላከል አንጻር እንዴት መቃኘት እንዳለበት ግለጹ፡፡
2. በምክር ቤቱ የቁጥጥር እና ክትትል ሂደት ውስጥ የፓርቲ ወገንተኝነት ተጽእኖ እንዴት ይገለጻል?
3. ቁጥጥር እና ክትትል ሙስናን በመከላከል ውጤታማ እንዲሆን ምክርቤቱ ምን ዓይነት ስራ መሥራት አለበት?

ምክር ቤቱ የመንግስትን አስፈፃሚ አካል የመቆጣጠር ልዩ ስልጣን አለው፡፡ እንደ አለማቀፍ የምክር ቤቶች ህብረት አገላለጽ 'የመንግስት ቁጥጥር አስፈፃሚውን ተጠያቂ ማድረግ- ከሶስቱ የምክር ቤት ዋና ተግባራት አንዱ ነው፡፡

ስለሆነም የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አንዱ ቀዳሚ ተግባር የሕግ አስፈጻሚውን፣ የዳኝነት አካሉንና በቋሚነትም ይሁን በጊዜያዊነት ከመንግሥት ጋር የሚሰሩ ሌሎች አካላትንና ተቋማትን ተግባርና ኃላፊነት መመልከት፣ ማገዝ፣ መቆጣጠርና ክትትል ማድረግ ነው፡፡

የምክር ቤት አባላት ቁጥጥርን እንዲያደርጉ መነሻ የሆኑ አራት ዋና ዋና ምክነያቶች ያሉ ሲሆን እነርሱም፡-

☞ የአስፈፃሚ እንቅስቃሴዎችን ግልጽነት እና ክፍትነት ለማረጋገጥ

ምክር ቤቶች የመንግስት ፖሊሲዎች እና ተግባራት ላይ ክርክር፣ ምርመራ የሚደረግበት እና የህዝብ አስተያት የሚሰጥበት የህዝብ መድረክ ላይ በማቅረብ የመንግስትን ተግባራትን እንዲታዩ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

☞ አስፈፃሚውን አካል ተጠያቂ ለማድረግ

የምክር ቤት ቁጥጥር የመንግስት ፖሊሲዎች መተግበራቸውን እና የሚፈለገውን ተፅእኖ እያሳደሩ እንደሆነ ይመረምራል፡፡

☞ የፋይናንስ ተጠያቂነት ለማረጋገጥ

ምክር ቤቶች በመንግስት የገንዘብ ድጋፍ በሚደረግላቸው አገልግሎቶች ውስጥ ያለውን ብክነት በማጉላት የመንግስት ወጪን ያፀድቃሉ እና ይመረምራሉ:: ዓላማቸውም ኢኮኖሚውን ማሻሻል፣ የመንግስት ወጪዎችን ቅልጥፍና እና ውጤታማነት ማሻሻል ነው::

☞ የሕግ የበላይነትን ከፍ ማድረግ

ምክር ቤቱ ፖሊሲዎችን በመከታተል እና ስልጣንን ያለአግባብ በመጠቀም ሊደርሱ የሚችሉትን በደሎች፣ የዘፈቀደ ባህሪ እና በመንግስት ህገ-ወጥ ወይም ኢ-ህገ መንግስታዊ ድርጊቶችን በመመርመር የዜጎችን መብት ማስጠበቅ አለበት::

ከነዚህ ዋና ዋና አላማዎች በመነሳት ምክር ቤት የመንግሥት ተቋማትን ዕቅዶች፣ የስራ አፈጻጸም፣ አደረጃጀት በመፈተሽ የሚጠበቅባቸው ኃላፊነት በአግባቡ እየተወጡ መሆኑን እና ውጤታማ መሆናቸውን የመከታተል ስራ ይሰራል::

የምክር ቤት ቁጥጥር በተግባር ውጤታማ እንዲሆን፣ ሥራ አስፈፃሚው ለክትትል እርምጃዎች ምላሽ መስጠት አለበት፣ ለምሳሌ የቃል ጥያቄዎች ሲጠየቁ፣ ወደ ምክር ቤት ሲጠሩ ወይም በምክር ቤት አካላት የውሳኔ ሃሳቦች ሲቀርቡ:: ተከታታይ የክትትል ጥሪቶች አስፈፃሚ አካላት የምክር ቤቱን ጥሪ ሰምተው እንደሆነ ለመከታተል፣ የመንግስትን ተጠያቂነት ለማጠናከር እና የመንግስታት ተገቢውን የእርምት እርምጃ የመውሰድ እድልን ይጨምራል:: ነገር ግን የመንግስት ምላሾችን ለመቆጣጠር እና ለመከታተል ተቋማዊ ዘዴዎች ከሌሉ ለግለሰብ የምክር ቤት ኮሚቴ አባላት የተተወ ስለሚሆን አስፈላጊ ስጋቶች ችላ ሊባሉ እና ኢፍትሃዊ ድርጊቶች ቁጥጥር ሳይደረግባቸው ሊቀጥሉ ይችላሉ::

አንድ ምክር ቤት ጠንካራ ቁጥጥር ለማድረግ ይረዳው ዘንድ ህጋዊ ስልጣን፣ አቅም (የገንዘብ፣ የቁሳቁስ እና የሰው ሃይል) እና ነፃነት ሊኖረው ይገባል:: ምክር ቤቶች በቁጥጥር ሂደት ሊጠቅሙባቸው የሚችላቸው ብዙ የቁጥጥር መሳሪያዎች ያሉ ቢሆኑም ዋና ዋናዎች የምክር ቤት ኮሚቴዎች፣ የፓርላማ ጥያቄዎች እና ጣልቃ ገብነቶች፣ የውይይት ሃሳብ እና ክርክሮች፣ የዜጎችን አቤቱታዎች መመልከት; እና የጸደቁ ህጎች ተፅእኖ ግምገማ ማድረግ የሚባሉት ናቸው::

#### 3.1.3.1 ዋና ዋና የቁጥጥር መሳርያዎች

#### ኮሚቴዎች

ኮሚቴዎች በዓለም ዙሪያ የሚገኙ የምክር ቤቶች ሁሉን አቀፍ የቁጥጥር መሣሪያ ናቸው:: የኮሚቴዎች የቁጥጥር ተግባር ማዕከላዊ ገጽታ በምርመራ ላይ ባለው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ከተለያዩ ግለሰቦች እና ድርጅቶች ማስረጃ የመፈለግ ስልጣናቸው ነው:: ብዙውን ጊዜ በአንድ የተወሰነ

የመንግስት ክፍል ላይ ስለሚያተኩሩ፣ የመንግስትን ፖሊሲ፣ ፋይናንስ እና አስተዳደርን ለመጠየቅ በጣም ሰፊ ፍቃድ ካላቸው እና በጥሩ ሁኔታ የሚተዳደሩ ከሆነ ኮሚቴዎች መንግስትን ተጠያቂ ለማድረግ በጣም ውጤታማ ዘዴ ሊሆን ይችላል፡፡

የምክር ቤት ኮሚቴዎች ካላቸው የእርስ በርስ ጥየቃ (Cross-Examination inquires) እና ምርመራዎችን (investigations) ማካሄድ እና ስነ-ምግባርን እና ታማኝነትን የማረጋገጥ ሃላፊነት አንጻር በፀረ-ሙስና ሥራ ውስጥ ከፍተኛ አቅም አላቸው፡፡

እንደ መንግስትን የመቆጣጠርያ መሳሪያነታቸው የኮሚቴዎች አቅም ያለው በመጠን እና በተደራሽነታቸው ላይ ነው፡፡ ኮሚቴዎች ጥቂት አባላት ያሉት ቡድን በዝርዝር እና በጊዜ ሂደት የተለያዩ ውስብስብ ጉዳዮችን እንዲመረምር ያስችላሉ፡፡ በተጨማሪም ኮሚቴዎች በብሔራዊ ጉዳዮች ላይ ሕዝቡ፣ የሲቪል ማህበረሰብ አካላት፣ ባለሙያዎች፣ ምሁራን እና የግሉ ሴክተር አባላት ሃሳባቸውን ለፓርላማ አባላት እንዲያደርሱ እድል ይሰጣሉ፡፡ ለምክር ቤት አባላትም ቢሆን ኮሚቴዎች በጣም አስፈላጊ ሲሆኑ አባላት የመንግስት ፖሊሲዎችን እና ፕሮግራሞችን ዝርዝር ሁኔታ ለመመርመር፣ በአንድ የተወሰነ ርዕስ ጉዳይ ላይ የተወሰነ እውቀት የሚያገኙበትን እድል ይፈጠራሉ፡፡ በተመሳሳይ ቀጣይነት ያለው የቁጥጥር ኮሚቴ ሥራ ተሳታፊ የምክር ቤት አባላት በኮሚቴው የትኩረት መስክ ውስጥ ባሉ ጉዳዮች እውቀት እንዲያገኙ እና ከክትትል ጋር በተያያዙ ሂደቶች እና ቴክኒኮች የተካኑ እንዲሆኑ እድል ይሰጣል፡፡ **ምርጥ ተሞክሮ**

በኬንያ ፓርላማ የጸረ ሙስና የተመረጠ ኮሚቴ የሙስናን መነሻ ምክነያት፣ገጽታ፣መጠንና ተጽዕኖ የማጥናትና የመመርመር ዋና ዋና የሙስና ፈጻሚዎችን እና ተጠቃሚዎችን እንዲለይና እርምጃ የሚወሰድበትን ምክረ ሃሳብ እንዲያቀርብ ሃላፊነት የተጠሰጠው ነበር፡፡ በዚህም መሰረት ከ 2 ዓመት ምርመራ በኃላ ሪፖርቱን ለፓርላማ ያቀረበ ሲሆን በውጤቱም እስከ 56 ፐርሰንት የሃገሪቱ የታክስ ገቢ በሙስና እንደሚመዘበር አረጋግጧል፡፡

## ጥያቄዎች እና ጣልቃገብነቶች

የፓርላማ ጥያቄዎች እና ጣልቃገብነቶች ከፀረ-ሙስና አንፃር በጣም መሠረታዊ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ የፓርላማ አባላት እውነታዎችን፣ መረጃዎችን እና ማስረጃዎችን በመሰበሰብ ጥያቄዎችን (የተፃፉ ወይም የቃል) በአስፈፃሚ ባለስልጣናት ላይ በማቅረብ ምላሽ ያሰጣሉ፡፡ በዚህ በኩል ከሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች መካካል- አዳዲስ ሂሳቦችን ወይም ማሻሻያዎችን ማዘጋጀት ፣ የተወሰኑ ባለስልጣናትን እስከ ክስ ወይም ከስልጣን እስከማስወገድ እና ጥያቄዎችን ማነሳሳት የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

**ምርጥ ተሞክሮ**

በእንግሊዝ ፓርላማው ሙስናና ብልሹ አሠራር መከላከያ ለሆነው የተጠያቂነት እና የግልጽነት አሠራር መሰርት ጥሏል። ለምሳሌ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1980ዎቹ መጨረሻ እንግሊዝ ከአሜሪካ ጋር በመተባበር በኢራቅ መሪ በሳዳም ሁሴን ላይ በወሰዱት ወታደራዊ ወረራ ድርጊቱ ከተፈጸመ ከአስር ዓመታት በኋላ ቀድሞ የነበሩት የሃገሪቱን ጠቅላይ ሚኒስትር ቶኒ ብሌርን በመጥራት እንግሊዝን በተሳሳተ መረጃ ወደ ጦርነት ከተዋል በሚል ለቀናት ሰፊ እና ጥልቅ ጥያቄ በማቅረብ እስከ ተጠያቂነት የሚያደርስ ስራ ሰርቷል።

## ክርክሮች

የፓርላማ ክርክሮች ከፀረ-ሙስና አንፃር ሌላው ጠቃሚ መሳሪያ ነው። በደንብ የተዘጋጁ የፓርላማ አባላት እና በተለይም የተቃዋሚ ፓርቲዎች መሪዎች በሙስና የተጠረጠሩ ባለስልጣናትን በአየር ላይ በሚደረጉ ክርክሮች ሊያሳጡ ይችላሉ።

**ምርጥ ተሞክሮ**

በአሜሪካም መሪዎች የመንግሥት ሥልጣናቸውን ለግል ጥቅማቸው አላግባብ ተገልግለዋል በሚል በአሜሪካ ፓርላማ (ኮንግረስ) በሕግ የተጠየቁበት አጋጣሚዎች አሉ። ከነዚህ መካከል ‹‹የወተርጌት ቅሌት›› ተብሎ በሚታወቀው ኩነት የዴሞክራቲክ ፓርቲን ስብሰባ በስውር ድምፅ መቅረጫ የመጥለፍ ተግባር ፈፅመዋል ወይም እንዲፈጸም አድርገዋል በሚል የወቅቱ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት የነበሩት ፕሬዝዳንት ኒክሰንን ኮንግረሱ የፕሬዝዳንትነት ዘመናቸው ሳይጨርሱ ከሥልጣን እንዲነሱ አድርጓል። የፕሬዝዳንት ቢል ኪልንተን እና የዶናልድ ትራምፕ ክሶች የተመረመሩትና ብዙ ሙግትና ክርክር የተደረገባቸው በኮንግረሱ ወይም በሃገሪቱ ፓርላማ ነው።

## የዜጎች አቤቱታ

የዜጎች አቤቱታዎች ሙስናን ለመዋጋት በጣም ኃይለኛ መሳሪያ ሁነው ሊያገለግሉ ይችላሉ። ለዚህም ዜጎች በቀላሉ ሊያገኟቸው የሚችሉ ግልጽ መመሪያዎች እና ሂደቶች ሲኖሩ የዜጎች አቤቱታዎች ሙስናን በመዋጋት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ።

የፓርላማ አባላት የቁጥጥር ሥልጣናቸውን በብቃት እንዲጠቀሙ ለማበረታታት የፓርላማ ተቋማዊ እና የሕግ ማዕቀፍ አስፈላጊ ነው። ይህ ማዕቀፍ የቁጥጥር መሳሪያዎችን ከማቅረብ በተጨማሪ የፓርላማ ተቋሙን ነፃነት እና የፓርላማ አባላትን ያለመከሰስ መብት ማስጠበቅ አለበት። እነዚህ ጥበቃዎች የፓርላማ አባላት በራሳቸው ላይ የበቀል እርምጃ ሳይወሰድባቸው

አስፈፃሚውን እንዲቃወሙ ያስችላቸዋል። በተጨማሪም የፓርላማው የህግ ማዕቀፍ ለአባላት እንደ መረጃ የማግኘት፣ ሰነዶችን የመጠየቅ እና የመንግስት እምብርት ድረስ የሚዘልቁ ጥያቄዎችን የማንሳት አቅም የሚሰጡ አይነት ተያያዥ መብቶችን ማካተት አለበት።

### 3.1.3.2 ሙስናን ለመከላከል የተቋቋሙ ተቋማትን መከታተል

**ማነቃቅያ ጥያቄ**

በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤቶች፤ የሙስና ወንጀልን ለመከላከል የተለየ የፀረ-ሙስና ተቋም ማቋቋም አስፈላጊ አይደለም የሚሉ ሐሳቦች ይሰነዘራሉ። ይህንን ተቋም ከመመሥረት ይልቅ የፖሊስ እና የፍትሕ ሥርዓታችን በማጠናከር እና አቅማቸውን በማሳደግ ሙስና ወንጀሎችን መከላከል በብዙ መንገድ አዋጭነው በማለት ይከራከራሉ። በዚህ ላይ ያላችሁን አስተያየት ግለጹ።

በአሁኑ ጊዜ ሀገራችንን ጨምሮ በብዙ የአፍሪካ ሀገራት ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል ሥልጣን የተሰጣቸው የፀረ-ሙስና ተቋማት ተቋቁመዋል። ተቋሞቹን በማደራጀትና ለነዚህ ተቋማት ምቹ የሕግ ሥርዓት በመዘርጋት ረገድ ምክርቤቶች የላቀ ሚና ተጫውተዋል።

የፀረ-ሙስና ተቋም በማቋቋም እና የወጡት ሕጎች በአግባቡ ተግባራዊ መደረጋቸውን መከታተል የሚቻለው ወንጀሉን መከላከል ላይ የሚሰራ ራሱን የቻለ ተቋም በማቋቋም ነው። በአሁኑ ወቅት በብዙ አዳጊ ሀገራት የፀረ-ሙስና ተቋማት ተመሥርተዋል። የፀረ-ሙስና ተቋማት ውጤታማ እንዲሆኑ፣ ራሳቸው ለሙስና እና ብልሹ አሠራር ተጋላጭ እንዳይሆኑ እንዲሁም በአስፈጻሚው አካል ተፅእኖ ስር እንዳይወድቁ ፓርላማው በቅርበት ሊደግፍ እና ሊከታተል ይገባል። ፀረሙስና ተቋም በብቁ ሙያተኞች የተደራጀ፣ ነፃና ገለልተኛ እንዲሆን እና ሙስና የፈጸመ ማንኛውም አካል ያለ ምንም ዓይነት ልዩነት ለሕግ የሚያቀርብ በማድረግ ረገድ የተወካዮች ምክርቤት ሚና ከፍተኛ ነው፡

### 3.1.3.3. የመንግሥት ተቋማት ሙስናን ለመከላከል የሚያስችሉ ስርአቶች መዘርጋታቸውን መከታተል

**ተግባር መወያያ ጥያቄ**

ምንም እንኳ ሙስናና ብልሹ አሰራር በተለይ በማደግ ላይ ባለ ሃገራት ላየ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ከፍ ያለ ቢሆንም ከዚህ ጋር የሚመጣጠን የመከላከል ሰራ እንዳልተሰራ ይገለጻል። ለዚህ ደግሞ በነዚህ ሃገራት ያለው ደካማ የሆነ የአስተዳደር ስርዓት እና የተቋማት በቅጡ አለመገንባት እንደ ዋና ምክነያት ይጠቀሳል።

በዚህ ረገድ በምክርቤቶች በመንግሥት ተቋማት ሊተገበሩ የሚገባቸው ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ዋና ዋና ስራዎች ዘርዝሩ፡፡

ሙስናን በተቋም ደረጃ መከላከል ወንጀሉን በመቀነስ ረገድ ከፍተኛ ፋይዳ አለው፡፡ በዚህ ረገድ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ከተሰጠውና ከሚጠበቅበት ኃላፊነቶች መካከል አንዱ በመንግሥት ተቋማት ውስጥ የግልጽነትና የተጠያቂነት አሠራር እንዲጠናከር በማድረግ ለሙስናና ብልሹ አሠራር ክፍተት የማይኖርበትን ሥርዓት መፍጠር ነው፡፡

ሙስና የሚፈጸመው የስራ ኃላፊንም ሆነ ባለሙያን ተጠያቂ የሚያደርግ አሠራር ሲዳከም ነው፡፡ የተወካዮች ምክርቤት በተቋማት የሚፈጸሙ ብልሹ አሠራር መረጃዎች የሚያገኙበትን መንገዶች ማጠናከር አለበት፡፡ እነዚህ መረጃዎችን በመተንተንና በማመሳከር ተቋማት ላይ የማስተካከያ እርምጃዎች መውሰድ ወይም እንዲወሰድ ማድረግ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡ የመንግሥት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጣቸውን በማሻሻል ሙስናና ብልሹ አሠራርን እንዲከላከሉ የተወካዮች ምክርቤት ማገዝ አለበት፡፡ የግልጽነትና የተጠያቂነት አሠራሮች እንዲያጠናክሩ አቅጣጫም ያመለክታል፡፡

### 3.1.3.4. የሥነምግባር ግንባታ ስራዎችን መከታተል

**ተግባር መወያያ ጥያቄዎች**

| |
|---|
| ለሙስናና ብልሹ አሠራር መስፋፋት አንዱ ምክንያት የዜጎች ሥነምግባር መዳከም እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይህን ለመቀረፍ ደግሞ እንደ ህዝብ ተወካይነታቸው ምክርቤቶች ሰፊ ስራ እንዲሰሩ ይጠበቃል፡፡ በተቃራኒው አንድ አንድ የምክር ቤት አባላት በሙስናና ብልሹ አሰራር ውስጥ ሲገቡ ይስተዋላል፡፡ |

ከዚህ በመነሳት

i. ከአንድ የምክር ቤት አባል የመልካም ስነ መግባር ምሳሌ ለመሆን ምን ምን ተግባራት ይጠበቃሉ?

ii. የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት በሀገር ደረጃ በሥነምግባር ግንባታ ዙሪያ ሊጫወት የሚገባውን ሚና እየዘረዘራችሁ ተወያዩበት፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት በሀገር ደረጃ የሚካሄዱ የሥነምግባር ግንባታ ስራዎችን ደረጃ እና ሁኔታ የማወቅ ኃላፊነትን ሊወጣ ይገባል፡፡ በዜጎች የሥነምግባር ግንባታ ለውጥ የሚያመጡ ፖሊሲና ስትራጂዎች እንዲነደፉ የማድረግ እና ተግባራዊ መሆናቸውን የመከታተልም ኃላፊነት አለበት፡፡

በሀገር አቀፍ ደራጃ የሥነምግባር ግንባታ ከፍተኛ ኃላፊነት ካላቸው ፀረሙስና ተቋማት፣ ለምሳሌ ከትምህርት ተቋማት፣ የሃይማኖት ድርጅቶች፣ ሚዲያ እንዲሁም ሲቪክ ማኅበራት በቅርበት፣ በትብብርና በቅንጅት የሚያሰሩ ሥልቶችን በመንደፍ እና የማስተባበር ሚና ሊወጣ ይገባል፡፡ በይበልጥ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሥነምግባር ግንባታ በተጠናከረ ሁኔታ መሰራቱን መከታተል እና መደገፍ ሌላው ኃላፊነቱ ነው፡፡

የሥነ ምግባር ደንቦች ፓርላማዎች እና የፓርላማ አባላት ውጤታማ የስነምግባር ስርዓቶችን ለመመስረት የሚሞክሩበት አንዱ መንገድ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የሕግ አውጭ የሥነ ምግባር ደንብ ተቀባይነት ያለው ባህሪ ነው ተብሎ የሚታሰበውን እና ያልሆነውን በመለየት የሕግ አውጪዎችን ባህሪ የሚቆጣጠር መደበኛ ሰነድ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር፣ በፓርላማ አባላት የባህሪ ተገቢነት፣ ትክክለኛነት፣ ግልጽነት እና ታማኝነት ላይ ትልቅ ትኩረት የሚሰጥ የፖለቲካ ባህልን ለማስተዋወቅ ያለመ ሰነድ ነው፡፡

የህግ አውጭው የስነ ምግባር ደንቦች ሊከሰት የሚችልን የጥቅም ግጭት ለማስቀረት ሲባል የሕግ አውጭው አባላት የታክስ ተመላሾችን፣ የቤተሰብ ገቢ ምንጮችን፣ ኢንቨስትመንቶችን፣ የአጋር ወይም የአክሲዮን ባለቤት የንግድ ሥራ የገቢ ምንጮችን፣ ያለባቸውን ዕዳ ፣ የሊዝ ውል እና ሌሎች ከሕዝብ አካላት ጋር ያሉ ግንኙነቶች፣ ክፍያዎች እና ክብር፣ ሙያዊ ወይም የሥራ ፈቃድ፣ በፋይናንስ ተቋማት ያለ ተቀማጭ ገንዘብ ፣ የግል ቀጣሪነት ወይም የግል ሥራ ሁኔታ፣ የቅርብ የቤተሰብ አባላት ስም እና የትዳር ጓደኛ እና ልጆች የገንዘብ ፍላጎቶች የመሳሰሉትን የጥቅም ግጭት ጉዳዮች በተመለከተ ፍላጎታቸውን እንዲገልጹ ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የስነምግባር ደንቦች አንዳንድ ተጨማሪ ገደቦችን በአባላት ላይ ሊጥሉ ይችላሉ፡፡. አንዳንዶቹ ህግ አውጪው በስልጣን ላይ እያለ የሚፈጸሙ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ የህግ አውጭው በስልጣን ላይ ከቆዩ በኋላም ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡ ከሚከለከሉ ተግባራት መካካል- የግል ጥቅምን ለማግኘት የህዝብ ስልጣንን መጠቀም ፣ ኦፊሴላዊ ተግባራት ላይ ተፅእኖ ለማድረግ ጥቅማጥቅሞችን መስጠት ፣ ሚስጥራዊ የመንግስት መረጃን መጠቀም ፣ የባለስልጣኖች ወይም የሠራተኞች ከተወሰነ ዋጋ በላይ ስጦታ መቀበል ፣ በመንግስት ባለስልጣናት ወይም ሰራተኞች ክፍያዎችን ወይም ክብር ስጦታ መቀበል ፣ በመንግስት ባለስልጣናት ወይም ሰራተኞች የግል ደንበኞችን መወከል፣ ፋይናንስ የጥቅም ግጭቶች፣ ዘመድ አዝማድ ጥቅቅሞሽ፣ በመንግስት ባለስልጣናት ወይም ሰራተኞች ከመደበኛ ስራ ውጭ መቀጠር ወይም የንግድ እንቅስቃሴዎች መግባት እና የመንግስት ላልሆኑ አገልግሎቶች የጉዞ ክፍያዎች መጠየቅ- የሚሉት ይገኙበታል፡፡

የስነ ምግባር ደንቦች መኖር ሙስናን ለመከላከል እንደ መነሻ ሊያገለግል ቢችልም ውጤታማ ለመሆን ግን ማዕቀቦች፣ ተቋማዊነት፣ የባህል አመለካከቶች እና ስልጠናዎችን ጨምሮ በርካታ ምክንያቶች አስተዋፅዖ ያደርጋሉ።

### 3.1. 3.5 ዓለማቀፍ እና አህጉር አቀፍ የፀረ-ሙስና ትብብር እንዲጠናከር ክትትል ማድረግ

**አስረጅ ናሙና**

| |
|---|
| በአንድ ወቅት የአንዱ ሀገር ምክርቤት ለውሳኔ የቀረበ ዓለማቀፍ የፀረ-ሙስና ስምምነትን ውድቅ አደረገ። ለዚህም እንደ ዋና ምክንያት የቀረበው ከዚህ በፊት ያጸደቅናቸው ስምምነቶች ሙስናን ለመከላከል እንብዛም አላገዙንም ችግሩም እጨመረ እንጅ እቀነሰ አልመጣም የሚል ነው። መጀመሪያ ከዚህ በፊት ተቀብለን ያጸደቅናቸውን ስምምነቶች ውጤታማነት እንገምግም የሚል ሐሳብም ተነሳ። ስምምነቱን ለምክርቤት ያቀረበው አካል የስምምነቱ መጽደቅ የሚያመጣው የዲፕሎማሲ ፋይዳ ስላለ ይጽደቅ በሚል ተከራከረ። ነገር ግን ምክር ቤቱ ውሳኔውን ለሌላ ጊዜ አስተላለፈው። |

ከዚህ በመነሳት የትኛው ሐሳብን ትደግፋላችሁ? ምንስ መደረግ አለበት? ለምን?

ሙስና የሚያስከትለው ጉዳት በአንድ ሀገር ተወስኖ የሚቀር አይደለም። ወንጀሉ በዓለማቀፍ ደረጃ የሚያደርሰው ጉዳትም ከፍተኛ ነው። ለዚህም እንደ ምሳሌ ከሚጠቀሱት የሙስና ተግባራት መካከል ሕገወጥ የገንዘብና የሰዎች ዝውውርና ሽብርተኛነት ናቸው።

በዚህ የተነሳም ከጊዜ ወደ ጊዜ ሙስናን የመከላከል ዓለማቀፍ የትብብርና የመደጋገፍ ስራዎች እያደጉ በመሄድ ላይ ናቸው። በዚህ ረገድ ሀገራችን ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውና ያፀደቀቻቸው የተባበሩት መንግሥታት የፀረ-ሙስና ስምምነት (2003 እ.አ.አ.) እና የአፍሪካ ኅብረት የሙስና መከላከያና መዋጊያ ስምምነት (2005 እ.አ.አ.) በአብነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። ሙስናና ብልሹ አሠራርን መከላከል ቀዳሚ ትኩረታቸውና አጀንዳቸው አድርገው ከሚሰሩ የዓለም ባንክ እና ትራንስፓራንሲ ኢንተርናሽናል ከመሳሰሉ ድርጅቶች የሚደረጉ የትብብርና የመደጋገፍ ስራዎችን መከታተልና መደገፍ ሌላው የምክርቤት ተግባር ነው።

### 3.1.4. የበጀት አመዳደብ

በአብዛኞቹ ሃገራት ያሉ ም/ቤቶች ዓመታዊ የመንግስት በጀት የማጽደቅና አወጣጡንም አመቱን ሙሉ የመቆጣጠር ሃላፊነት አላቸው።ይሁን እንጅ በብዙ የአለማችን ሃገራት በተላይ ደግሞ በማደግ ላይ ባሉ ሃገራት ያሉ ም/ቤቶች የመንግስትን ፋይናንስ አጠቃቀም እና ትግበራ የመቆጣጠር ስራ እዚህ ግባ የሚባል እንዳልሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። ይሁን እንጅ ምንም

እንኳ በመደበኛ ሁኔታ በጀትን የመከለስ ልምዱ ደካማ ቢሆንም በአንዳንድ ሃገራት ያሉ ም/ቤቶች የበጀት ሂደቱ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳርፉበት ዘዴ ቀይሰዋል፡፡ ለምሳሌ በጋና የፋይናንስ ኮሚቴ ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በጀት ከመጽደቁ በፊት ምክክር የሚደርግበትን አሰራር የዘረጋ ሲሆን የህዝብ ቀጥጥር ኮሚቴ በበኩሉ የየሩብ ዓመቱን የበጀት አፈጻጸም ሪፓርት የሚጠይቅበት ሂደት አለው፡፡

ዓመታዊ የሀገር በጀት ከሀገር ውስጥ ከሚሰበሰብ ገንዘብና ከውጪ በሚገኝ ብድርና እርዳታ የሚሸፈን እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በነዚህ የበጀት ምንጮች አማካይነት የሚገኝ ሀብትን በአግባቡ በመመደብ የሙስና መከላከል ሚናውን ም/ቤቱ መወጣት አለበት፡፡ የበጀት አመዳደብ ሂደት የመንግስት ወጪዎች የሚወሰንበት እና የሚመደብበት ስርዐት ነው፡፡ የበጀት ዕቅድ የመስራት፤ ተግባር ላይ የማዋልና የመቆጣጠር ተግባራት የስርዐቱ አካላት ናቸው፡፡ እነዚህ ሂደቶች በአግባቡና ፍትሀዊ በሆነ መንገድ የማይሄዱ ከሆነ ለሙስና ተጋላጭነታቸው አጠራጣሪ አይሆንም፡፡ስለሆነም ከዕቅድ ጀምሮ ያሉ ተግባራት በባለድርሻ አካላት ተሳትፎ መዳበርና መስተካከል ስላለበት የህዝብ ተወካዮች ምክርቤት ይህ ሂደት በአግባቡ መከናወኑን ክትትል ያደርጋል፡፡

### 3.1.4.1 ዓመታዊ የበጀት አመዳደብ ሂደት

**ማነቃቅያ ጥያቄ**

| |
|---|
| ለሙስና በር የሚከፍቱ የበጀት አመዳደብ አሰራሮችን ዘርዝሩ ፡፡ |

የመንግስት አስፈፀሚው አካል የሚጠይቀውን በጀት የሚያፀድቀው የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ነው፡፡ በዝርዝር ተዘጋጅቶ የመጣው በጀት ከዓላማውና ዝርዝር ተግባራቱ ጋር መጣጣም ይገባዋል፡፡ በአብዛኛው የታቀዱት ተግባራት ወቅታዊ አለመሆን፣ ተግባራቱ ከተመደበላቸው በጀት ጋር ያለመመጣጠን እና የበጀት አለቃቀቅ ሂደቱ ጤናማ ያለ መሆን ይስተዋላሉ፡፡ ምክርቤቱ በጀቱን ከማጽደቁ በፊት እነዚህን አካሄዶች መፈተሽ አለበት፡፡

ያለፈውን ዓመት የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት አንኳር ጉዳዮችን ማጤን በበጀት አፀዳደቅ ሂደት የመጀመሪያው ተግባር ነው፡፡ ከዚህ ሪፖርት ላይ የተከናወኑ ሥራዎችና የወጣው ወጪ ንጽጽርን ማየት ይቻላል፡፡ በአነስተኛ ወጪ የታቀዱት ሥራዎች እንዲከናወኑ ይጠበቃል፡፡ ሆኖም ግን በብልሹ አሰራሮችና በሙስና ሳቢያ የወጪው መጠን ከፍተኛ የሚሆንባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው፡፡ ስለዚህ እንደነዚህ ዓይነት ሁኔታዎች እንዳይደገሙ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ክፍተት የፈጠሩ ቦታዎችን በመለየት ማስተካከያ እንዲደረግ ም/ቤቱ ማድረግ አለበት፡፡

በተቋማት የሚታቀዱ ተግባራት ብዙ ቢሆኑም የሀገር የበጀት አቅም ውስን ስለሆነ የተወሰኑ ተግባራትን ለመሰረዝ ም/ቤቱ ሊገደድ የሚችልባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው፡፡ አንዳንድ የተቋማት መሪዎች ከም/ቤቱ አባላት ጋር ያላቸውን ቅርበት በመጠቀም የሚፈልጉትን ያህል በጀት ለማግኘት እንቅስቃሴዎችን ያደርጋሉ፡፡ የም/ቤቱ አባላት የበጀት ምደባ በሚያደርጉባቸው ጊዜያት ሁሉ ፍትሐዊነትን መከተል ይገባቸዋል፡፡ ውስኑን በጀት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት በመመደብ የሙስና መከላከል ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

በአጠቃላይ  የበጀት አመዳደብ ሂደትን ወስብስብ የሆነና አባላትም የበጀት ቁጥጥርን ለማድረግ በቂ የሆነ ቴክኒካል እውቀት ስለማይኖራቸው የምክር ቤት ቁጥጥር ኮሚቴ መመስረት እጅግ አጋዥ ይሆናል፡፡ ይህ ኮሚቴ አስፈላጊው የቴክኒክ፣ የሰው እና የገንዘብ ሃብት እንዲሁም በቂ እና ከስራ አስፈጻሚው ነጻ የሆነ ስልጣን ከተሰጣቸው የም/ቤቱን የበጀት ቁጥጥር ክህሎት በማጠናከር ረገድ ጉልህ ሚና መጫወት ይችላሉ፡፡

በሌላ በኩል የዋና ኦዲት ተቋማት እና እንባ ጠባቂ የመንግስት ተቋማት አሰራር፣ ትግበራ እና ወጭን በጥንቃቄ ለመቆጣጠር የሚረዱ ቁልፍ ተቋማት ናቸው፡፡ ስለሆነም በነዚህ ተቋማት እና በፓርላማ ኮሚቴዎች መካከል የሚኖረው ግንኙነት በመንግስት የፋይናንስ አሰራር ላይ ውጤታማ የሆነ ቁጥጥር ለማረጋገጥ ወሳኝ ጥቅም አለው፡፡

**ምርጥ ተሞክሮ**

የኡጋንዳን ም/ቤት እ.አ.አ በ 2001  በአጸደቀው የበጀት አዋጅ መሰረት ነጻ የፓርላማ በጀት ቢሮ መስረቷል፡፡ ይህ ቢሮ የበጀት ትርጉም እና ኢኮኖሚ መረጃ ትንተና የቴክኒክ አቅም በፓርላማው ውስጥ እንዲፈጠር የሚሰራ ሲሆን በተጨማሪም ተጨባጭ፣ጊዜውን የጠበቀና ነጻ ትንተናና ሪፓርት በቁልፍ ከበጀት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ያቀርባል፡፡

### 3.1.4.2 የብድር ስምምነትን የማፅደቅ ሂደት

መንግስት ለተለያዩ ልማት ስራዎች ድጎማ ከተለያዩ አህጉራዊ እና ዓለምአቀፍ ድርጅቶች፣ ባንኮች እና ሃገራት መጠናቸው ብዙ የሆነ ብዙ ዓይነት የብድር እና የገንዘብ ድጋፍ ስምምነቶችን ይፈፅማል፡፡ ብዙዎቹ በዚህ መንገድ የሚገኝ ገንዘብ ምንጮች በመጨረሻ የሚፀድቁት በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ነው፡፡ እነዚህ የብድርና የድጋፍ ስምምነቶች እጅግ ብዙ መጠን ያላቸው ገንዘቦች ብቻ ሳይሆኑ ከፍተኛ ወለድ የሚከፈልባቸውም ጭምር ናቸው፡፡

የተወካዮች ምክርቤት የዚህ ዓይነት ስምምነቶች በሃገር ላይ እና አልፎ ተርፎ በወደፊት ትውልድ ላይ ሊኖራቸው የሚችለውን አንደምታ በሚገባ ትኩረት ሊሰጣቸው እና ጥንቃቄ ሊያደረገባቸው ይገባል፡፡ በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ከፍተኛ የሃገር መሪዎች እና

ተባባሪዎቻቸው ከሚወቀሱባቸው ድርጊቶች መካከል እና ለሙስና መፈፀም መንገድ ከሚያደርጉባቸው ጉዳዮች አንዱ በሃገር ስም የሚፈፀሙ የገንዘብ ብድርና ድጋፍ ስምምነቶች ናቸው፡፡ በዚህ መንገድ የሚገኝ ገንዘብ በህገወጥ መንገድ ወደ ውጪ ሃገር ያሸሻሉ፡፡ በብድር ስምምነት የሚፈፀሙ ገንዘብ ከፊሉ በውጪ ሃገር ባንኮች እንደሚሸሸጉ የተለያየ ጥናቶችእና በዘርፉ የሚሰሩ ዓለም አቀፍ ተቋማት ያረጋግጣሉ፡፡

በዚህ ረገድ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የገንዘብ ድጋፎች እና ስምምንቶች ከጥቅም ግጭት እና የሙስና ተግባራት የፀዱ መሆኑቸውን እና የገንዘብ ስምምነቶች እና የብድሮቹን አስፈላጊነት በሚገባ መረዳት፣ ማጤን እና መመርመር የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ከፍተኛ ኃላፊነት ነው፡፡

ምክር ቤቱ የግልፅነትና የተጠያቂነት አሰራር የማስፈን የላቀ ሚና መጫወት እንዳለበት ይታመናል፡፡ በዚህ ረገድ በሚፈፀሙ የድጋፍና ብድር ስምምነቶች ላይ ወንጀሉ ተፈፅሞ ሲገኝም ጉዳዩ በአስቸኳይ እንዲጣራ፣ እንዲመረመር እና ወደ የሚመለከተው ፍትህ አካል እንዲቀርብ የማድረግ ሚናውን መወጣትም ይጠበቅበታል፡፡

### 3.1.5. የሚሾሙ የሥራ አስፈፃሚ አባላትን ማጽደቅ

*ማነቃቅያ ጥያቄ*

| |
|---|
| የሚሾሙ የመንግስት ሥራ አስፈፃሚ አባላት የሚለውን ሀረግ አብራሩ፡፡ |

በከፍተኛ ኃላፊነት ላይ የሚመደቡ እጩዎችን ሹመት የሚያፀድቀው የተወካዮች ም/ቤት ነው፡፡ እጩው ለታጨበት ቦታ ብቁ ነው ተብሎ የሚታመነው በሥነምግባሩ ምስጉን፣ ሥራውን ለመሥራት ቁርጠኝነት ያለውና ለቦታው የሚመጥን የትምህርት ዝግጅት ያለው መሆኑን ም/ቤቱ ሲያረጋግጥ ነው፡፡ እነዚህን መስፈርቶች ባላሟላበት ሁኔታ የሚቀርብ እጩ ብቃቱ አጠያያቂ ነው፡፡ የተጣለበትን ኃላፊነትም ለመወጣት ይቸገራል፡፡ መስፈርቱን የሚያሟሉ እጩዎችን ብቻ በማጽደቅ ቦታውን እንዲይዙ በማድረግ የሙስና መከላከል ሚናውን ም/ቤቱ እንዲወጣ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ሎርድ ኖላን በ1999 እ.አ.አ የመንግስት ቢሮ ሃላፊዎች ሊከተሏቸው የሚገቡ ብሎ ያዘጋጃቸውን ሰባቱ የህዝባዊ ስራ መርሆዎችን መመልከት ጠቃሚ ይሆናል፡፡ እነዚህ መርሆዎች በኛም አገር ምክር ቤቱ የስራ አስፈጻሚ አካለትን ሹመት በሚመለከትበት ጊዜ ሊጠቀምባቸው የሚችሉ በመሆናችው ዘርዝር ተደርገው ቀርበዋል፡፡

***ከራስ ወዳድነት ነፃ የሆነ*** — የመንግስት መስሪያ ቤት ሃላፊዎች ከህዝብ ጥቅም አንፃር ብቻ ውሳኔዎችን መወሰን አለባቸው፡፡ ለራሳቸው፣ ለቤተሰባቸው ወይም ለጓደኞቻቸው የገንዘብ ወይም ሌሎች ቁሳዊ ጥቅሞችን ለማግኘት ይህን ማድረግ የለባቸውም፡፡

***ታማኝነት*** — *የመንግስት መስሪያ ቤት ሃላፊዎች እራሳቸውን በማንኛውም የገንዘብም ሆነ ሌላ ግዴታ ውስጥ በመጣል ለውጭ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ኦፊሴላዊ ተግባራቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ ተጽእኖ ስር ሊያድሩ አይገባም፡፡*

**ተጨበጭ እና እውነተኛ** —*የመንግስት መስሪያ ቤት ሃላፊዎች የህዝብን ስራ ሲያካሂዱ፣ ምደባዎችን ሲያደረጉ፣ ኮንትራቶችን ሲሰጡ ፣ ወይም ግለሰቦችን ለሽልማት እና ጥቅማጥቅሞች ሲጠቁሙ በብቃትና ችሎታ ላይ ተንተርሰው ምርጫ ማድረግ አለባቸው፡፡*

***ተጠያቂነት*** — *የመንግስት መስሪያ ቤት ሃላፊዎች ለውሳኔያቸው እና ለድርጊታቸው ተጠያቂ እና እራሳቸውን ለቢሮአቸው ለሚስማማው ማንኛውም ምርመራ ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡*

***ክፍትነት*** — *የመንግስት መስሪያ ቤት ሃላፊዎች ስለሚወስዷቸው ውሳኔዎች እና እርምጃዎች በተቻለ መጠን ክፍት መሆን አለባቸው፡፡ ለውሳኔያቸው ምክንያቶችን መስጠት እና መረጃን መገደብ ያለባቸው ሰፊው የህዝብ ጥቅም በግልፅ ሲጠይቅ ብቻ ነው፡፡*

**ሐቀኝነት** — *የመንግስት መስሪያ ቤት ሃላፊዎች ከህዝባዊ ተግባራቸው ጋር በተያያዘ ማንኛውንም የግል ጥቅም የማወጅ እና የህዝብን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ የሚነሱ ግጭቶችን ለመፍታት እርምጃዎችን የመውሰድ ግዴታ አለባቸው፡፡*

***አመራር*** — *የመንግስት መስሪያ ቤት ሃላፊዎች እነዚህን መርሆዎች በአመራር እና ምሳሌ በመሆን ማስተዋወቅ እና መደገፍ እንዲሁም ሙስናና ብልሹ አሠራር የፈጸሙ አመራሮችን ከያዙት ቦታ እንዲነሱ እና በሕግ እንዲጠየቁ የማድረግ አለባቸው፡፡*

## 3.2 ክፍል ሁለት- የምክርቤት ዘርፍ ሙስናና ብልሹ አሠራርን የመከላከል ሚናቸውን ማጎልበቻ መንገዶች

### 3.2.1. ሙስናን በመከላከል ዙሪያ የምክርቤት አባላትን ግንዛቤ ማሳደግ

**አስረጅ ናሙና**

በምክር ቤት የተሾሙ የአንድ መሥሪያ ቤት ኃላፊ እናታቸው በማረፋቸው መ/ቤቱ ሙሉ በሙሉ አገልግሎት አቋርጦ ሁሉም ሰራተኛ የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ተገኝቷል፡፡ በቀብር ሥነ ሥርዓቱ ላይ ሚቿ የድርጅቱ የፋይናንስ ዳይሬክተሩም አክስት፣ እንዲሁም የተሽከርካሪ ስምሪት ክፍል ኃላፊ የቅርብ ዘመድ መሆናቸው ታወቀ፡፡ ይህን ሁኔታ ያወቁ የተቋሙ ሰራተኞች ጉዳይ በምሥጢር ለተወካዮች ምክርቤት ጥቆማ አቀረቡ፡፡ ጉዳዩንም ሲከታተል ከቆየ በኋላ ምክርቤቱ ምላሹን ለተቋሙና ጥቆማ ላቀረቡት በደብዳቤ አሳወቀ፡፡ ከምክርቤት ለድርጅቱ

የተላከው ደብዳቤ ድርጅቱ በጉዳዩ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጥ የሚጠይቅ ነበር፡፡ የድርጅቱ ኃላፊ ችግሩን በአፋጣኝ አስተካክላለሁ በሚል ምላሽ ለም/ቤቱ ላኩ፡፡

i. የም/ቤቱን ተግባር እንዴት ትመለከቱታላችሁ? ምንስ ማድረግ ነበረበት? ምክርቤቱ ጉዳዩን ያስተናገደበት መንገድ ትክክል ነበረ ወይ?

ii. ይህ ዓይነት አሠራር ከምን የመነጨ ሊሆን ይችላል?

ሙስናና ብልሹ አሠራርን በመከላከል ያለው ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት ምክርቤቱ የተለያዩ ስራዎች መሥራት ይጠይቃል፡፡ በዚህ ረገድ የምክር ቤቱ ቀዳሚ ስራ የምክርቤት አባላትን በሙስናና ብልሹ አሠራር መከላከል ዙሪያ ተከታታይነት ያለውን የአቅም ግንባታ እና የግንዛቤ ማጎልበቻ ስራዎችን መሥራት ነው፡፡

ተወካዮች ምክርቤት አባላት መልካም ሥነምግባርን፣ የሙስና ባሕርያትን፣ ፀረሙስና ሕጎችን እና አህጉራዊና ዓለማቀፋዊ የፀረ-ሙስና ስምምነቶችን እንዲያውቁ የማድረግ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡ ያዳበሩትን ዕውቀት ወደ ወከላቸው ማኅበረሰብ በማዳረስ የዜጎችን ሙስናን የመከላከል አቅም የማሳደግ ስራ እንዲሰሩ የማነቃቃት ስራ መሥራት ተገቢ ነው፡፡

### 3.2.2 ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነፃ መሆን

የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ባልዳበረበት እና ሁሉንም የመንግሥት ሥልጣን አንድ አካል በተቆጣጠረበት ሀገር ውስጥ የሚገኙ ምክርቤቶች ሙስናን የመዋጋት ሚና ዝቅተኛ ነው፡፡ ለዚህ አንዱ ምክንያት የምክርቤቱ አባላት ሥልጣን በያዘው ፓርቲ የተሞላ መሆኑ ነው፡፡ የፓርቲ ወገንተኝነት ሰፍኖ በሚገኝበት ምክር ቤት በአስፈጻሚው እና በፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች የሚፈጸሙ ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል ቁርጠኝነት ሲያንሰው ይስተዋላል፡፡ ምክር ቤት ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል ከፖለቲካ ፓርቲም ሆነ ከማንኛውም አካል ተፅዕኖ እና ጣልቃ ገብነት ነፃ በመሆን በሕግ እና በሕሊና መመራት እና መሥራት ይጠበቅበታል፡፡

### 3.2.3. የዴሞክራሲ ሥርዓት እና ባህል እንዲጎለብት የላቀ ሚና መወጣት

**ማነቃቅያ ጥያቄ**

የዴሞክራሲ ስርዓት መኖር ለጸረ ሙስናና ብልሹ አሰራር ትግሉ ያለው አስተዋጾ እንዴት ይገለጻል?

ዲሞክራሲ ሙስናና እና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚያስችል ጠቃሚ ሥርዓት ነው፡፡ በተለያዩ አካላት የሚፈጸሙ ሙስናና ኢ-ሥነምግባራዊ ተግባራትን ተጠያቂ በማድረግ የዴሞክራሲ ሥርዓት መጎልበት ዓይነተኛ መሣሪያ ነው፡፡

ሙስና እና ብልሹ አሠራርን በመከላከል ረገድ ከፍተኛ ፋይዳ ካላቸው የዴሞክራሲ እሴቶች መካከል ግልጽነት፣ ተጠያቂነት እና አሳታፊነት ቀዳሚ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ እነዚህ እሴቶች በአግባቡ ባልዳበሩበት ሥርዓት ሙስናና ብልሹ አሠራሮች ተንሰራፍተው ይገኛሉ፡፡ በዚህ ረገድ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት የዴሞክራሲ ሥርዓትን በማጠናከር የጎላ ሚና ሊጫወት ይገባል፡፡

ምክር ቤቶች የዲሞክራሲ የማዕዘን ድንጋይ ናቸው፡፡ ሕገ መንግሥታዊ ተግባራቸውን ለመወጣት ሥልጣን ሊሰጣቸውና አስፈላጊው መንገድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በስራቸው ውስጥ ዋና ዲሞክራሲያዊ እሴቶችን ማካተት አለባቸው፡፡ ዲሞክራሲ በአንድ ሃገር ውስጥ ሥር እንዲሰፍን እና መልካም አስተዳደር እንዲያብብ የምክር ቤት አባላት ተቀዳሚ ተግባር ህዝቡ ምን እንደሚፈልግ እና አንገብጋቢ ጉዳዮቻቸው ምን እንደሆኑ ማወቅ ሲሆን ፓርላማው የሚያወጣው ህግ እነዚያን ወሳኝ ጉዳዮች መዳሰሳቸውን ማረጋገጥ መቻል አለበት፡፡

ምክር ቤት ዜጎች በምርጫ በንቃት በመሳተፍ፣ ለሕገ መንግሥት ማሻሻያ እና ለመንግሥት የፖሊሲ አጀንዳ አስተዋፅዖ በማድረግ በአስተዳደር ሂደቶች ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ ለማብቃት መጣር አለበት፡፡ፓርላማው ዴሞክራሲንና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ብሎም የህዝብን ተሳትፎ ለማጎልበት ለሕዝብ ክፍትና በቀላሉ ተደራሽ መሆን ያለበት ሲሆን በዚህም ዜጎቹ አስተዳደርን ጨምሮ ሕይወታቸው በሚነካ የፓርላማውን የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት በቅርበት እንዲከታተሉ ማድረግ አለበት፡፡ ለዚህ ጥረት መሳካት ደግሞ የመገናኛ ብዙሃን ተሳትፎ እጅጉን አስፈላጊ ነው፡፡

ምክር ቤቶች የእውነት ተወካይ እንዲሆኑ ምርጫ ነፃ እና ፍትሃዊ መሆን አለበት፡፡ ዜጎች ስለ ምክር ቤት ስብሰባዎች ፣ ህጎች እና ፖሊሲዎች መረጃ ማግኘት እና ከፓርላማ አባላት ጋር ቀጣይነት ያለው ውይይት ማድረግ መቻል አለባቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ የምርጫው ጥራት ወሳኝ ነው፡፡ ምክነያቱም በተጨበረበሩ ምርጫዎች የተመረጡ ተወካዮች ሚናቸውን በተለይም የውክልና ሚናን ለመወጣት ይቸገራሉ፡፡ ነፃ፣ ፍትሃዊ እና ግልጽ የፓርላማ ምርጫዎች ታማኝ ፓርላማዎችን እና የፓርላማ አባላትን ተጠያቂነት ለመገንባት ወሳኝ ናቸው፡፡ በዲሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጠ ፓርላማ ብቸኛው ትክክለኛ የህዝብ ድምጽ ሲሆን ለሚያገለግለው ህዝብ ተጠያቂነት የዴሞክራሲ ስርዓት መሰረታዊ ምሶሶ ነው፡፡

### 3.2.4. የጠባቂ (Watchdog) ተቋማትን ለየት ባለ መንገድ የመደገፍ አቅምን ማሳደግ

**ማነቃቅያ ጥያቄ**

| |
|---|
| ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል የተለየ ድጋፍ የሚፈልጉ የመንግስት ተቋማት የትኞቹ ናቸው? |

ምክር ቤት ቁልፍ ከሆኑ የክትትል እና ምጥጥን (checks and balances) ተቋማት መካከል አንዱ ሲሆን ሌሎች ተመሳሳይ ሚና ያላቸው ተቋማት ደግሞ ከፍተኛ የኦዲት ተቋማት ፣ እንባ ጠባቂዎች፣ ፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች፣ የፍትህ አካላት፣ ነፃ ፕሬስ የመሳሰሉትን ናቸው፡፡ በዚህም የተነሳ ምክር ቤቶች ከነዚህ ተቋማት ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ወሳኝ ሚና አለው፡፡ ስለዚህም ፓርላማው እነዚህን ተቋማት በተለየ ሁኔታ መደገፍ ይጠበቅበታል፡፡

የዋና የኦዲት ተቋማት የመንግስት ሂሳቦችን የማጣራት ሃላፊነት ያለባቸው ብሄራዊ ኤጀንሲዎች ናቸው፡፡ ሕገ መንግሥታዊ ሥልጣናቸው፣ የሪፖርት ግንኙነታቸው እና ውጤታማነታቸው ከአገር አገር እና በአገሮች ውስጥ ባለው የመንግሥት ፖሊሲ መሠረት የሚለያይ ቢሆንም ዋና ዓላማቸው የመንግሥትን የሕዝብ ገንዘብ አስተዳደር፣ የጥራት እና ተዓማኒነት እንዲሁም ሪፖርት የተደረገ የመንግስት የፋይናንስ መረጃ የበላይ ተመልካቾች ሆነው መሥራት ነው፡፡

በዌስትሚኒስተር ስርዓት፣ ዋና የኦዲት ተቋማት የፓርላማ ቁጥጥር ተግባር ዋና አካል ነው፡፡ ምክነያቱም ውጤታማ የቁጥጥር ተግባር የመንግስት ወጪዎችን እና ገቢዎችን መመርመርን ስለሚጠይቅ ጥቂት የፓርላማ አባላት ይህንን ተግባር ለመፈፀም ክህሎት ስላላቸው፣ ምክር ቤቶች በተለይም በዋና የኦዲት ተቋማት ላይ በመንተራስ የመንግስት ሂሳቦችን ኦዲት ያደርጋሉ፡፡

የዋና የኦዲት ተቋማት ውጤታማ ስራ መስራት እንዲችሉ የኦዲት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች በማዘጋጀት እና በፍትሃዊነት፣ ትክክለኛ እና ተጨባጭ የኦዲት ውጤቶችን ሪፖርት የማድረግ ነፃነትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ሌላው በምክር ቤት ሊወሰድ የሚገባው ወሳኝ እርምጃ ደግሞ በኦዲት ሂደት ውስጥ በተገለጹት ችግሮች ላይ የእርምት እርምጃ ለመውሰድ ለኦዲት ውጤቶች ተገቢውን ትኩረት መስጠት ነው፡፡

የዋና የኦዲት ተቋማት በክትትል ተግባራቱ ውስጥ ለምክር ቤት ታማኝ እና በጣም ጠቃሚ እንዲሆን ከተፈለገ በምክር ቤትም ሆነ በሌሎች የመንግስት አካላት እንደ ገለልተኛ አካል በሃላፊነት ወሰኑ ውስጥ ባሉ ጉዳዮች ላይ የራሱን ውሳኔ መስጠት መቻል አለበት፡፡

ምክር ቤቱም ሆነ የኮሚቴዎቹ ከ ዋና የኦዲት ተቋማት ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት እንደ ትብብር መታየት አለበት፡፡ በዚህ ረገድ የዋና የኦዲት ተቋማት ኦዲት የሚደረግባቸው ጉዳዮችን የመምረጥ (በህግ ከተለዩት በስተቀር) እና እነዚያን ኦዲቶች እንዴት በተሻለ መንገድ ማከናወን እንደሚቻል የመወሰን ስልጣን ሊኖራቸው ይገባል፡፡

የምክር ቤት ኮሚቴዎች ለዋና የኦዲት ተቋማት  በተለይ አሳሳቢ ሆነው የሚያገኟቸውን ርዕሰ ጉዳዮች ኦዲት ላይ ኦዲት እንዲደረግ ሀሳብ በሚያቀርቡበት ጊዜ የዋና የኦዲት ተቋማት ለእንደዚህ አይነት ሀሳቦች ከፍተኛ ትኩረት መስጠት መቻል አለባቸው፡፡ ይህን ሲያደርጉ ግን የምክር ቤት ኮሚቴዎች በዋና የኦዲት ተቋማት አመታዊ የኦዲት ፕሮግራም ውስጥ እንዲካተት ያቀረቡት ማንኛውም ሀሳብ ወይም ለኦዲት መርሃ ግብሩ ላይ ያነሱት ተጨማሪ ጥያቄዎች በዋና የኦዲት ተቋማት  በኦዲት ስራው ውስጥ የራሱ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ጉዳዮች ፣ የበጀት ድልድል እና የሰራተኛ ውስንነቶች አንፃር የግድ መታየት እንዳለበት እና የመጨረሻው ውሳኔም የዋና የኦዲት ተቋማት ላይ የተመሰረተ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ሌላው ምክር ቤቱ እና ኮሚቴዎቹ ያቀረቡትን የኦዲት ሪፖርቶችን የሚመለከቱበትን መንገድ በተመለከተ ግልጽ ህጎችን እና ሂደቶችን መደንገግ ይጠበቅበታል፡፡ በተለይ ለኦዲት ሪፖርቶች ምላሽ የመስጠት ኃላፊነት ያላቸው አንድ ወይም ከዚያ በላይ የፓርላማ ኮሚቴዎች መኖራቸው የመንግስት እና የህብረተሰቡን ትኩረት ከኦዲት ሪፖርቶች በሚነሱ ግኝቶች እና ምክሮች ላይ እንዲያተኩር እና የውሳኔ ሃሳቦችን ተግባራዊ ለማድረግ ጫና ለመፍጠር ይረዳል ፡፡

በአጠቃላይ ውጤታማ ከፍተኛ ኦዲት ተቋማት እንዲኖሩ እና የቁጥጥር ስራውን ለማሳለጥ ምክር ቤቱ የሚደግፍ አካባቢያዊ ሁኔታ በመፍጠር፣ ስልጣንና ሃለፊነታቸውን በህግ በግልጽ በመደንገግ፣ ነጻነታቸውን በመጠበቅ እና በቂ የገንዘብ ድጋፍ ፣ ምንጭ እና ሰራተኞች እንዲኖራቸው በማስቻል ሃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል፡፡

### 3.2.5. የሙስናና ብልሹ አሠራርን መረጃ ማግኛ ሥርዓት ማጠናከር



**ማነቃቅያ ጥያቄ**

| |
|---|
| መረጃ ማግኛ ሥርዐት ማለት ምን ማለት ነው? |

የተወካዮች ምክርቤት አባላት ከተለያዩ አካባቢዎችና ክልሎች የተውጣጡ ሕግ አውጪ አካላት በመሆናቸው የሕዝብ ዓይንና ጆሮ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣውን ሙስናና ብልሹ አሠራር ለመከላከል አንዱ መንገድ መረጃ እና ጥቆማ የማግኛ መንገዶችና ዘዴዎችን ማጠናከር ይገባል፡፡ ምክር ቤቱ በዓይነትና በመጠን እያደገ፣ እየሰፋ እና እየዘመነ ከመጣው ከመገናኛ ብዙኃን ጋር በቅርበት በመሥራት ጠቃሚ መረጃዎችን የማግኘት አቅምን

ማሳደግ ተገቢ ነው። የሕዝብ ተወካዮች አባላትም ዘመናዊ የመገናኛ ሥልቶችን በመጠቀም የወከላቸውን ማኅበረሰብ በቅርብ የማግኘት አሠራሮችን ተግባራዊ የማድረግ አቅምን መፍጠር ተገቢ ነው።

የምክር ቤት አባላት የሚጫወቱት ጠቃሚ ሚና የዜጎችን ፍላጎትና ምርጫ መግለጽ እና ህግ በማውጣት ወደ ፖሊሲ መቀየር ነው። ለዚህም የፓርላማ አባላት በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ለማድረግ ሰፊ የመረጃ እና የእውቀት ግብዓቶችን በቀላሉ ማግኘት መቻል አለባቸው። በመረጃ ቋቶች፣ ኢንተርኔት እና ዲጂታል ቤተ-መጻሕፍት፣ የምክር ቤት አባላት እንደ ህጎች እና ሂደቶች ካሉ የሕግ አውጪ ሰነዶች ጋር የተያያዙ ግብዓቶችን በብቃት ማግኘት ይችላሉ። በኢንተረኔት መረብ ላይ የህግ አውጪ ኮሚቴ ሪፖርቶችን በፍጥነት በማግኘት እና በሂደት እና በክርክር ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ህጎች የመከታተያ ዘዴ በመጠቀም የህግ አውጭነት ስራቸውን ጥራት ማሳደግ ይቻላል።

ከዚህ በተጨማሪም የምክር ቤት አባላት የወቅቱን ውስብስብ የፖሊሲ ጉዳዮች ለመረዳት በገለልተኛ እና አስተማማኝ የምክር ቤት ጥናትና ምርምር፣ የመረጃ አገልግሎት፣ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ከመገናኛ ብዙሃን ጋር ባለው ግንኙነት የመረጃ ተደራሽነታቸውን ማሳደግ እና ማመቻቸት አለባቸው።

ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ከሚረዱ ዘዴዎች አንዱ እና ዋንኛው ኢ-መንግስት ነው። በዚህ ረገድ ከሚሳጣቸው ጥቅሞች መካካል የሚከተሉት መጥቀስ ይቻላል።

- ☞ በቢሮ ሃላፊዎች እና በዜጎች መካከል ያለውን የመረጃ አለመመጣጠን በመቀነስ፣ ሙስና ጣልቃ ሳይገባ መብታቸውን እንዲያረጋግጡ ያስችላቸዋል።
- ☞ የቢሮ ሃላፊዎችን ውሳኔ መገደብ፣ ጉቦ የመቀበል እድላቸውን መቀነስ
- ☞ በሙስና የተዘፈቁ ኔትወርኮችን ለማዳበር እድሎችን በሚፈጥሩ የቢሮ ሃለፊዎችን እና ዜጎች መካከል ያለውን ግንኙነት ለመቀነስ የተወሰኑ ሂደቶችን ማቀላጠፍ እና በራስ ሰር መስራት።
- ☞ ብዙ ጊዜ ጉቦ የሚሰጡ አቀባዮችን ማስወገድ
- ☞ በሕዝብ ቢሮክራሲዎች ውስጥ ሬድ-ቴፕ በመቀነስ ለሙስና ሊገቡ የሚችሉ ነጥቦችን ያስወግዳል
- ☞ ከመንግስት ባለስልጣናት ጋር የሚደረጉ ግብይቶችን ግልፅነት ማሳደግ፣ ብልሹ ባህሪን ለመከላከል አዲት ማድረግ ይችላሉ

- ዜጎች በሙስና ላይ እንዲደራጁ፣ ሪፖርት እንዲያደርጉ እና እንዲንቀሳቀሱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የሚሄድ የጋራ የድርጊት መሳሪያዎችን እና መድረኮችን ማቅረብ፡፡
- እርካታን በመደበኛነት ለመከታተል፣ ችግሮችን ለመለየት፣ ሙስናን ሪፖርት ለማድረግ እና የአገልግሎት ጥራትን ለማሻሻል ከአገልግሎት ተጠቃሚዎች ግብረ መልስ እና ሪፖርቶችን መቀበል

### 3.2.6. የዜጎችን አመኔታ የሚገነቡ ተግባራትን ማጠናከር እና አርአያ መሆን

**ማነቃቅያ ጥያቄ**

| |
|---|
| የተወካዮች ም/ቤት አባላት ለዜጎች አርአያ የሚሆኑባቸውን ሁኔታዎች ዘርዝሩ፡፡ |

ነፃና ፍትሐዊ የምርጫ ሥርዓት እንዲዳብር የሚያደርጉ አሠራሮችን እንዲጎለብቱ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ከታችኛው የአስተዳደር አካል በምርጫ የሚያዙ ኃላፊነቶች ሕዝብ የተሳተፈባቸው በነፃና ተአማኒነት ባለው ምርጫ ሥርዓት የማካሄዱ ባህልም ሊጎለብት ይገባል፡፡ የዚህ መሰል የምርጫ ባህል ባደገበት ሁኔታ ወደ ሕዝብ ውክልና የሚመጡ አካላት ሙስናና ብልሹ ተግባራት የመከላከል አቅማቸውና ቁርጠኝነታቸው የጎለበት ይሆናል፡፡ ዜጎችም የሚያዩአቸውን ብልሹ አሠራሮች ለተወካዮቻቸውና ለመንግሥት ተቋማት መረጃ በመስጠትና ጥፋቶችን በማጋለጥ ሙሉ እምነት ይኖራቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት እና የምክርቤት አባላት የሕዝብ ውክልና ሥርዓትን ዴሞክራሲዊ በማድረግ ሂደት የላቀ ሚና ሊወጡ ይገባል፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ሕግ የማውጣት እና የወጡ ሕጎች አፈጻጸም የመከታተል ኃላፊነቱ በተጓዳኝ በአሠራሩም እያንደንዱ ተወካይ በግሉ እና በተቋም ደረጃ የመልካም ሥነምግባር ምሳሌ በመሆን ከሙስናና ብልሹ አሠራር መከላከል የላቀ ሚና መወጣት አለባቸው፡፡ ይህንን ተግባር በብቃት እንዲወጡ ደግሞ እራሳቸው ታማኝነትን፣ መተማመንን እና ህጋዊነትን ማሳደግ እና ማጠንከር አለባቸው፡፡

ይህም ምክር ቤቶች የሚመረጡበት ሂደት ግልጽና ፍትሃዊ እንዲሆንና የህብረተሰቡን ፍትሃዊ ውክልና ማረጋገጥ እንዳለበት ይጠይቃል፡፡ በተጨማሪም የምክር ቤት አባላት እንደ የሥነ ምግባር/የሥነ ምግባር ደንቦች፣ ከሌሎች ድንጋጌዎች፣ የንብረት መግለጫ፣ የጥቅም ግጭት ሕግ፣ ወዘተ የመሳሰሉትን ጨምሮ ለራሳቸው የታማኝነት መሣሪያዎችን መንደፍ እና መተግበር አለባቸው፡፡

ምክር ቤቶች እንደ የህዝብ ተወካይ አካላት እንደመሆናቸው በአባሎቻቸው እና በሰራተኞቻቸው መካከል ተቋማዊ የህዝብ ታማኝነት ባህልን ማስተዋወቅ እና ማስቀጠል በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

ምክር ቤቶች ጉዳዮቻቸውን በሙያዊ ብቃት መምራት እና ለሁሉም ዜጎች አክብሮት ማሳየት አለባቸው፡፡

በተጨማሪም ምክር ቤቱ ጠንካራ መመዘኛዎች እና ደንቦች በማዘጋጀት የምክር ቤት አባላት እንዴት አይነት ባህሪ ሊኖራቸው እንደሚገባ ግልጽ መመርያ በማውጣት፣ እንዴት በትክክል እንደሚሠሩ በመከታተል እና ጥሰቶችን በመቅጣት ስልጣንን አለአግባብ መጠቀም እና ሌሎች የሙስና ዓይነቶችን ለመከላከል ይረዳል፡፡

የምክር ቤት አባል ሚና ውስብስብ እና በርካታ የስነምግባር ግርታዎችን ሊፈጥር ይችላል፡፡ ግልጽ እና በቋሚነት የሚተገበሩ መመዘኛዎች መኖር ለምክር ቤት አባላት እና ለሰራተኞቻቸው ህዝቡ ምን አይነት ጠባይ እንዲኖራቸው እንደሚጠብቅባቸው በግልጽ እንዲረዱ ያስችላሉ፡፡

ነገር ግን ደንቦች ሲዘጋጁ የምክር ቤት ተግባራትን በመተግበር ላይ ጣልቃ መግባት በሚያስችል መልኩ መሆን የለበትም፡፡ ለምሳሌ ተወካዮች አላስፈላጊ የቢሮክራሲያዊ ሂደቶችን እንዲያልፉ የሚጠይቁ እንዳይሆኑ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡ በተቃራኒው ደንቦች የፓርላማ አባላት የውክልና፣ የመመርመር እና የህግ አውጭነት ሚናቸውን የሚጫወቱበት ፍትሃዊ እና የተረጋጋ ሁኔታ እንዲፈጥሩ ይጠበቃል፡፡

በደንብ የተገለጹ የምክር ቤት የሥነ ምግባር መመዘኛዎች ለሕዝብ እና ለመገናኛ ብዙኃን የሚዳኙበትን ግልጽ መለኪያዎች በመስጠት ተጠያቂነትን ያሻሽላሉ፡፡ ዜጎች ሥነ ምግባርን የመቆጣጠር ሥርዓት ፍትሃዊ እና ውጤታማ ነው ብለው ካመኑ እና ማንኛውም በደል በግልጽ እንደሚወጣ እና እንደሚቀጣ ካወቁ ፓርላማው በሚሰራው ስራ ላይ በቀላሉ እምነት እንዲያሳድሩ ያስችላል፡፡

ነገር ግን ምክር ቤቱ ካልታመነ መሰረታዊ ተግባራቶቹን ማለትም የመቆጣጠር፣ የመወከል እና ህግ የማውጣት አቅሙን ያዳክማል፡፡ ብዙውን ጊዜ ግልጽ የሆኑ ሂደቶች እና ከሥነ ምግባር ጋር የተያያዙ ደንቦችን ከውጤታማ ማዕቀቦች ጋር አዳምሮ መተግበር ወሳኝነት አለው፡፡ በእርግጥ ግልጽ መመዘኛዎች መኖራቸው በተለይ የሚዲያ ምርመራ ከፍተኛ በሆነበት አካባቢ ለምክር ቤት አባላት ጠቃሚነቱ የጎላ ነው፡፡

የምክር ቤት አባላት የሚመረጡት ከተለያዩ አስተዳደግ፣ ጸታዎች እና ሙያዎች ነው፡፡ ይህ ብዝሃነት መራጮችን ለመወከል ችሎታቸው አስፈላጊ ነው፡፡ ምክር ቤት ከገቡ በኋላ ግን ሁሉም የምክር ቤት አባላት በቢሮ ውስጥ ስነምግባርን በሚመለከት ተመሳሳይ ህጎችን ማክበር

አለባቸው። ግልጽ ደረጃዎች የምክር ቤት አባላትን አንድ ለማድረግ ይረዳሉ። ይህም የፖለቲካ ልዩነቶችን እንዲያሸንፉ እና የባልደረባነት ስሜት እንዲገነቡ ያስችላቸዋል።

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል አቅማቸውን ለማሳደግ የሚገለግሉ ተግባራት ተዘርዝረዋል። አባላቱን በጽንሰ ሃሳቡ ዙሪያ ግንዛቤ ማጎልበቻ ስራዎች መሥራት፣ ከፖለቲካ ፓርቲ ወገንተኝነት ነፃ መሆን፣ የዴሞክራሲ ሥርዓት መጎልበት ላይ የላቀ ሚና መጫወት ምክርቤቶች ሙስናና ኢ-ሥነምግባራዊ ድርጊቶችን የመከላከል ኃላፊነትን ለመወጣት ዓይነተኛ ሥልቶች ናቸው። ከነዚህ በተጨማሪ መረጃ መሰብሰብና ማግኛ መንገዶችን ማጠናከር ምክርቤቱ ሙስናና ብልሹ አሠራርን በመከላከል የዜጎችን አመኔታ መገንቢያ ጠቃሚ ተግባራት ናቸው። ስለሆነም የርእሱን ዝርዝር ይዘቶች እንዲያበለጽጉ በተመቻቹት የቡድን ውይይቶች አማካይነት የሠልጣኞች ዕውቀትና ተመክሮ የሚዳብር መሆኑ ይታመናል።

በዚህ ምዕራፍ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ሙስናና ብልሹ አሠራርን በመከላከል ረገድ ሊወጣ የሚገባቸውን አንኳር ተግባራት ተብራርተዋል። ከነዚህ መካከል የመንግሥት ተቋማትን መከታተል፤ በአካል ተገኝቶ መመልከትና ማገዝ ዋነኛው ተግባሩ ነው። ምክርቤቱ በክትትልና ምልከታው ሙስናና ብልሹ አሠራርን የሚከላከሉ ተቋማት መቋቋማቸውን፣ ወቅታዊ የፀረ-ሙስና ሕግ ማዕቀፎች መዘርጋታቸውን ትኩረት ያደርጋል ። በመንግሥት ተቋማት የሚመደቡ ወይም የሚሾሙ አካላት ዕውቀት፣ ብቃት፣ ልምድ እና ሥነምግባር መስፈርቶች ተግባረዊ እንዲሆኑ የማድረግ ሚና መወጣት አለባቸው። እነዚህ አካላት ሙስናና የመከላከል ቁርጠኝነታችን እንዲዳብር ምክርቤቱ እገዛ የማድረግ ኃላፊነት አለበት። ሙስናና ብልሹ አሠራር የሚፈፅሙ አካላት ካሉም እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው በማድረግ የተጠያቂነት ሥርዓትን የማጠናከር ኃላፊነት አለበት። ስለሆነም የርእሱን ዝርዝር ይዘቶች እንዲያበለጽጉ በተመቻቹት የቡድን ውይይቶች አማካይነት የሠልጣኞች ዕውቀትና ተመክሮ የሚዳብር መሆኑ ይታመናል።

## የምእራፍ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**የሚከተሉትን አጠቃላይ ጥያቄዎች አሰልጣኙ ከስር በቀረቡት ትዕዛዞች መሠረት መልሱ።**

i. ከታች በሠንጠረዥ ውስጥ በሰፈሩት ሐሳቦች ላይ የሀገራችን የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ሙስናን እና ብልሹ አሠራርን በመከላከል ያለውን የእንቅስቃሴ ደረጃ ከ1–4 ነጥብ በመስጠት አመልክቱ፤ ተጨባጭ ምሳሌም አስቀምጡ። (4 - **በጣም ከፍተኛ** ፣ 3 - **ከፍተኛ** ፣ 2 - **ዝቅተኛ**፣ 1 - **በጣም ዝቅተኛ**)

| ተ.ቁ | የተወካዮች ም/ቤት ሙስናን ለመከላከል ያደረገው ጥረት መገለጫዎች | ነጥብ | ምሳሌዎች |
|---|---|---|---|
| 1 | የሙስና ወንጀልን ለመከላከል የሚያግዙ ሕጎች መውጣታቸውን እና የወጡት ሕጎች ተግባራዊነታቸውን መከታተል | | |
| 2 | ሙስናን ለመከላከል የተቋቋሙ ተቋማትን መከታተልና መደገፍ | | |
| 3 | የምልከታና ክትትል ኃላፊነትን በሚፈለገው ደረጃ መወጣት | | |
| 4 | የመንግሥት ተቋማት የውስጥ አሠራር ከሙስና መከላከል የሚስችሉ ስርአቶች መዘርጋታቸውን እና ውጤታማነታቸውን መከታተልና መፈተሽ | | |
| 5 | ሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ራሱን ከሙስናና ብልሹ አሠራር ማፅዳትና ምሳሌ መሆን | | |
| 6 | በሀገር ደረጃ የስራ ሥነምግባር ግንባታን የማጠናከር ስራዎችን እና በዚህ ደረጃ ኃላፊነት ያላቸውን አካላት መደገፍ | | |
| 7 | የሲቪክ ማኅበራት እና የሚዲያ አካላት ሙስናና ብልሹ አሠራርን የመከላከልና የመዋጋት አቅማቸውን መደገፍ | | |
| 8 | ዓለማቀፍ እና አህጉር አቀፍ የፀረ-ሙስና ትግልና ትብብር እንዲጠናከር ማገዝ | | |

ii. የሀገሪቱን ዓመታዊ በጀት ለመመደብ በሚደረግ ሂደት ላይ ለሙስና የሚጋለጡ አካባቢዎችን በመለየት በምሳሌዎች የተደገፉ ማብራሪያዎችን ስጡ፤

iii. በመንግስት አስፈፀሚው አካል አቅራቢነት የተወካዮች ም/ቤት ሹመታቸውን የሚያፀድቅላቸው እጩዎች "በሥነምግባራቸው የተመሰገኑ ናቸው" ለሚለው መገለጫዎቹ ምን እንደሆኑ ግለፁ፡፡

iv. ፕሬዝዳንት ሙሃማዱ ቡሃሪ እ.አ.አ በ2015 ምርጫ ወደ ስልጣን የመጡት በሁለት ቁልፍ መልእክቶች ጀርባ ሲሆን እነሱም የደህንነት ሁኔታን ማሻሻል እና ሙስናን ለመዋጋት የሚደረገውን ትግል ማደስ የሚሉት ነበሩ ፡፡ ከነዚህም ቢያንስ በሁለተኛው አንዳንድ ለውጥን ማሳየት ችለዋል፡፡ አስተዳደራቸው ከአሜሪካ፣ ከእንግሊዝ እና ከተለያዩ የመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ጋር በህገወጥ ገንዘብ ተገዝተዋል ተብለው የተጠረጠሩትን የመንግስት ባለስልጣናት ንብረት ለመያዝ እና ወደ ሀገራቸው ለመመለስ በቅርበት ሰርቷል፡፡ የናይጀሪያ ግንባር ቀደም የፀረ-ሙስና ኤጀንሲ የኢኮኖሚ እና የፋይናንስ

ወንጀሎች ኮሚሽን (ኢ.ኤፍ.ሲ.ሲ.) የበለጠ እንዲንቀሳቀስ ሆኗል ። በዚህም የቀድሞ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት በተለይም በቀድሞ የካቢኔ አባላት፣ በክልል አስተዳዳሪዎች እና በከፍተኛ የመንግስት ሰራተኞች ላይ ተከታታይ ምርመራ ጀምሯል።

ነገር ግን፣ እ.አ.አ በየካቲት 2019 መራጮች ወደ ምርጫው ከመመለሳቸው ጥቂት ወራት በፊት፣ የቡሃሪ ፀረ-ሙስና ዘመቻ በህዝቡ ዘንድ ያለው ተቀባይኘት ደካማ ነበር። በቡሃሪ አስተዳደር መጀመሪያ ዘመን በርካታ ከፍ ያሉ ባለስልጣናት ላይ የሙስና ክስ ቢመሰረትም፣ በምርመራዎች ላይ አልፎ አልፎ ከፍተኛ የቅጣት ውሳኔዎችን ማሳለፍ አልተቻለም። የቡሃሪ ተቺዎች ማለትም በራሳቸው በገዥው ኦል ፕሮግረሲቭስ ኮንግረስ (ኤፒሲ) እና በተቃዋሚው ፒዲፒ ውስጥ ያሉት- የፀረ-ሙስና ጥረቶችን የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን ለማጥቃት እየተጠቀመበት ነው ይላሉ። ከዚህ አስረጅ ናሙና በመነሳት

☞ የፕሬዝዳንቱ የጸረ-ሙስና ትግል በህዝቡ ዘንድ ለምን ያነሰ ቅቡልነት አስገኘ?

☞ በፕሬዝዳንቱ ላይ የሚነሳውን ክስ ተገቢነት እንዴት ትመለከቱታላችሁ?

☞ የፕሬዝዳንቱ ተግባር በሌሎች መንግስት ተቋማት ላይ ያለው አንድምታ ምን ሊሆን ይችላል?

i. ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት ሲባል በምን ይገለጻል?

ii. የሕዝብ ተወካይ ምክርቤት አፈጉባኤ ተከታታይ የውጪ ጉዞ ያደርጋል። በዚህ ድርጊቱ ብዙ የምክርቤት አባላት በአፈጉባኤው ላይ ቅሬታ ያሰማሉ። ሆኖም ይህን ጉዳይ ለውይይት ብናቀርበው ፓርቲያችንን ለትችት ማጋለጥ ነው በሚል ነገሩ ተዳፍኗል። በዚህ ረገድ በሀገራችን የፖርቲ ወገንተኝነት ሙስናና ብልሹ አሠራርን በመከላከል የሚያሳድረውን አሉታዊ ተፅዕኖ ዘርዝሩ።

iii. የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል ልዩ ድጋፍ የሚፈልጉ እንደ የፌደራል ስነ መግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን፣ እምባ ጠባቂ እና ዋና ኦዲተር የመሳሰሉ ተቋማትን በምን በምን መደገፍ እንዳለበት ዘርዝሩ።

iv. የምክርቤቱ አባላት ከሙስና እና ብልሹ አሰራር የጸዳ ስብእና ምሳሌ በመሆን የላቀ እና የጎላ ሚና እንዲጫወቱ መሰራት አለባቸው የምትሏቸውን ተግባራት ዘርዝሩ።

v. የምክር ቤት አባላትን ስራ አስፈጻሚውን በተለይ ደግሞ የበጀት ቁጥጥን በተሻለ ሁኔታ እንዲፈጽሙ ምን አይነት ድጋፍ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ጥቀሱ።

**አባሪ 1**

**ከስልጠና በፊት የሰልጣኞች መገምገሚያ መጠይቅ**

(ሙስናን በመከላከል እና ሥነምግባር በማጎልበት ረገድ የምክር ቤቶች ሚና)

| ተ.ቁ | ርዕሰ ጉዳይ | በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ከዚህ በኃላ ያለዎት ግንዛቤ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ(5) | ከፍተኛ (4) | መካከለኛ (3) | ዝቅተኛ (2) | በጣም ዝቅተኛ (1) |
| 1 | የሙስና ጽንሰ ሃሳብ ምንነት | | | | | |
| 2 | ሙስና የሚያደርሳቸውን ጉዳቶች | | | | | |
| 3 | የሙስና መከላከያ ሥልቶች | | | | | |
| 4 | የሥነምግባር ምንነት እና መሠረታዊ ባሕርያትና ገጽታዎች | | | | | |
| 5 | የሙያ ሥነምግባርን ምንነትና ፋይዳ | | | | | |
| 6 | የሥነምግባር ደንብን አስፈላጊነት | | | | | |
| 7 | ሥነ ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ | | | | | |
| 8 | የምክር ቤት የሙስና ስጋትና ታጋላጭነት | | | | | |
| 9 | በምክር ቤት የሚፈጸሙ የሙስና አይነቶች | | | | | |
| 10 | የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ሙስናና ብልሹ አሠራርን በመከላከል የሚጫወቱትን ሚና | | | | | |
| 11 | የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ሙስናና ብልሹ አሠራርን በመከላከል ረገድ በዓለማቀፍና በሀገር አቀፍ ደረጃ የተስተዋሉ ምርጥ ተመክሮዎችን | | | | | |

አባሪ 2

**ከስልጠና በኃላ የሰልጣኞች መገምገሚያ መጠይቅ**

(ሙስናን በመከላከል እና ሥነምግባር በማጎልበት ረገድ የምክር ቤቶች ሚና)

## ዋቢ ምንጮች

| ተ.ቁ | ርዕሰ ጉዳይ | በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ከዚህ በኃላ ያለዎት ግንዛቤ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ( 5) | ከፍተኛ (4) | መካከለኛ (3) | ዝቅተ ኛ (2) | በጣም ዝቅተኛ (1) |
| 1 | የሙስና ጽንሰ ሃሳብ ምንነት | | | | | |
| 2 | ሙስና የሚያደርሳቸውን ጉዳቶች | | | | | |
| 3 | የሙስና መከላከያ ሥልቶች | | | | | |
| 4 | የሥነምግባር ምንነት እና መሠረታዊ ባሕርያትና ገጽታዎች | | | | | |
| 5 | የሙያ ሥነምግባርን ምንነትና ፋይዳ | | | | | |
| 6 | የሥነምግባር ደንብን አስፈላጊነት | | | | | |
| 7 | ሥነ ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ | | | | | |
| 8 | የምክር ቤት የሙስና ስጋትና ታጋላጭነት | | | | | |
| 9 | በምክር ቤት የሚፈጸሙ የሙስና አይነቶች | | | | | |
| 10 | የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ሙስናና ብልሹ አሠራርንበመከላከል የሚጫወቱትን ሚና | | | | | |
| 11 | የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ሙስናና ብልሹ አሠራርን በመከላከል ረገድ በዓለማቀፍና በሀገር አቀፍ ደረጃ የተስተዋሉ ምርጥ ተመክሮዎችን | | | | | |

Federal Anti Corruption Commision of Ethiopia. (2012) Ethiopian Second Corruption Survey. Volume 1

Fjeldstad, O.(2002) “The fight against corruption and the role of parliamentarians”. Chr. Michelsen Institute: Working Paper 6. Bergen, Norway

Harutyunyan, K.(2021) The Role of Parliaments in the Fight Against Corruption. Westminister Foundation of Democracy

Jonston, M.(1997) “public officials, private interests and sustainable Democracy: connection between politics and corruption.” In kimberily A. Elliot (ed.) Corruption and the Global Economy. Institute for International Economics, Washington D.C.

Klitgaard R. (1988) Controling Corruption University of California Press፡ London England

Mare, C.(2007) Parliamentary Approaches to Corruption. U4 Helpdesk Transparency International.

Marie, L. (ND) Understanding and Mainting Ethical Values in the Public Sector Through an Integrated Ethical Approach to Leadership.

OSCE/ODIHR (2022) Parliamentary Integrity: A Resource for Reformers. Warsaw,Poland.

Power G. Handbook on Parliamentary Ethics and Conduct A Guide For Parliamentarians.

Rose-Ackerman, S. (1996) “Democracy and ‘Grand corruption’”. International Social Science Journal. Special Issue on Corruption in Western Democracy

Stapenhurst, R. & Pelizzo, R. (2004) Legislative Ethics and Codes of Conduct. World Bank Institute

The International Bank for Reconstruction and Development/The World Bank (2006) The Role of Parliament in Curbing Corruption. Stapenhurst R. Etal (ed.) Washington DC.

UNODC. (2017) Module Serious on Anti- Corruption. Module 1 What is Corruption and Why Should We Care?

World Bank (2006) Diagnising Corruption inEthiopia, Perceptions, Realities, and the Way Forward for Key Sectors. Library of Congress, Washington D.C.

የፌደረራል ስነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን (2014 ዓ.ም) ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፣የሲቪል ማህበራት እና የፖለቲካ ፓርቲዎች ሙስናን የመከላከል ሚና በሚል የተዘጋጀ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
**FEDERAL ETHICS AND ANTI-CORRUPTION COMMISSION**

ስልክ;- +251115-52-77-85/+251115-53-69-01
ፖሳቁ P.O.Box :- 34798/99
ኢ-ሜይል:- E-mail FeaccEthiopia2013@et
ፌስቡክ/www.facebook.com/feaccOfficial
ድረ-ገጽ/ www.feacc.gov.et